Alemu & Bedilu

# የወንጌል ባለአደራ

በበቀለ ሻንቆ

አሳታሚ፡- የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ - ኢትዮጵያ
የመ.ሣ.ቁ. 41303
አዲስ አበባ

የወንጌል ባለአደራ

**A STEWARD OF THE GOSPEL**

**Copyright © 1999, 2004 by Bekele Shanko**

የመጀመሪያ ዕትም 1991 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም 1997 ዓ.ም.

ይህን መጽሐፍ ወይም የመጽሐፉን ማንኛውንም ክፍል ለማባዛት፣ ወይም ለመገልበጥ፣ ለመቅረጽ፣ ወዘተ የሚቻለው ደራሲውን በማስፈቀድ ብቻ ነው ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት

1. በ1954 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ
2. በ1980 ዓ.ም. ከታተመው አዲስ ትርጉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ
3. እ.ኤ.አ. በ1985 ከታተመው ሕያው ቃል የአማርኛ አዲስ ኪዳን

የሽፋን ስዕል በልዑል ገብርኤል

አሳታሚ፦ የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ - ኢትዮጵያ

ንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ
አዲስ አበባ

## መታሰቢያ

ይህ መጽሐፍ፦

ጊዜ፣ ሁኔታና ቦታ በማይሽረው የፍቅር እሳት ልባቸው እየነደደ ፣ ከጌታ የተቀበሉትን የወንጌልን ተልዕኮ በታማኝነት ለመፈጸም ሕይወታቸውንና ነፍሳቸውን ሳይሳሱ ለወንጌል ለሰጡ በየትውልዱ ሁሉ ለኖሩ መታሰቢያ ይሁን ።

## *ማስታወሻ*

ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ የሚገኝ ማናቸውም ገቢ ወንጌል ያልደረሳቸው ወንጌልን እንዲሰሙ የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪን የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴ ለመደገፍ እንዲውል የተሰጠ ነው ::

## *የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለዚህ መጽሐፍ ምን አሉ?*

"በዚህ ጥሩ ዘመን፣ 'በእኛ' አካባቢ፣ ከተጻፉት ጥሩ ጥሩ መጻሕፍት መካከል 'የወንጌል ባለአደራ' የተሰኘች ይህች መጽሐፍ አንድዋ ናት። በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ሞክሼ ስለወንጌል፣ ወንጌልን ስለምንመሰክርላቸው ሰዎችና ስለራሳችንም ብዙ ጠቃሚና ገቢራዊ (PRACTICAL) ሀሳቦችን ያካፍለናል።

ይህም ብቻ አይደለም። ሞክሼ ዘንድሮ በ"የወንጌል ባለአደራ" በጽሑፍ ለእኛ የሚያስተላልፈውን መልዕክት አምና እራሱ በ"ዘመቻ ፊሊጶስ" በሥራ ላይ አውሎ አሳይቶናል። ሞክሼ አገራችን ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር በወንጌል ተደርሳ ለማየት ብዙዎቻችን የምናልመውን ሕልም ወደ እውን እንዲለውጥልን እግዚአብሔር ቁልፍ በሆነ ቦታ ያስቀመጠልን የተወደደ ወንድም ነው። ይህች መጽሐፉ የወንጌል ስርጭትን በተመለከተ ለብዙዎች እንደ መመሪያ (MANUAL) ትሆናለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።"

በቀለ ወልደኪዳን
ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን

"ይህ መጽሐፍ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወንጌልን ለማሠራጨት ያለበትን ኃላፊነት በብርቱ ያስገነዝባል። በተጨማሪም፣ ለወንጌል ምስክርነት እንቅፋት የሚሆኑ ምክንያቶችን ከነመፍትሄያቸው ያሳያል፣ የወንጌል መልዕክት ምን ማካተት እንዳለበት ይገልጻል፣ እንዴት መመስከር እንደሚቻልም ያብራራል።"

ዶ/ር ብርሃኑ ሃብቴ
ከብርሃን ወንጌል መጥምቃውያን ቤ/ክ

"የመጽሐፉን ረቂቅ ጽሁፍ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ደስ እያለኝና መንፈሴን እያጋለው አንብቤአለሁ። መጽሐፉ ስለ ወንጌል ምንነት፣ ወንጌልን የመመስከር አስፈላጊነት፣ በእግዚአብሔር ልብ ያለውን የሰውን መዳን፣ የእኛንም የወንጌል ባለአደራነት የዳሰሰ፤ ለሚያነቡት ሁሉ በተለይም ለክርስቲያኖች የመዳናቸውንና በዚህ ዓለም የመኖራቸውን ዋና ዓላማ በሚስቡ ቁም ነገሮች በማስደገፍ የተጻፈና ለወንጌል የሚያነሳሳ ነው። ወንድሜ በቀለ እግዚአብሔር ሲሰራ ካየውና በሕይወቱም ካለፈበት ተነስቶ ይህን መጽሐፍ ጽፏል። እግዚአብሔርም ይህን መጽሐፍ ለክብሩና ለታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ዕድገት እንዲያውል ጸሎቴ ነው።"

ጥላሁን ኃይሌ
ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

“ከደራሲው የግል ዕውቀት ባሻገር፣ የአገልግሎቱን የተጨመቀ ልምድ በመመርኮዝ ለወንጌል ስርጭት የሚጠቅሙ ሥልቶችንና ግንዛቤዎችን ያሰፈረበት መጽሐፍ ስለሆነ በማንኛውም ምዕመን መነበቡ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡”

ሰለሞን ሉሉ
ከኢትዮጵያ የክርስቲያን ነጋዴዎች ህብረት

“የወንጌል ባለአደራ መጽሐፍ በተለይ የወንጌልን ጥሪ ተቀብለው የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑ ምዕመናን፣ ለአገልጋዮችና ለመሪዎች ሁሉ፤ የወንጌልን ምንነት፣ ጥልቀቱንና ስፋቱን፣ የክርስትናንም ትርጉም እንደገና የሚያስገነዝብ ትምህርታዊና ወንጌልም እንዲሮጥ በግልና በህብረት ያለብንን ኃላፊነትና ተጠያቂነት በጉልህ የሚያሳይ ነው፡፡ የወንድም በቀለ ሻንቆ ብዕር ከሕይወቱና ከአገልግሎት ፍሬው የመነጨ ስለሆነ መጽሐፉ ለብዙዎች በረከት እንደሚሆን አምናለሁ፡፡”

ኩርሲ ሸፈኖ
ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

“የወንጌል ሥርጭት ዐቢይና ተቀዳሚ የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ነው፡፡ በአገራችን የሚገኙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና ምዕመናን ሕይወታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በበለጠና በተሻለ መንገድ ለዚህ ተቀዳሚ ተልዕኮ ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህ መጽሐፍም የአብያተ ክርስቲያናትን መሪዎችና ምዕመናንን ለወንጌል ሥርጭት ሊኖራቸው የሚገባውን የሕይወት መሰጠት የበለጠ ያበረታታል ብዬ አምናለሁ፡፡”

እንዳለ ገ/መስቀል
ከአዲስ አበባ ባይብል ኮሌጅ(ABC)

“ወንጌል በግል የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት፣ በማህበርም የቤተክርስቲያን ትልቁ አጀንዳ መሆን አለበት፡፡ ‘ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ’ የሚለው ትዕዛዝ የተሰጠው ለክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ ነው፡፡ ይህ ጽሁፍ አማኞች ሁሉ ወንጌልን ለሰዎች ለማዳረስ ያለብንን ታላቅ ኃላፊነት ከማስገንዘቡም በተጨማሪ ለመመስከር የሚፈልጉ ሁሉ የወንጌል አደራቸውን እንዲወጡ የሚያግዝና መንገዱንም የሚጠቁም ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ እያንዳንዱ አማኝ ሊያነበውና የወንጌል ድርሻውን ሊወጣ ይገባል እላለሁ፡፡”

መጋቢ ስለሺ ከበደ
ከገነት ቤተ ክርስቲያን

“ይህ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ወንጌላውያን አገልግሎታቸውን በየጊዜው የሚመዝኑበት፣ እንዴት እንደሚመሠከሩ ላላወቁ መመሪያ የሚሆን፣ በተለይ ለአዳዲስ አማኞች በትምህርት መልክ ቢሰጥ በወንጌል ማድረስ ከፍተኛ ፍሬ ማግኘት ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህም በክርስቲያኖች ሁሉ መነበብ ያለበት መጽሐፍ ነው፡፡”

ሳሙኤል ኃይሉ
ከክርስቲያን ሠራተኞች ህብረት

“የክርስቲያን በዚህ ዓለም የመኖሩ ዋናው ምክንያት የክርስቶስ ምስክር ለመሆን ነው፡፡ ዘመናችንን ስንመለከተው ግን ክርስቲያኑ ህብረተሰብ የመኖሩን ዓላማ የ‘ወንጌል ባለአደራ’ መሆኑን የረሳበት ዘመን ይመስላል፡፡ በዚህ ዝንጉነት በበዛበት ዘመን ወንድማችን አቶ በቀለ ሻንቆ ይህንን ትልቅ አደራ እንዳንዘነጋው ለማድረግ በዚህ መጽሐፍ ያደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው፡፡ መጽሐፉ ስለ ወንጌል ምንነት በጥልቀት የሚያስረዳና ወንጌልን እንዴት ማዳረስ እንደሚቻል የሚያሳዩ ጠቃሚ ምክሮችንና ዘዴዎችን የያዘ ስለሆነ፤ ለክርስቶስ ወንጌል ቅናት አለኝ ብሎ ለሚያምን አማኝ ሁሉ ይህ መጽሐፍ አገልግሎትን በብቃት ለመወጣት ትልቅ እገዛ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ፡፡”

ፍሬው ታምራት
ከኢትዮጵያ ቲኦሎጂ ኮሌጅ (ETC)

“በጌታ ምጽአት መዳረሻ ላይ አጉልተን ልናከናውነው የሚገባን ተግባር በዚህ መጽሐፍ ተገልጾአል፡፡ ወንድማችን በቀለ የእግዚአብሔርን ቃል፣ የራሱንና የሌሎችን ቅዱሳን ልምድ ባማከለ መልክ ይህን ጠቃሚ መጽሐፍ አበርክቶልናል፡፡ የክርስቲያን ሁሉ አብይ ተልዕኮ በዚህ ጥራዝ ተጠቁሟል፡፡ ለበረከት ይዋል፡፡”

ደረጀ አበበ
ከሕይወት መጽሔት ዝግጅት

“የመኖሬ ዓላማ ምንድነው ብለው ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ? ለጥያቄዎስ መልስ አግኝተዋል? የ‘ወንጌል ባለአደራ’ ለቤተክርስቲያን መሪዎችም ሆነ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ የመኖርን ዓላማ ያስጨብጣል፡፡ ወንድም በቀለ ሻንቆ እግዚአብሔር በአገራችንና በዓለም ዙሪያ በአስደናቂ ሁኔታ በሚሠራበት በዚህ

ዘመን የወንጌልን እሳት ለመቆስቆስና ለማነሳሳት ኃይል ያለውን መጽሐፍ አበርክቶልናል። በዘመናቸው የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገልና ጌታ ታሪክን ለመሥራት እንዲጠቀምባቸው የሚሹ ሁሉ የ'ወንጌል ባለአደራ'ን በማስተዋል እንዲያነቡትና እንዲተገብሩ እመክራለሁ።"

ጌታቸው ቤዮሮ
ከታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ኢትዮጵያ

"ይህ የ'ወንጌል ባለአደራ' የተባለ መጽሐፍ ለወንጌል የሚያነሳሳን፣ የወንጌልን አደራ ለሌሎች የምናስተላልፍበትን መንገድና ዘዴ የሚጠቁመን፣ ሌሎችንም መልካም የወንጌል ባለአደራዎች እንዲሆኑ ለማሰልጠን የምንጠቀምበት መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ጸሐፊውም ወንድማችን በቀለ የዳበረ የወንጌል አገልግሎት ልምዱን አካፍሎናል ብዬ አስባለሁ። "

ወንጌላዊ ሽፈራው ፈይሣ
ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

"በወንድም በቀለ ሻንቆ "የወንጌል ባለአደራ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ተመልክቼዋለሁ። መጽሐፉ በርዕሱ እንደተገለፀው ቤተ ክርስቲያንና አማኙ ክርስቲያን ከጌታ የተቀበለውን የወንጌል ተልዕኮ ባለአደራነት ሁልጊዜ እያሰበ በትጋት እንዲፈጽመው የሚያሳስብ ነው። የዓለምን ሕዝብ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ለመድረስ ሁላችን የወንጌል ባለአደራዎች ነን። ሰው "በጉውን ማን ያሳየኛል?" የሚል በውስጡ የነፍስ ጩኸት አለበት። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ እነዚህንና የመሳሰሉትን እውነቶች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ፣ የተለያዩ አገልጋዮችን የሕይወትና የአገልግሎት ምስክርነት በማካተትና እንዴት የወንጌልን ተልዕኮ መፈጸም እንደሚቻል የሚያስተምር ስለሆነ፣ ለግል አገልግሎት፣ ለወንጌል ስርጭት ስልጠና፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ብንጠቀምበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። "

ፈቀደ ተፈራ
ከወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ



## ማውጫ ገጽ

ምሥጋና .................... 11
መቅድም .................... 13
መግቢያ .................... 15
1. ወንጌል ምንድር ነው?.................... 17
2. ወንጌልን ለምን እንመሰክራለን? .................... 31
3. ክርስቲያንና መልዕክቱ .................... 43
4. ወንጌልና የወንጌል በረከቶች .................... 59
5. ለተለያዩ ዓይነት ሰዎች ወንጌልን መመስከር .... 69
6. የመከሩ ጥሪ .................... 81
7. መክሊት የተሰጣቸው ባሪያዎች .................... 93
8. የትውልዱ የወንጌል ባለአደራ .................... 103
9. ወንጌልና ጸሎት .................... 119
10. በራዕይ መኖር .................... 135
11. ለወንጌል ዋጋ መክፈል .................... 155
12. የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል .................... 167
ዋቢ መጻሕፍት .................... 179
ተጨማሪ መግለጫ .................... 181

# ምሥጋና

ይህ መጽሐፍ የእኔ ብቻ ሥራ ሳይሆን የብዙ ሰዎች ጥረት ውጤት ነው፡፡ የክርስቶስ ወንጌል ሕይወቴን ለውጦ ባለታሪክ ባያደርገኝ ኖሮ ዛሬ እንደዚህ ዓይነቱን መጽሐፍ ጽፌ ለማቅረብ በፍጹም አልችልም ነበር፡፡ የእኔን ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመሞቱና ሞትን ድል አድርጎ በመነሳቱ፣ ከምህረቱ የተነሳ የኃጢአቴን ዕዳ የከፈለልኝን፣ ስለ ወንጌል እንድጽፍ ያበቃኝን መድኃኒቴን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሁሉ በፊት አመሰግናለሁ፡፡

በየዕለቱ በታማኝነት እግዚአብሔርን እንዳገለግልና በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንዳድግ፣ እንዲሁም ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በማበረታታት በሕይወቴ ከፍተኛ በረከት የሆነችኝን ውድ ባለቤቴን ወ/ሮ ሸዋዬ ስዩምን፤ በአገልግሎትና በሥራ ብዛት ደክሞኝ ወደ ቤት ስገባ ወዲያው በእቅፌ ውስጥ በመግባት ውሉአቸውን እያጫወቱኝ ድካሜን የሚያስረሱኝን ልጆቼን ናታን (ናቲን)፣ ኤሊም (ሃኒንና) ፊሊፕ (ቤቢን) አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ጌታ ኢየሱስን ካመንኩበት ከአምስት ዓመት ዕድሜዬ ጀምረው እግዚአብሔርን በመፍራት ያሳደጉኝንና እግዚአብሔር ሕይወቴን እንዲባርክ ቀንና ሌሊት በትጋት የጸለዩልኝን አባቴንና እናቴን አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ይህን መጽሐፍ ከመታተሙ በፊት ረቂቅ ጽሑፉን አንብበው ጠቃሚ አስተያየቶችን የሰጡኝን አቶ በቀለ ወ/ኪዳንን፣ አቶ ጥላሁን ኃይሌን፣ ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁንን፣ ወንጌላዊ ሽፈራው ፈይሣን፣ አቶ እንዳለ ገ/መስቀልን፣ አቶ ሰለሞን ሉሉን፣ አቶ ደረጀ አበበን፣ አቶ ኩርሲ ሽፈኖን፣ መጋቢ ስለሺ ከበደን፣ አቶ ፍሬው ታምራትን፣ አቶ አበበ ታፈሰን (ከአሜሪካን)፣ አቶ ሳሙኤል ኃይሉን፣ ዶ/ር ብርሃኑ ሃብቴን፣ አቶ ጌታቸው ቤዮሮንና አቶ ፈቀደ ተፈራን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

በተጨማሪም ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ እግዚአብሔር ብርታትን እንዲሰጠኝ እንዲሁም መጽሐፉ ከታተመ በኋላ በመጽሐፉ ውስጥ ያለው መልዕክት የብዙ ሰዎችን ሕይወት እንዲለውጥ በጸሎት የረዱኝን ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁንና የክርስቲያን ሠራተኞች ህብረት የሃያ አራት ሰዓት የጸሎት አገልግሎት የሚያገለግሉ ወንድሞችና እህቶች እግዚአብሔር እንዲባርካቸው እመኛለሁ፡፡ ከጊዜ ማነስ የተነሳ የሚረሱ ሀሳቦችን በተለያዩ ጊዜያት በመጽሐፉ ገጾች ስጨምር፣ የተደጋገሙ ሀሳቦችን ስቀንስ፣ አማርኛዩን እንደገና ሳስተካክል፣ ወዘተ በዚህ ሁሉ ሳትሰለች ጽሑፉን በኮምፒውተር የሠራችልኝን ፀሐፊዬን ወ/ሮ ገነት ተስፋዬን እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

የመጽሐፉን የሽፋን ስዕል በብዙ ጥንቃቄ የሰራልኝን ሰዓሊ ልዑል ገብርኤልን በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ወንጌል በዚህች ምድር እንዲሮጥና ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲጨመሩ በቀደሙት ትውልዶችና በዚህም ትውልድ የወንጌልን አደራ በታማኝነት ለተወጡና እየተወጡ ላሉ የወንጌል አገልጋዮች ሁሉ በጌታ ስም ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

እኛ በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ያለን አገልጋዮች ወንጌልን ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማድረስ ባለን ሩጫ ሁሉ ለወንጌል ጥሪ ታማኞች በመሆን በጸሎት፣ ገንዘባቸውን በመስጠትና በሚያስፈልገው ሁሉ አብረውን ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡትን ወንድሞችና እህቶች፣ አብያተ ክርስቲያናትንና መንፈሳዊ ድርጅቶችን በሙሉ እጅግ አድርጌ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ለወንጌል አገልግሎት ራሳቸውን ሰጥተው ማንኛውንም ዋጋ በመክፈል በየገጠሩና በየከተማው ሁሉ፣ ከዚህ ቀደምና በዚህም ዘመን ወንጌልን እያሠራጩ በታማኝነት ያገለገሉና የሚያገለግሉ የታላቁ ተልዕኮ አገልጋዮችን በሙሉ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም መጽሐፉን ማተሚያ ቤት ገብቶ እስከሚወጣ ድረስ ህትመቱን በመከታተልና ጥራቱን በመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉትን የንግድ ማተሚያ ድርጅት ባልደረባና የሥነ ጽሑፍ ጓደኛዬ የሆነውን አቶ ምናሴ ጌታቸውን እንዲሁም የታላቁ ተልዕኮ አገልጋይ የሆነውን አቶ ሰለሞን አበበን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

በቀለ ሻንቆ
ሚያዚያ 1991 ዓ.ም.





# መቅድም

ለራበው ሰው የእንጀራ መገኘት እንጂ የወጡ ጣዕም ጉዳይ እምብዛም አያስጨንቀውም፡፡ እኔም ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ለሆሄያትና ለሰዋሰው ሕግ፣ ለተዋጣለት የዐረፍተ ነገር አሰካክ ብዙ አልተጨነቅኩበትም፡፡ የአጻጻፍን ሥርዓት መከተሉ እጅግ አስፈላጊ ቢሆንም የእኔ የመጀመሪያው ዓላማዬ ወጡን በማጣፈጡ ላይ ሳይሆን ለራበው እንጀራን በመስጠቱ ላይ ነው፡፡ አንባቢው በአንድ አንቀጽ ውስጥ እንኳን ሳይቀር ሆሄያት ተቀያይረው (ለምሳሌ "ሀ"ና "ሐ"፣ "ስ"ና "ሥ"፣ ወዘተ) ሊያገኝ ይችላል፣ የቋንቋ ችግር የሌለበት ወይም የሰዋሰውን ሕግ ጠንቅቆ የሚያውቅና የሚያከብር አንባቢ ከሆነ ደግሞ የእኔ ዓይነቱ የተሰባበረ አጻጻፍ ሊያናድደው ይችላል፡፡ ለእንደዚህ ዓይነቱ አንባቢ አስቀድሜ ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ከልቤ የሚወጣው መልዕክቱ በደንብ እስከገባው ድረስ የአጻጻፍ ሥርዓቱ እንኳን ትክክል ባይሆን አንባቢው ብዙ እንደማይጎዳ አስባለሁ፡፡

ዐረፍተ ነገሮችን በማንዛዛት የመልዕክቱን ሀሳብ ሊጎዳ ስለሚችል እንዲሁም አንባቢን ስለሚያሰለች የአንስታይ ጾታን አልተጠቀምኩም፡፡ ይህንንም በማድረጌ የሚያዝኑ እህቶቼ ካሉ ይቅርታ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አልልም፡፡ ምናልባትም "አንተ"፣ "አንቺ" እያልን እንዳንቸገር እንደ እንግሊዝኛው ቃል የወል መጠሪያ የምናገኝበትና እንደ እኔ ወንዱንም ሴቱንም "አንተ" በማለታችን ይቅርታ የማንጠይቅበት ዘመንስ ይመጣ እንደሆነ ማን ያውቃል?

የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶቻችን አሁንም ገና መስተካከል የሚገባቸው የትርጉም ችግሮች እንዳሉባቸው ለአንባቢ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ሦስት ሲሆኑ እነርሱም በ1954 ዓ.ም. የታተመውና በዘልማድ የ"ድሮ" ብለን የምንጠራው፣ በ1980 ዓ.ም. የታተመውና

"አዲሱ ትርጉም" ብለን የምንጠራው፣ እንዲሁም እ.አ.አ. በ1985 ዓ.ም. የታተመው ሕያው ቃል የአማርኛ አዲስ ኪዳን ናቸው። ከሦስቱም ትርጉሞች ውስጥ የጥቅሱን ትክክለኛ ሀሳብ ወይም ከሌሎቹ ይልቅ ወደ ትክክለኛው ሀሳብ የቀረበውን ትርጉም በመምረጥ ተጠቅሜአለሁ።

አዲሱን ትርጉም ወይም ሕያው ቃልን ያላነበቡና የድሮውን ትርጉም ብቻ የሚወዱ ሰዎች ከአዳዲሶቹ ትርጉሞች የተወሰዱ ጥቅሶች ሲያጋጥሙአቸው የእኔ ጥቅስ መስሎአቸው እንዳይደነግጡ ጥቅሱ ከየትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ንደተወሰደ በጥቅሱ አጠገብ ተገልጿል። ለምሳሌ በ1980 ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ጥቅስ ከሆነ (ዮሐ. 3:16፣ አዲሱ ትርጉም) ተብሎ ተቀምጧል። የጥቅሱን ሀሳብ የበለጠ ለማብራራት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘሁበት ቦታ የራሴን ተተኪ ወይም ገላጭ ቃል በቅንፍ ውስጥ ለይቼ አስቀምጫለሁ።

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ለምዕመኑ የወንጌል ባለአደራነቱን ማሳሰብ ቢሆንም በአገልግሎት ልምድ እንዳየሁት የወንጌል ስርጭትና የደቀመዝሙር ሥልጠና ለመካፈል ከሚሰበሰቡ ሰዎች መካከል እንኳን ክርስቶስን የሕይወታቸው ጌታና አዳኝ አድርገው ስለመቀበላቸው እርግጠኛ ያልሆኑ አገልጋዮችና ምዕመናን ያጋጥማሉ። ስለዚህም እንደእነዚህ ያሉ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሌሎች ለማድረስ ከመውጣታቸው በፊት ክርስቶስ በሕይወታቸው ስለመኖሩና የዘላለምን ሕይወት ስለ ማግኘታቸው እርግጠኞች መሆን ስለሚያስፈልጋቸው በግላቸው ክርስቶስን እንዴት ሊቀበሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ በጥቂትና አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ቀርቦአል።

በተጨማሪም የሕይወትን መንገድ የሚፈልጉና እውነትን የተጠሙ ሁሉ እንደዚህ ዓይነቱን መጽሐፍ ሊያነቡት ስለሚችሉ በውስጡ ለእነርሱም የሚሆን መልዕክት ማቅረቡ አስፈላጊ ስለሆነ ከዋና ተደራሲው ፍላጎት ወጣ ለማለት ችያለሁ። ስለዚህም አንባቢው በመጽሐፉ ውስጥ ክርስቶስን እንዲቀበል የሚጋብዝ ዓይነት ጽሑፍ ወዳለበት ሥፍራ(ዎች) ሲደርስ "እንደዚህ ዓይነቱን እዚህ ውስጥ ለምን አስገባ?" ብሎ ከሚቆጣኝ ይልቅ በትዕግስት እያነበበ እንዲያልፍና ይህንንም ክርስቶስን የማያውቁትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንዴት ሊጠቀም እንደሚችል እንዲያስተውል አደራ እላለሁ።





# መግቢያ

የልጅነት ጊዜ ትዝታ ብዙ አለኝ። የወንጌል ቅናት ዕረፍት የነሳቸው አባቶች "የምሥራች" እያሉ ሸዋን፣ ሲዳሞን፣ ከፋን፣ ጋሞጎፋን፣ ባሌን፣ ወለጋንና የመሳሰሉትን ክፍላተ ሃገሮች፤ በእግርና በበቅሎ፣ ያለ ገንዘብና ያለ ስንቅ፣ ተራራ ወጥተው ቁልቁለት ወርደው፣ ወንዝ ተሻግረው ሜዳን አቋርጠው የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል እንዴት እንደሰበኩ ትዝ ይለኛል። እኔም ብዙ ርቀት መጓዝ የልጅነት ዕድሜዬ ባይፈቅድልኝም የቅርብ አካባቢዎችን ከአባቴ ጋር እየዞርን ወንጌልን ስንሰብክ፣ በክርስቶስ ስም አጋንንት ስናስወጣና ለበሽተኞች ጸልየን ሲፈወሱ፣ በአካባቢያችን ከነበረው ከሰይጣን አሠራር ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል የበላይነቱን ሲቀዳጅ ማየቴ ዛሬ ያለሁበትን እንድጠይቅ ያደርገኛል። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለትውልዱ የወንንጌል ባለአደራዎች ሁሉ ብርቱ ጥያቄን ያስነሳል ብዬ አምናለሁ።

ያ በወንጌል እሳት የተቀጣጠለው የአባቶቻችን ትውልድ ገና ሳያልፍ በእኛ በልጆቻቸው ትውልድ የወንጌሉ ወኔና ቅናት፣ ጫካውን አቋርጦ በረሃውን ተጉዞ የመሄዱ የወንጌል አርበኝነት ወዴት ደረሰ? አሁንም በሕይወት ካሉ የወንጌል አባቶቻችን እግር ሥር ተቀምጠን ለወንጌል ሲሉ ከክርስቶስ ጋር ያሳለፉበትን፣ ከሰይጣን ጋራ ግብ ግብ ገጥመው የእግዚአብሔር ብርሃን በጨለማ እንዲበራ ያደረጉበትን የወንጌል ገድል ሲያወጉን ብንሰማቸው ምን ይሰማን ይሆን? ብዬ አስባለሁ።

እነርሱ በትውልዳቸው በመልካም ሮጠው ያን ገድል ለእኛ አስተላለፉት፣ እኛስ ለሚቀጥለው ትውልድ ምን እናስተላልፍ ይሆን? ብዬ እሰጋለሁ። መከፋፈልን፣ መለያየትን፣ ቅናትን፣ እኔነትን ወይስ ይህንን ሁሉ በደሙ አፍርሶ አንድ ያደረገንንና ሕይወታችንን የለወጠውን የክርስቶስን ወንጌል ለተከታዩ ትውልድ እናስተላልፍ ይሆን?

ይህንንም መጽሐፍ እንድጽፍ ያደፋፈረኝ ዋናው ጉዳይ ይህ ነው፡፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ካስታረቀበት ጊዜ ጀምሮ፣ ከዚያም በሐዋርያት፣ እንዲሁም በየትውልዱ የወንጌል ባለአደራዎች ሆነው በታማኝነት በመኖር ለእኛ ያስተላለፉትን ወንጌል እኛም ታማኞች ሆነን ለሚቀጥለው ትውልድ እንድናስተላልፍ በጥቂቱም ቢሆን ይረዳናል ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡ እግዚአብሔር በልቤ ያስቀመጠውን ሸክም በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያንና በእያንዳንዱ ጉባዔ ተገኝቼ ለጥቂት ጊዜ እንኳን ብናገርና ሸክሜን ባስተላልፍ እጅግ ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የአገልግሎት ኃላፊነቴን አስፍቶልኝ በቅርቡ ከቤተሰቤ ጋር ከኢትዮጵያ ወደ ሌላ አገር ስለምሄድ እግዚአብሔር በውስጤ ያስቀመጠውን የወንጌል ጉዳይ በተሰባበረ ቋንቋና አጻጻፍ እንኳን ቢሆን በወረቀት ላይ አስፍሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የቤተክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናን እንዲሁም ክርስቶስን በግላቸው ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ ባስተላልፍ በመጠኑም ቢሆን እፎይታን አገኛለሁ ብዬ ስላመንኩ እነሆ ይህን መጽሐፍ በጌታዬ ብርታት ጻፍኩኝ፡፡ ይህንንም መጽሐፍ ለሚያነብ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አዲስ የወንጌል ራዕይን፣ የልብ መነሳሳትንና ለእግዚአብሔር ሀሳብ መታዘዝን እንዲሰጥ እየጸለይኩ እነሆ ጽሑፉን በደስታ አበረክታለሁ፡፡

በቀለ ሻንቆ





# ምዕራፍ አንድ

## ወንጌል ምንድነው ?

ወንጌል የሚለው ቃል በግሪክ እቫንጀሊዮን በመባል የሚታወቅ ሲሆን ትርጉሙም መልካም ዜና፣ የምስራች ቃል፣ የሚያስደስትና የሚያረካ ዜና ማለት ነው፡፡ ድልን የሚያውጅ፣ ለልብ ደስታን የሚሰጥ መልዕክት ማለት ነው፡፡ ወንጌል የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከ75 ጊዜ በላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ወንጌል ማለት በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ የነበረውን ሰው እግዚአብሔር የራሱን መፍትሄ መንገድ አዘጋጅቶ ወደራሱ ህብረት ለመመለስ ለአዳምና ሔዋን፣ ከዚያም ለአብርሃም፣ እንዲሁም ለእስራኤላውያን የገባውን ቃል ኪዳን በመሲሁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሰው ልጆች ሁሉ በመፈጸም የዘላለምን ሕይወት መንገድ ለሰዎች ሁሉ የከፈተበት የምስራች የሚያበስር መልዕክት ነው፡

ወንጌል በአዲስ ኪዳን ብቻ የተገለጠ መልዕክት ሳይሆን የብሉይ ኪዳንም ቁልፍ መልዕክት ነው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ማንነት ተጠራጥሮ መልዕክተኞችን ወደ ኢየሱስ በላከበት ጊዜ ኢየሱስ ስለራሱና ስለ መልዕክቱ የገለጠው ይህን እውነት ነበር፡፡ ይህም መልዕክት የብሉይ ኪዳን መካከለኛ መልዕክት ወንጌል እንደነበረ /ማቴ. 11፡2-5/ የሚገልጽ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳያስም በትንቢቱ የተናገረው ስለዚህ ወንጌል እንደነበረ ኢየሱስ ራሱ በምድር ላይ አገልግሎቱን በጀመረበት ጊዜ ሲናገር እንደዚህ አለ፡-

“የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ መልካም ዜናን (ወንጌልን) ለድሆች እንዳበስር ሾሞኛል፤ ለታሰሩት መፈታትን፣ ለታወሩት ማየትን እንዳውጅና የተጨቆኑትንም ነጻ እንዳወጣ ልኮኛል፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ህዝቡን የሚያድንበትን የጸጋ ዓመት እንዳስታውቅ ልኮኛል፡፡” (ሉቃ 4፡18-19፣ አዲሱ ትርጉም)፡፡ ይህ የተጠቀሰው ክፍል ስለ ወንጌል ምንነት ብዙ ትርጉም ይሰጠናል፡፡

## 1/ ወንጌል ለድሆች የምስራች ነው

ድሆች ማለት በሥጋዊና በምድራዊ ነገር ድሃ የሆኑትን ብቻ አይደለም፡፡ ይህንን ቃል በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ብዙዎች በማጣመም ስለተረጎሙት ወንጌል የሚያስፈልገው ምንም ነገር ለሌላቸው ፣ ለተናቁ፣ ለበሽተኞች፣ ረዳት ለሌላቸው፣ ሀብት ላልበዛላቸው ሰዎች ስለሆነ ለእኛ አያስፈልገንም በማለት እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን የደህንነት መንገድ ችላ ይላሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ድሆች ሲል ግን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደሃ የሆኑ፣ በውስጣቸው የነፍስ ጩኸት ያለባቸው፣ እውነትን ለማወቅና ለመከተል የሚጠሙ፣ በነፍሳቸው የሚቅበዘበዙና የሚንከራተቱ፣ የሕይወት ትርጉም የጠፋባቸው ማለት ነው፡፡ የወንጌሉ የምስራች የሚያስፈልገው ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች ነው፡፡ እነዚህም ሰዎች በመንፈስ ድሆች ናቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስም ስለ እነዚህ ሰዎች ሲናገር "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፡፡ መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና" ይላል /ማቴ. 5፡3/፡፡ በመንፈሳቸው ድሃ የሆኑ ሰዎች የምስራቹን የተጠሙ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር መንግስት ቅርብ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡

## 2/ ወንጌል ለታሰሩት መፈታትን ይሰጣል

የታሰሩት ስንል በሰይጣን መንግስት ውስጥ የታሰሩት ማለታችን ነው፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያለው ሁለት መንግስት ብቻ ነው፣ የእግዚአብሔር መንግስትና የሰይጣን መንግስት፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት ማለት የነፃነት፣ የሰላም፣ የእርካታ፣ የደስታ፣ የዘላለም ሕይወት፣ የቅድስና፣ የጽድቅና የእውነት መንግስት ሲሆን ፤ የሰይጣን መንግስት ደግሞ በተቃራኒው የመታሰር፣ ነጻነትና ሰላም የሌለበት፣ ሞት የነገሠበት፣ የጨለማ፣ የመቅበዝበዝ፣ እረፍት የሌለበት፣ የመጨነቅ፣ የርኩሰትና የውሸት መንግስት ነው፡፡

ወደ እግዚአብሔር መንግስት ያልገቡቱ ሁሉ በሰይጣን መንግስት ውስጥ የታሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የምስራቹን ወንጌል ሰምተው ከተቀበሉ ከሰይጣን መንግስት መፈታትን ያገኛሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እውነት ሲያረጋግጥ፡- "ምክንያቱም እርሱ (እግዚአብሔር) ከጨለማ ኃይል አድኖ ወደ ተወደደው ልጁ (ክርስቶስ) መንግስት እንድንገባ አድርጎናል፡፡ በእርሱም (በክርስቶስ) ተዋጅተን የኃጢአታችንን ይቅርታ አግኝተናል፡፡" ይላል (ቆላ. 1፡13-14፣ አዲሱ ትርጉም)፡፡





ወንጌል ከሰይጣን እስራት እንዴት እንደሚፈታ እኔ ምስክር ነኝ፡፡ በወንጌል የሚገኘውን መፈታት ስላገኘሁ ነው ዛሬ ስለ ወንጌል መጻፍ የቻልኩት፡፡ የአምስት ዓመት ልጅ የነበርኩበት ጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ አባቴ ባለውቃቢን የሚያገለግል ሰው ስለነበረ ቤተሰባችን በሙሉ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ይኖር ነበር፡፡ ሰይጣን በቤታችን የፈለገውን የማዘዝ፣ የፈለገውን የመግደል፣ የፈለገውን በሕይወት የማኖር ሙሉ ስልጣን ነበረው፡፡ "የምፈልገው ዓይነት መሥዋዕት አልቀረበልኝም ስለዚህም ዛሬ በሬህን፣ በቅሎህን፣ ልጅህን ለመግደል መጥቻለሁ" በማለት ሰይጣን በቤታችን የፈለገውን ያደርግ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት አባቴ ከሁለት ሚስቶች (አንዷ የእኔ እናት ነች) የወለዳቸው ሰባት ልጆች ገና በልጅነታቸው ሞተዋል፡፡ ህዝብ ተሰብስቦ፣ በሬ ታርዶ፣ የተመረጠው ሁሉ ቀርቦ ለሰይጣን ክብር ይጨፈርለት ነበር፡፡ ሰይጣን ከአባቴ የሚፈልገው ሥርዓት ነው ተብሎ አባቴ ቀንና ማታ ሳያቋርጥ ነጭ አረቄ መጠጣትና ትንባሆ ማጨስ ግዴታው ነበር፡፡

የእናቴ ኃላፊነት ደግሞ ቀንና ሌሊት አባቴ የሚጠጣበትን መለኪያ (ብርጭቆ) በአረቄ መሙላትና አዲስ ትንባሆ መቀየር ስለነበር እናቴ እንደ ሰው ሌሊት እንቅልፍ መተኛት አትችልም ነበር፡፡ በቤታችን የሚወለድ ሌላ ልጅ እንዳይሞት ከፈለገ አባቴ እኔን ዕድሜዬን በሙሉ የሰይጣን አገልጋይ እንድሆን ለሰይጣን ማስረከብ እንዳለበት ስለተነገረው በአምስት ዓመት ዕድሜዬ የሰይጣን አገልጋይ ሆኜ እንዳድግ ተፈርዶብኝ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ቤታችን ሞት የነገሠበት፣ ጨለማ የሰፈነበት፣ በሰይጣን ገመድ የተጠፈርንበት፣ ለነገ የመኖር ተስፋ የሌለበት ነበር፡፡ በዚህ እስራት ውስጥ ስንኖር ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት ገበሬዎች በምሽት ወደ ቤታችን መጥተው "የምሥራች! ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ከእስራት ይፈታል" በማለት የወንጌልን የምሥራች የገለጹልን፡፡ በእርግጥም ከእስራት የሚፈታ የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚያን ምሽት ወደ ቤታችን ገባ! እስራታችን በሙሉ ተበጣጠሰ! ጨለማችንም በራ፡፡ በዚህ ምክንያት እኔም ዛሬ ሰው ሆኛለሁ፡፡ ክርስቶስ እኔንም ባለታሪክ አድርጎኛል፡፡ ከእስራቴ ፈቶ የራሱ አገልጋይ አድርጎኛል፡፡ ወንጌል ዛሬም በሰይጣን ለታሰሩት ሁሉ መፈታትን ይሰጣል፡፡

## 3/ ወንጌል ለታወሩት ማየትን ይሰጣል

ይህም ማለት በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ላሉ፣ የት እንዳሉ ላላወቁና ወዴት እንደሚሄዱ ግራ ለገባቸው ሁሉ ወንጌል መንፈሳዊ ዓይናቸውን ይከፍትላቸዋል፣ ጨለማቸውን ያበራላቸዋል፣ መነሻና መድረሻቸውን በግልጥ ያሳያቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰው ሕይወት ሲገባ መንፈሳዊ ዓይንን ይከፍታል። ከዚያ በፊት ለማየት ያልቻልነውን እውነት እናያለን፣ ያልተረዳነው ይገለጥልናል።

እውነትን ሰምተው፣ ብዙም ታሪክ አይተው ነገር ግን ከኢየሱስ ሞት በኋላ ተስፋ ቆርጠውና ፈርተው ለነበሩ ደቀመዛሙርት፣ ኢየሱስ አእምሮአቸውን ከከፈተላቸው በኋላ ነበር እውነቱ የተገለጠላቸው። ከዚያም በኋላ ለእውነት ሕይወታቸውን አስገዝተዋል። /ሉቃ. 24:45/ ወንጌል ለታወሩት ማየትን የሚሰጥ ታላቅ የምሥራች ነው። በወንጌል ኃይል ሽባዎች ይዘላሉ፣ ዲዳዎች ይናገራሉ፣ ዕውራን ያያሉ፣ ድውያን ይፈወሳሉ፣ ሰዎች ከአጋንንት ነጻ ይወጣሉ። (ማቴ. 9:18-38፣ ዮሐ. 9 ተመልከት።)

## 4/ ወንጌል የተጨቆኑትን ነጻ ያወጣል።

ሰውን ጭቆና ውስጥ የሚያስገባው ሰው ሳይሆን ሰይጣን ነው። ሰው በሌላ ሰው እየተጨቆነና እየተረገጠ እያለም የልብ ሰላም፣ ደስታና እርካታ ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ሰው በሰይጣን ከተጨቆነ ብዙ ሀብት፣ ንብረት፣ እውቀትና ችሎታ ቢኖረውም ሰላም አይኖረውም፣ ዕረፍትና እርካታ አይኖረውም፣ በሚመች አልጋ ላይ ተኝቶ እንኳ እንቅልፍ አይወስደውም። ወንጌል የመጣልን እውነተኛ ነጻነትን እንድናገኝ ነው። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስ ዋና ተልዕኮው ነበር። ሰይጣን የረገጣቸውን ነጻ ማውጣት።

ክርስቶስ የሰይጣንን ኃይል ከረገጠ በኋላ ለተረገጡት ሁሉ ድልን አወጀላቸው። "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።" /ቆላ. 2:14-15/። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባደረገው ተጋድሎውና በሞቱና ትንሳኤው የሰይጣንን ሥልጣን፣ ኃይልና አሰራሩን በሙሉ ድል በማድረጉ ምክንያት በሰይጣን የተጨቆኑትን ነጻ ለማውጣት የሚችል ኢየሱስ እርሱ ብቻ መሆኑን አስመስክሯል።





## 5/ ወንጌል የደህንነት መልዕክት ነው

እግዚአብሔር ህዝቡን የጎበኘበት፣ የህዝቡን ጭቆናና መረገጥ አይቶ የድልን የምሥራች ያወጀበት፣ የሰው ልጆች ከዘላለም ሞት ተሻግረው ወደ ዘላለም ሕይወት መግባት የሚችሉበት መልዕክት ወንጌል ነው። የወንጌልን መልዕክት ሰምቶ መቀበል ማለት በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስንና ምህረትን ማግኘት ማለት ነው። ወንጌል የአዲስ ኪዳን መካከለኛ መልዕክት ብቻ ሳይሆን የብሉይ ኪዳንም መካከለኛ መልዕክት ነበር።

## ወንጌል በብሉይ ኪዳን

የሰው ልጅ በኃጢአት በወደቀበት ጊዜ እግዚአብሔር በሰውና በሰይጣን መካከል ጠላትነትን ሲያደርግ፣ ከሴቲቱ የሚወለድ (ማለትም መሲሁ ኢየሱስ ክርስቶስ) የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥና ሰይጣንን ድል እንደሚያደርግ፣ የሰው ልጅም በኃጢአት ምክንያት ያጣውን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ህብረትና ክብር መልሶ እንደሚያገኘው ተስፋ ከሰጠበት (ዘፍ. 3:15) ጊዜ አንስቶ ወንጌል የብሉይ ኪዳን ዋና መልዕክት ነበር። የብሉይ ኪዳን ትምህርቶች ሁሉ ዋናው ርዕሳቸው አንድ ብቻ ሆኖ፣ ይኸውም የሰው ኃጢአትና የእግዚአብሔር ይቅርታ ሲሆን ሁሉም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሰው ልጆች ሁሉ ሊመጣ ያለውን ታላቁን የደህንነት በረከት ይገልጹ ነበር። በብሉይ ኪዳን የነበረውን የወንጌልን ሥፍራ በጥቂቱ ለመግለጽ ከብሉይ ኪዳን ሐዋሪያው ጳውሎስ የጠቀሰውን የአብርሃምን ምሳሌነት ብቻ መጥቀሱ በቂ ይሆናል።

## አብርሃም የወንጌል ሰው

ወንጌል ማለት ሰው ከእግዚአብሔር ዘላለማዊና መለኮታዊ ሀሳብ ጋር እንዲስማማ ከእግዚአብሔር የሚተላለፍለት የጥሪ መልዕ ክት ማለት ነው። አብርሃም በኖረበት ዘመን የነበሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሀሳብ እጅግ ርቀው በራሳቸውና በመሰላቸው መንገድ በሚሄዱበት ጊዜ ነበር እግዚአብሔር አብርሃምን "ከአገርህና ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ" /ዘፍ. 12:1/ ብሎት የተናገረው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የነበረው ሀሳብ የተለየና መልካም ሀሳብ ነበር። አብርሃምም ለእግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ ራሱን በማስገዛት የሚሄድበትን አገር

ገና ባያውቀውም ለእግዚአብሔር ታዞና የተወለደበትን መንደር ለቆ ወጣ፣ በእምነትም እግዚአብሔር በሰጠው ምድር ተቀመጠ፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለአብርሃም መታዘዝና በመታዘዙም ስላገኘው በረከት "እንግዲህ የሚያምኑ ሁሉ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ እወቁ፡፡ እግዚአብሔር አረማውያንን በእምነት እንደሚያጸድቅ መጽሐፍ አስቀድሞ አይቶ 'ሕዝቦች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ' በማለት አስቀድሞ ለአብርሃም የምስራቹን ቃል አብስሮአል፡፡ ስለዚህ የሚያምኑ ሁሉ ከአመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ" ብሎ ተናገረ፡፡ /ገላ. 3፡8-9፣ አዲሱ ትርጉም/

እንግዲህ ለአብርሃም የተሰበከለት የወንጌል ቃል ይህ ሲሆን አብርሃምም የተሰበከለትን የወንጌል ቃል በእምነት ተቀበለ፡፡ በዚህም ምክንያት አብርሃም ለራሱና ለብዙዎች የበረከት ምንጭ ሆነ፡፡ ለአብርሃም የተበሰረለት የምስራች ቃል ጽድቅ የሚገኘው በእምነት እንደሆነና እግዚአብሔርን መታዘዝ የሚያመጣው በረከት ታላቅ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን እንደ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት የሚቀበሉ ሁሉ እንደሚጸድቁ ያሳያል፡፡ የሚስቱ የሣራ ማህፀን እንደ ምውት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር "ልጅን እሰጥሃለሁ"፣ "የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተና በዘርህ ይባረካሉ" በማለት ለአሕዛብ ሁሉ በረከት የሚሆን መሲሁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣ የሚገልጽ የምስራች ቃል ባበሰረለት ጊዜ አብርሃም ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት ተቀበለ፡፡ ይህንንም ቃል ባመነ ጊዜ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት፡፡

ይህም ጽድቅ እግዚአብሔርን ላመነው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ዛሬም እግዚአብሔር በወንጌሉ መልዕክት የሚያበስርላቸውን የምሥራች ቃል ሰምተው የሚያምኑ ሁሉ በእምነታቸው ምክንያት እንደሚጸድቁ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ጽድቅ የሚገኘው በሥራ ሳይሆን በእምነት ነው፡፡ "እንግዲህ የቀድሞው አባታችን አብርሃም አገኘ የምንለው ምንድን ነው? አብርሃም የጸደቀው በሥራ ቢሆን ኖሮ የሚመካበት ነገር ባገኘ ነበር፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት መመካት አይችልም፡፡ ምክንያቱም 'አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት' ተብሎ ተጽፎአል፡፡ የሚሠራ ሰው የሚያገኘው ደመወዝ፣ ተገቢ የጉልበቱን ዋጋ ነው እንጂ ስጦታ አይደለም፡፡ ሰው መልካም ሥራ ባይኖረው እንኳ ኃጢአተኞችን በሚያጸድቅ አምላክ ካመነ፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል፡፡" /ሮሜ. 4፡1-5፣ አዲሱ ትርጉም፡፡/



የወንጌል ባለአደራ

በእምነት ብቻ መጽደቅ የተሰጠው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የተናገረውን በእምነት ለሚቀበሉ ሁሉ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲያረጋግጥ "ነገር ግን 'ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት' የሚለው ቃል የተጻፈው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን፣ ለእኛም ጭምር ነው፤ ጌታችን ኢየሱስን ከሞት ባስነሣው አምላክ ለምናምን ለእኛም፣ እምነታችን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርልናልና፡፡ ይህ ጌታችን ኢየሱስም ስለ ኃጢአታችን ለሞት ተላልፎ የተሰጠውና እኛንም ለማጽደቅ ከሞት የተነሣው ነው፡፡" ይላል /ሮሜ. 4፡23-25፣ አዲሱ ትርጉም፡፡/

እግዚአብሔርም ለአብርሃም በመታዘዙና በእምነቱ ምክንያት አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ የምስራቹን እንዳበሰረለት ሁሉ፣ እግዚአብሔር አሁንም በወንጌሉ የምስራች ለሰዎች ሁሉ ዘላለማዊ በረከትን አዘጋጅቷል፡፡ ይህን መልዕክት በእምነት የሚቀበሉ ሁሉ ከአብርሃም ጋር በእግዚአብሔር መንግስት ይባረካሉ፡፡ መልዕክቱን አንታዘዝም የሚሉ ሁሉ ደግሞ የዘላለም ቅጣት እንደሚጠብቃቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይነግረናል፡፡ /ማር. 16፡15-16 ፣ ዮሐ. 5፡24 ፣ ዮሐ. 3፡16-18/

## 6/ ወንጌል የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው

የክርስቶስ ወንጌል ወደ ሰዎች የሚመጣው በእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ነው፡፡ /1ተሰ. 1፡5/ ወንጌል የሰውን ሕይወት፣ ቤተሰብን፣ አገርንና ዓለምን የመለወጥ ታላቅ ኃይል አለው፡፡ ምክንያቱም ወንጌል የእግዚአብሔር የማዳን፣ የመለወጥና የመስራት ኃይል የተገለጠበት መንገድ ነውና፡፡

የወንጌልን የማዳን ኃይል በራሱ ሕይወትና እርሱ ወንጌልን በሰበከላቸው ሰዎች ሕይወት በሚገባ የተረዳው ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ እንዲህ ብሎ ጽፏል፡፡ "እኔ በወንጌል ቃል አላፍርም፣ ምክንያቱም የወንጌል ቃል በመጀመሪያ አይሁዳውያንን፣ ቀጥሎም አረማውያንን፣ የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ ማዳን የሚችል የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ ይህም የወንጌል ቃል እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸድቀው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት መሆኑን ይገልጣል፤ ምክንያቱም 'ጻድቅ ሰው በእምነት ሕይወትን ያገኛል' ተብሎ ተጽፎአል፡፡" /ሮሜ. 1፡16-17፣ አዲሱ ትርጉም፡፡/

ወንጌል ምንም እንኳን የመስራት፣ የመለወጥና የማዳን ኃይል ያለው ቢሆንም የሚያድነውና የሚለውጠው የምስራቹን ቃል ሰምተው የሚታዘዙትን ሰዎች ብቻ ነው። ወንጌል "ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው።" ሰምተው በእምነት ለማይቀበሉት ግን ምንም አይጠቅማቸውም። /ዕብ. 4፡2/ ይህንን ወንጌል በእምነት በመታዘዝ ተቀብለው ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጠላቸው ሁሉ ደግሞ ይህን ታላቅ የምስራች ላልሰሙት የማድረስ ኃላፊነት አለባቸው።

ወንጌሉን ተቀብለው ክርስቶስን ለመከተል የወሰኑ ሁሉ ክርስቲያን የሚል ስም ያገኛሉ። ክርስቲያን ማለት ክርስቶስን የሚከተል፣ ክርስቶስን የሚመስልና የክርስቶስን አደራ ተቀብሎ የሚፈጽም ማለት ነው። ክርስቲያን ከሆንን በኋላ ክርስቲያን የሚለውን ስም ተሸክመን መኖር ሳይሆን ክርስቲያን ሆነን እንድንገኝ እግዚአብሔር ይፈልጋል። በእጭሩ ክርስቲያን ዓላማ ያለውና ለዓላማው ደግሞ ራሱን ሰጥቶ የሚኖር መሆኑን እንድንገነዘብ ያስፈልጋል።

## 7/ ወንጌል የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ነው

ወንጌል እግዚአብሔር አስደናቂ የሆነ ፍቅሩን ለሰው ልጆች የገለጠበት መንገድ ነው። ይህንንም ፍቅሩን የገለጠው አንድያ ልጁን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት አሳልፎ በመስጠቱ ነው። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ወዷልና"። /ዮሐ. 3፡16/

ይህ የወንጌል መልዕክት እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ያለውን ዓላማ በሚገባ ያሳያል። ይህንንም የተናገረው ጌታ ኢየሱስ ሲሆን ለማንና ለምን እንደተናገረ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስትን ከመጀመሪያው ቁጥር አንስተን በምናይበት ጊዜ ሃይማኖተኛና የእስራኤል መምህር ለነበረው ኒቆዲሞስ ለተባለ ሰው ነበር። ይህም ሰው እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለውን ዓላማ ጠንቅቆ ሳያውቅና ለራሱ የደህንነትን መንገድ ዳግመኛ መወለድን ሳይረዳ ሌሎችን ሲያስተምር የነበረ የኦሪት ሕግ አዋቂ ነበር።

የደህንነትን መንገድ ለራሳቸው ሳያረጋግጡ ሌሎችን ስለ ሃይማኖት የሚያስተምሩ እንደ ኒቆዲሞስ ያሉ በዓለም ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ይገኛሉ። አንተም ምናልባት ይህን መጽሐፍ





እያነበብህ ሳለ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ገና በትክክል ያላወቅህ ወይንም ደግሞ ስለ ደህንነትህ እርግጠኛ ያልሆንክ ልትሆን ትችላለህ። አሊያም እንደ ኒቆዲሞስ ያለ የሕይወትን መንገድ ያላወቀ ሌላ ሰው ትዝ ሊልህ ይችላል።

ይህ ከሆነ ይህንን መንገድ ዛሬውኑ ልታውቅ ወይም ልታሳውቅ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ወዳዘጋጀልህ የደህንነት መንገድ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ልትገባ ወይም ሌላውን ሰው ልታስገባ ትችላለህ። የእግዚአብሔርን መልዕክት ስማ፣ ታዘዘውም። የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በመታዘዝ የሕይወት መንገድ ይገኛል። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶና አምኖ እንደጸደቀ ሁሉ አንተም የእግዚአብሔርን መልዕክት አሁን ሰምተህ ብታምን ትጸድቃለህ፣ የእግዚአብሔርንም በረከት ትወርሳለህ።

ለመሆኑ ይህ የእግዚአብሔር መልዕክት ምንድር ነው? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኒቆዲሞስና ሌሎች እንደርሱ ያሉ ሃይማኖተኞች እንዲያውቁት የሚፈልገው ነገር ምንድር ነው?

## ሀ/ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ዓላማ አለው

ሰው ከሌላ ፍጥረት ሁሉ የተለየ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ከሌሎች ሁሉ ፍጥረታት ልዩ አድርጎ ፈጥሮታል። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" /ዘፍጥ. 2፡7/። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ ሲፈጥር ሕያው ነፍስ ያለው ሆኖ የተፈጠረው ሰው ብቻ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የተሰጠው ሰውም ዘላለማዊ ነው። ይህም ማለት ሌላ ፍጥረት ሁሉ ፍጻሜ ሲኖረው ሰው ግን ፍጻሜ የለውም።

ነገር ግን ሰው ምድራዊ ሕይወቱን ጨርሶ ወደ ሌላኛው ዓለም በሚሻገርበት ጊዜ ሁለት የተለያየ ዓይነት ሕይወት ይጠብቀዋል። ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም የደስታ የሰላምና የዕረፍት ሕይወት ወይም ከሰይጣን ጋር የሥቃይ የጣርና የሲያል ሕይወት።

ሰው ግን ከእነዚህ ከሁለቱ መንገዶችና መድረሻዎች ለራሱ ለመምረጥ ሙሉ መብት ተሰጥቶታል። ጥበበኞች የዘላለምን ሕይወት ሲመርጡ ሞኞች ግን የዘላለምን ሥቃይና ሞት፣

ከእግዚአብሔርም ክብር ተለይተው ከሰይጣን ጋር መኖርን ይመርጣሉ፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ሰው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኝ ነው፡፡ እርሱ ለእያንዳንዱ ሰው ያለውም ዓላማ ይኸው ነው፤ ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው፡፡ ሰው ደግሞ የዘላለምን ሕይወት ሊመርጥ የሚችለው ዛሬ ነው፡፡

ሰው ይህንን የዘላለምን ሕይወት መምረጥ የሚችለው እግዚአብሔር በላከው በልጁ በማመን ነው፡፡ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ" ስለሚል በልጁ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኛል እንጂ ከእግዚአብሔር ተለይቶ አይጠፋም፡፡ ይህንንም ያረጋገጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር በራሱ አፍ "በእርሱ የሚያምን ለዘላለም አይጠፋም" ብሎ ከተናገረ በእርሱ (በክርስቶስ) የሚያምን በእርግጥም አይጠፋም፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሚበልጥ ማረጋገጫ ከቶ ሊኖር አይችልምና፡፡

እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው የሕይወቱን ዓላማ እንዲያውቅ ይፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ይቅርና ይህ የደህንነት መንገድ መዘጋጀቱን እንኳ የማያውቅ ሁሉ "ለምን ተፈጠርኩ? ለምንስ እኖራለሁ? ከየትስ መጣሁ? ወዴትስ እሄዳለሁ?" ብሎ ራሱን እንዲጠይቅና እግዚአብሔር ለእርሱ ሕይወት ያለውን ዓላማ እንዲያውቅ ይፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር የሚያኖረን በዓላማ ነው፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው በምድር ላይ የሚኖርበትን ዘመንና ቦታ መድቦለታል፡፡ አንተ አሁን በዚህ ዘመንና በዚህ ሥፍራ የምትኖረው በአጋጣሚ አይደለም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር መድቦልህ ነው፡፡ እርሱ ያውቅሃል፤ በዚህ ዘመንና በዚህ ሥፍራ እንድትኖር ያደረገህ እግዚአብሔር ነው፡፡ ለምን ባለፈው ትውልድ አልተፈጠርክም? በዚህ ትውልድ ለመኖር እራስህ መርጠህ ወይም በራስህ ፈቃድ ወደዚህች ምድር አልመጣህም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በፈቃዱና በዓላማ በዚህ ዘመንና ትውልድ እንድትኖር አደረገህ፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሔር ለምን ፈጠረህ? በዚህ ጊዜ በምድር ላይ የምትኖረውስ ለምንድር ነው?

ሐዋሪያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እየመሰላቸው ነገር ግን የማይታወቅን አምላክ ሲያመልኩ ለኖሩ ለግሪክ ሰዎች የተናገረውን እዚህ መጥቀሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ "የአቴና ሰዎች ሆይ፤ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ





እመለከታለሁ፡፡ የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ፡- ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና፡፡ እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ፡፡ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጉድለው በሰው እጅ አይገለገልም፡፡ ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ፤ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው" /ሐዋ. 17፡22-27/፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ የግሪክ ሰዎች እግዚአብሔር ለምን እንደፈጠራቸውና የሕይወታቸው ዓላማ ምን መሆን እንዳለበት እንዲያውቁ ይናገራቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተወሰኑትን ዘመኖችና ለሚኖሩበትም ሥፍራ ዳርቻ የመደበላቸው እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ ነው፡፡ አንተም እግዚአብሔርን ትፈልገው ዘንድ መንገዱንም ታውቅ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በላከው በልጁ አምነህ የዘላለምን ሕይወት እንድትወርስና ለሌሎችም የዘላለምን የሕይወት መንገድ ታሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ይፈልግሃል፡፡

## ለ/ እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እንዲሁ ወደደ

እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ የወደደው እንዲሁ ያለ ምክንያት ነው፡፡ ሰው ግን ሰውን ሲወድ ለመውደዱ ምክንያት አለው፡፡ በዝምድና፤ በጓደኝነት፤ በመስጠትና በመቀበል ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የሰው ፍቅር ይለካል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ምንም መለኪያ የለውም፤ ምንም ምክንያት የለውም፡፡

ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትዕዛዝ የጣሰ ለእግዚአብሔር የማይታዘዝና ለፈቃዱም የማይገዛ፤ እግዚአብሔርንም የማይወድ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ሰውን ወደደው፡፡ ሰውንም ስለወደደ ለሰው የሚገባውን ሞት ክርስቶስ እንዲሞት ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከው፡፡

ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ በመሆኑና የኃጢአትም ደመወዝ ሞት ስለሆነ፤ በዚህም ምክንያት ሰውን ከሚጠብቀው ከዘላለም ሞት እንዲያመልጥ ኃጢአት ያላወቀውን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን

ለሰው ሁሉ ኃጢአት እንዲሞት ወደ ዓለም በመላኩ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ያለውን ፍቅር ገለጸ፡፡ ይህንንም እውነት መጽሐፍ ቅዱስ፡- "ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና፡፡ .... ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፡፡" /ሮሜ 5፡6፣8/ በማለት ይመሰክራል፡፡

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ያፈቅራል፡፡ ወንጀለኛውን፣ ሌባውን፣ አመንዝራውን፣ ክፉ አድራጊውን፣ ሃይማኖተኛውን፣ መልካም የሚሠራውን፤ ሀብታሙንና ደሃውን፣ የተማረውንና ያልተማረውን፣ ሁሉንም ሰው እኩል ያፈቅራል፡፡ ክርስቶስ የሞተው ለሁሉም ዓይነት ሰው ነው፡፡ በደሙ እንዲጸድቁ፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዲድኑ፣ በልጁ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ የተጠሩት ሁሉም ናቸው፡፡ ሰው ሁሉ ስለዚህ አስደናቂ ፍቅር ሊሰማ ይገባዋል፡፡ ለዚህም ፍቅር ሰው የበኩሉን ምላሽ እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንንም የፍቅር አዋጅ፣ ታላቁን የምሥራች የቀመስን ሁላችን ላልቀመሱት እንድናውጅ ተጠርተናል፡፡

ይህ ዘመን እውነተኛ ፍቅር ከሰው ልጆች መካከል እየጠፋ ያለበት ዘመን ነው፡፡ አንድ እውነተኛ ፍቅር ቢኖር፣ እኛ ይህን ፍቅር የተረዳን ሰዎች ላልተረዱት መናገር አቅቶናል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ያፈቅራል፡፡ እስቲ እኛ ደግሞ ክርስቲያኖች የሆንን "እግዚአብሔር ያፈቅርሃል" ብለን ለሰዎች እንናገር፡፡ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን (ሰውን) ሁሉ እንዲሁ ወዷልና፡፡" ወገኔ ሆይ እግዚአብሔር እንዲሁ ወዶሃል፣ አንተም ፍቅሩን ልትቀበል ይገባሃል፡፡ ፍቅሩን ከተቀበልክ በኋላም የፍቅሩ አዋጅ ነጋሪ ልትሆን ይገባሃል፡፡

የእግዚአብሔርን ምህረትና ፍቅር የቀመሱ ሁሉ ላልቀመሱት መናገር እንዳለባቸው ሐዋሪያው ጴጥሮስ ለቤተክርስቲያን በጻፈው መልዕክቱ አስረግጦ እንዲህ ይላል፡- "እናንተ የንጉሥ ካህናት ናችሁ፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ ቅዱስና ንጹህ እንዲሁም የተለየ ወገን አድርጎ ለራሱ የመረጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ማድረጉ ከጨለማ ድንቅ ወደ ሆነው ብርሃኑ ያወጣችሁ መሆኑን ለሌሎች እንድትናገሩለት ነው፡፡ ቀድሞ እናንተ ወገን አልነበራችሁም፣ ዛሬ ግን ወገኖቹ ናችሁ፡፡ ቀድሞ የእግዚአብሔር ምህረት አልነበራችሁም፡፡ አሁን ግን መላ ሕይወታችሁ በምህረቱ ተለውጧለች፡፡" /1ጴጥ. 2፡9-10፣ ሕያው ቃል/





እግዚአብሔር ወገኖቹ ያደረገን እንዲሁ ስለወደደን ብቻ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ወገን ለመሆን የሚገባን ሆነን አልነበረም፡፡ አሁንም ለማይገባቸው ሁሉ እግዚአብሔር ፍቅሩን እንዲሁ ይገልጥላቸዋል፡፡ እውነተኛ ፍቅር የሚገኘው በእግዚአብሔር ዘንድና ከእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ወንጌል የዚህ የእውነተኛ ፍቅር መልዕ ክት ነው፡፡ እኛ ደግሞ የወንጌል መልዕክተኞች ነን፡፡ ከመልዕክት ሁሉ የሚበልጥ መልዕክት፣ ከአገልግሎት ሁሉ የሚልቅ አገልግሎት፣ ከሥራ ሁሉ የሚያረካ ሥራ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰው ልጆች ሁሉ ማብሰር ነው፡፡

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው በመጀመሪያ እርሱ ለእኛ ሕይወት ያለውን ዓላማ፣ እንዴት እንደወደደንና በፊታችን እንዴት ያለ አስደናቂ የዘላለም ሕይወት እንዳዘጋጀልን ማወቅና ለዚህ ዓላማው ራሳችንን መስጠት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሌላ ከእኛ የሚፈልገው፣ ይህን የመጀመሪያውን ዓላማውን ከተረዳን በኋላ ለሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ለሰው ልጆች ያዘጋጃትን የዘላለምን ሕይወት መንገድ ማብሰር ነው፡፡ እያንዳንዳችን የወንጌል ባለአደራዎች ነንና፡፡

ምናልባትም በዚህ ሰዓት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚወደኝ አሁን ገብቶኛል፡፡ ታዲያ ፍቅሩን እንዴት ልቀበለውና ልለማመደው እችላለሁ? የሚል ጥያቄ በልብህ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ዓላማና ፍቅሩን ከአሁን ሰዓት ጀምሮ መለማመድ ትችላለህ፡፡ እግዚአብሔር ያለው በሩቅ ሳይሆን በአጠገብህ ነው፡፡ ሰው ጽድቅንና መዳንን የሚያገኘው እንዴት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፡- "ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በአፍህ ብትመሰክርና እግዚአብሔር ከሞት እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ፡፡ ምክንያቱም ሰው በልቡ ሲያምን ይጸድቃል፤ በአፉም ሲመሰክር ይድናል፡፡" (ሮሜ.10፡9-10፣ አዲሱ ትርጉም) ይላል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ መስክር፣ እግዚአብሔርም ከሞት እንዳስነሣው በልብህ እመን፡፡ ለእግዚአብሔርም በጸሎት የልብህን መሻት ግለጥለት፡፡ እግዚአብሔር ስለሚወድህ አንተ በጸሎት ስታነጋግረው ለመስማትና ጸሎትህን ለመመለስ እጅግ ደስ ይለዋል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የሚመስል ጸሎት በመጸለይ ክርስቶስ ወደ ሕይወትህ እንዲመጣና የእግዚአብሔርም ዓላማ በሕይወትህ እንዲገለጥ ልትጸልይ ትችላለህ፡፡ "እግዚአብሔር ሆይ እኔን እንደምታፈቅረኝ አሁን ገብቶኛል፡፡ አንድ ልጅህንም ለእኔ

ለኃጢአተኛው በመስቀል ላይ እንዲሞት ልከሃል፡፡ ለሕይወቴም የተለየ ዓላማ እንዳለህ አምናለሁ፡፡ ሕይወቴ ትርጉም ያለውና የሚያረካ እንዲሆን ፈቃድህ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ለእኔ ያለህን ፍቅር እቀበላለሁ፡፡ እኔ በደለኛና ኃጢአተኛ ነኝና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፡፡ ልጅህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ስለሞተልኝና ፍቅሩን ስለገለጠልኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ጌታ ኢየሱስ መላ ሕይወቴንና ፈቃዴን እንዲቆጣጠርና የአንተም ዓላማ በሕይወቴ እንዲፈጸም እራሴን ለአንተ እሰጣለሁ፡፡ ፍቅርህ ከገባኝ በኋላ ደግሞ ላልገባቸው ሁሉ የምሥራቹን ወንጌል ለመናገር እወስናለሁ፡፡ አሜን"

ይህንን ዓይነት ጸሎት በእምነትና በሙሉ ፈቃድህ ከጸለይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ሕይወትህን መቆጣጠር ይጀምራል፡፡ እርሱም ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ማወቅ ትጀምራለህ፡፡ ከዚህ በኋላ ያንተ ኃላፊነት የምሥራቹን ወንጌል ላልሰሙ ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው መናገር ነው፡፡ እኛ የተጠራነው የእግዚአብሔርን በጎነት እንድንናገር ነውና፡፡ ወንጌል ማለት የእግዚአብሔር ምህረቱ፣ ፍቅሩ፣ ማዳኑና ኃይሉ ለሰው ልጆች የተገለጠበት የምሥራች ቃል እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የምሥራቹን ወንጌል ለሌሎች እንድንመሰክር የሚያነሳሱን ምክንያቶች ምን እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

## ወንጌልን ለምን እንመሰክራለን?

ወንጌልን ለሰዎች የመናገር ኃላፊነት የጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው፡፡ ስለሆነም ደህንነትን ያገኘ እያንዳንዱ ክርስቲያን ስላገኘው ደህንነትና እግዚአብሔር በሕይወቱ ስላደረገለት ነገር ለሌሎች እንዲመሰክር እግዚአብሔር ይጠብቅበታል፡፡

በሕይወታችን ያየነውንና የሰማነውን፣ የተደረገልንን ነገር ለሌሎች አለመናገር በራሱ ኃጢአት ነው፣ የምስጋና ሕይወት ማጣትና ውለታ ቢስ መሆን ነው፡፡ ለመሆኑ ወንጌልን ለሰዎች መመስከር ለምን አስፈለገ? እያንዳንዱ ክርስቲያን የምሥራቹን ወንጌል ለሌሎች መመስከር ያለበት ለምንድን ነው? ከዚህ ቀጥሎ ጥቂት ምክንያቶችን እንመለከታለን፡፡

### 1/ ጌታችን ኢየሱስ ወንጌልን የሚያስራጭ ስለነበር

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ የነበረውን ክብሩን ትቶ ወደ ምድር የመጣበት ዋናው ዓላማ የምሥራቹን ወንጌል፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ ለሰው ልጆች ለማብሰር ነበር፡፡ ይህ ዋና ተልዕኮው ነበር፡፡ ምናልባት በዚህ ሰዓት ራሳችንን መጠየቅ የሚገባን ኢየሱስ በእርግጥ የሕይወቴ መሪ ነው ወይ? የሚለውን ቢሆን ተገቢ ነው፡፡ መልሳችን አዎን ከሆነና ኢየሱስ በእርግጥ የሕይወታችን መሪ ከሆነ የእርሱ ዓላማ የእኛ ዓላማ፣ ራዕዩ የእኛ ራዕይ፣ ተልዕኮው ተልዕኮአችን፣ ቅድሚያው ቅድሚያችን ሊሆን እንደሚገባ እናምናለን፡፡

የኢየሱስ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ዓላማ ሰዎችን ከኃጢአት ማዳንና ከሰይጣንና ከጨለማው መንግስት ወደ ዘላለማዊው

የእግዚአብሔር መንግስት ማፍለስ ነበር፡፡ እርሱ ለተከታዮቹ የሰጠው የመጀመሪያውና የመጨረሻው ጥሪና ተልዕኮ የወንጌሉ ተልዕኮ ነበር፡፡ አገልግሎቱን ሲጀምር ለተከታዮቹ የሰጠው የመጀመሪያው ጥሪ "በኋላዬ ኑና (ወይም ተከተሉኝና) ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ" /ማቴ. 4:19/ የሚል ሲሆን አገልግሎቱንም ፈጽሞ ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ቀኝ ሲያርግ የሰጠው የመጨረሻው ጥሪ ያው ነበር "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚል /ማር.16:15/፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ጅማሬውም ሆነ ፍጻሜው ወንጌል ነበር፡፡ አገልግሎቱን ሲጀምር የመጀመሪያ መልዕክቱ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል፡፡" የሚል የወንጌል መልዕክት ነበር፡፡ /ሉቃ. 4:17-19/ አገልግሎቱንም ጨርሶ ለተከታዮቹ ሲያስረክብ የመጨረሻ መልዕክቱ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሚል ነው፡፡ /ሐዋ. 1:8/

ኢየሱስ የወንጌሉን መልዕክት ለመናገር ሰዎች ወዳሉበት ስፍራ ሄዷል እንጂ ሰዎች ወደእርሱ እስኪመጡ አልጠበቀም፡፡ ጌታ ወንጌልን እየሰበከ በየከተማው በየገጠሩና በየመንደሩ ዞሯል፡፡ ክርስቲያኖች ወንጌልን የትና እንዴት መመስከር እንዳለባቸው ኢየሱስ ራሱ ምሳሌ ሆኖ ከማሳየቱም በላይ "ቤቴ እንዲሞላ ወደ ገጠር በሚወስዱት ጐዳናዎችና ስላች መንገዶች ሂደህ ሌሎች እንዲመጡ አድርግ" /ሉቃ. 14:23፣ አዲሱ ትርጉም/ በማለት ወደ ተለያዩ መንደሮች ገጠሮችና አካባቢዎች ሄደን ስለ መንግስተ ሰማያት ግብዣ ለሰዎች እንድንናገር አዞናል፡፡ ወንጌልን ያልሰሙትን ሰዎች የምናገኛቸው ወዳሉበት በመሄድ እንጂ ወደእኛ እንዲመጡ በመጠበቅ አይደለም፡፡

ከእኛ ብዙዎቻችን የጌታን አዳኝነት የቀመስነው በራሳችን አነሳሽነትና ፍላጎት የእግዚአብሔር ቃል ወደሚነገርበት ስፍራ ሄደን አይደለም፡፡ ነገር ግን ሌሎች ሰዎች ቢያንስ በአንድ መንገድ ምክንያት ሆነውልን ነው እኛ ደህንነትን ልናገኝ የቻልነው፡፡ ሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ መስክረውልን፣ አሊያም ጸልየውልን ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ጋብዘውን ወይም ትራክት ሰጥተውን ወይም





የመዝሙር ካሴት አስደምጠውን ነው፡፡ ስለዚህ ለእኛ እንደተደረገልን እኛ ደግሞ ለሌሎች ልናደርግ ይገባናል፡፡ ኢየሱስ መሪያችን ነው ብለን ከተቀበልን እርሱ በተጓዘበት መንገድ መጓዝ አለብን፡፡

እርሱን እናመልካለን ብለው የተከተሉት የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች ተልዕኮውን ተልዕኮአቸው በማድረግ ኖረዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነዚያ ክርስቲያኖች ሲመሰክር "በየቀኑም በቤተ መቅደስና በየቤቱም ስለ መሲሁ ኢየሱስ ማስተማርንና የምሥራች መናገርን አላቋረጡም ነበር" ይላል፡፡ /ሐዋ. 5:42/ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች ወንጌልን የመሰከሩት በየዕለቱ ነበር፡፡ እንደ እኛ እሁድ እስከሚደርስ አልጠበቁም፣ ነገር ግን ሰኞም ማክሰኞም ረቡዕም፣ በእያንዳንዱም ቀን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው፣ አዳኝ ነው እያሉ ይመሰክሩ ነበር፡፡

ዛሬ በአካባቢያችን በየዕለቱ የሚሠሩ ብዙ የክፋት ሥራዎች አሉ፡፡ ሰዎች ይህን የክፋት ሥራ በየዕለቱ ለመሥራት እጅግ ይተጋሉ፡፡ ለምሳሌ ቡና ቤቶች በየዕለቱ የአልኮል መጠጥ ይሸጣሉ፣ የዳንስና የጭፈራ ቤቶች በየዕለቱ ተግባራቸውን ያከናውናሉ፣ የፊልም ቤቶች በየዕለቱ ይከፈታሉ፣ ወንጀልና ዝርፊያ የመሳሰሉ ክፉ ሥራዎች በየዕለቱ ይፈጸማሉ፡፡ ሰዎች እነዚህንና ሌሎችንም የክፋት ሥራዎች ለመሥራት በየዕለቱ የሚተጉ ከሆነ እኛ ሰዎችን ለዘላለም የሚያድነውን የክርስቶስን ወንጌል በየዕለቱ ለመስበክ እንዴት አንተጋም?

የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች ወንጌልን በመቅደስና በየቤታቸው ሁሉ ይመሰክሩ ነበር፡፡ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት ወንጌል የሚነገርበት ሥፍራ ነበረ እንጂ፣ በቤተመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ብቻ ወንጌልን ይናገሩ፣ ወይንም ደግሞ ወንጌል መነገር ያለበት በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ ነው በማለት ኃላፊነታውን ችላ አላሉም፡፡ ነገር ግን ኃላፊነታቸውን አውቀው በትጋት በየዕለቱ እንዲሁም በየቤታቸው ወንጌልን መስክረዋል፡፡ ስለዚህ መሪያችን ኢየሱስ እንዲሁም የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች በየስፍራው ሁሉና በየዕለቱ ወንጌልን ይሰብኩ እንደነበረ ሁሉ እኛም የቤተክርስቲያን ግድግዳና የእሁድ የአምልኮ ስብሰባ ሳያግደን ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም በቆራጥነት መነሳት ያስፈልገናል፡፡

## 2/ ወንጌልን መመስከር ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ

ወንጌልን መመስከር ልንታዘዘውና ልንፈጽመው የሚገባን መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው፡፡ ይህም ትዕዛዝ የተሰጠው ለቤተክርስቲያን መሪዎች፣ ለመጋቢዎች፣ ለወንጌላውያን፣ ለዲያቆናት ወይም ደግሞ "ለምስክርነት ቡድን" ብቻ ሳይሆን ከጌታ ዘንድ አዲስ ሕይወትን ለተቀበሉ ሁሉ ነው፡፡ ይህም ማለት ሁሉም ክርስቲያን ወንጌልን ለሌሎች እንዲመሰክር ተጠርቷል ማለት ነው፤ ስለሆነም ሁሉም ጥሪውን በፈቃደኝነትና በመታዘዝ ሊቀበል ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወንጌልን የመመስከር፣ የምስራቹን የማወጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ወንጌልን ለመመስከር ከጌታ ዘንድ "ልዩ ጥሪ" እስኪመጣ ወይንም ደግሞ ጥሪያችን በቤተክርስቲያን መሪዎች እስኪጸድቅ መጠበቅ አያስፈልግም፡፡

አንድ ሰው የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔርን መልካምነትና ቸርነት እንዲመሰክር ተጠርቷል፡፡ /1ጴጥ. 2፥8-9/ የክርስቶስ ትዕዛዝ ደግሞ በጣም ግልጽና ቀላል ነው፣ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ፡፡" የሚል ነው /ማቴ. 5፥14-16/ ጌታ የሰጠን ትዕዛዝ፡፡ የእኛ ምላሽ ደግሞ መሆን ያለበት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መታዘዝ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ደግሞ ለእርሱ ፍቅር የሌላቸው ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለእኛ የበራልንን ብርሃን እኛ ደግሞ ለሌሎች እንድናበራ ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ኃይል፣ አመራሩን፣ ችሎታውንና ብርታቱን ማወቅና መለማመድ የምንችለው እርሱን ለመታዘዝ እርምጃ ስንወስድ እንጂ ዝም ብለን በተቀመጥንበት ሥፍራ አይደለም፡፡ እኛ ስንሄድ እግዚአብሔር ይመራናል፣ እኛ ስንታዘዝ ሥልጣኑንና የሥራውን ብርታት በየዕለቱ ሕይወታችን እናያለን፡፡ ስለዚህ ምናልባት እስከዛሬ ድረስ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የአምላካችንን ትዕዛዝ፣ ወንጌልን ለሰዎች መመስከር ችላ ያልን ሁላችን እርሱን ልንታዘዝ አሁን ልንወስን ይገባናል፡፡

## 3/ ሰዎች ያለ ክርስቶስ የጠፉ ስለሆነ

መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የደህንነት መንገድ ኢየሱስ እንደሆነ ሲገልጽ "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን





ለሰዎች የተሰጠው ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና..." /የሐዋ. 4፥12/ በማለት በግልጥ ያስታውቃል፡፡ የሰዎች ሁሉ ፍላጎት ወደ እግዚአብሔር መድረስ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህም ነው ሰዎች ለተለያየ ሃይማኖት ራሳቸውን የሚሰጡት፡፡ ነገር ግን ሰዎች ወደ እርሱ መድረስ እንዲችሉ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ አንድ ብቻ ነው፡፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ፡፡ ኢየሱስም ራሱ ስለዚህ ሲናገር "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" በማለት መንገዱን በማያሻማ ሁኔታ ገልጾታል፡፡ /ዮሐ. 14፥6/

ስለዚህም ኢየሱስ ያለው ወይም እርሱን ያመነ ብቻ ወደ ዘላለም ሕይወት ሲገባ ኢየሱስ የሌለው ሁሉ መድረሻው የዘላለም ስቃይ ወይም ሲኦል ነው፡፡ የእያንዳንዱ ሰው የመጨረሻ መድረሻ ከሁለት አንዱ ብቻ ነው፡፡ መንግስተ ሰማያት ወይም የዘላለም እሳት፡፡ /1ዮሐ. 5፥11-13/ የኢየሱስን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፣ ስሙን ለመጥራት እንዲችሉ ሰዎች ማመን አለባቸው፤ ለማመን ደግሞ የምስራቹን ወንጌል መስማት አለባቸው፡፡ የምስራቹን እንዲሰሙ የሚነግራቸው ያስፈልጋል፡፡ የሚነግራቸው ደግሞ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ወደ ሰዎች መሄድ ወይም መላክ አለበት፡፡ /ሮሜ. 10፥13-15/፡፡ ስለዚህ ሰዎች በኢየሱስ አምነው ደህንነትን እንዲያገኙና ከዘላለም ሞት እንዲተርፉ የመጀመሪያው ምክንያት እኛ ክርስቲያኖች መልዕክቱን ለመናገር መሄድ ብቻ ነው፡፡ እኛ ካልሄድንና ካልነገርን ሰዎች ሊሰሙ፣ ሊድኑና የጌታን ስም ሊጠሩ አይችሉም፡፡

ሰዎች ወንጌልን መስማትና ኢየሱስን የማመንና ያለማመን ውሳኔ ማድረግ ያለባቸው በዚህ ምድር ላይ በሚኖራቸው የሕይወት ዘመናቸው ብቻ ነው፡፡ ከዚህች ምድር አንዴ ካለፉ በኋላ ወንጌልን ለመስማትና ወደ ደህንነት ለመምጣት እድል አይኖራቸውም፣ አይችሉምም፡፡ ሰው በምድር ያለውን የሕይወት ዘመኑን ከፈጸመ በኋላ የእግዚአብሔርን ምህረት ሊያገኝ አይችልም፡፡ የእግዚአብሔርን ምህረት የመቀበልና እምቢ የማለት እድል ለሰዎች የተሰጠው በዚህ ምድር ብቻ ነው፡፡

ይህንን እውነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሀብታሙ ሰውና ስለድሃው አልዓዛር በተናገረው ታሪክ ግልጥ አድርጎታል፡፡ /ሉቃ. 16፥19-31 ተመልከት/ ስለዚህ ነው **መጽሐፍ** ቅዱስ "የመዳን ሰዓት አሁን ነው፣ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው" /2ቆሮ. 6፥2/ በማለት ውሳኔያችንን አሁን እንድናደርግ ጠንከር አድርጎ የሚጠራን፡፡

ሰው በአንድ በሽታ የተለከፈውን ሰው የሚያድን መድኃኒት ቢያገኝለት ያን መድኃኒት ለበሽተኛው ለማድረስና በሽተኛውን ለመፈወስ ምንኛ ይቸኩላል? ኃጢአት ከማንኛውም በሽታ የከፋ በሽታ ነው። ኃጢአት ሰውን ከገደለ ውጤቱ የዘላለም ሥቃይ ነው። እኛ ክርስቲያኖች ሰውን ሁሉ ከኃጢአት በሽታ የሚያድን ታላቅ መድኃኒት ወይም መድኃኒዓለም በሕይወታችን አለ። ይህን መድኃኒት ለሰዎች ሁሉ መስጠት እንችላለን። ይህም መድኃኒት ለሰዎች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ የሞተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እኛ ይህን አዳኝ ባለመስጠታችን ምክንያት በየዕለቱ ወደ ዘላለም ስቃይ የሚሄዱ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ይሆን? እኛ በጌታችን ፊት ቆመን ሳለ የሚያውቁን ሰዎች ከሲያል ስማችንን ጠርተው ምናልባት በምድር ላይ እያለሁ ስለ ኢየሱስ ብትነግረኝ ኖሮ አሁን በዚህ እሳት ባልተሠቃየሁ ነበር ቢሉን ምን ይሰማን ይሆን?

## 4/ *አዝመራው ብዙ ስለሆነ /ማቴ. 9፡35-38/*

ጌታችን ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ እጅግ ያሳዘነውና ያሳሰበው ጉዳይ የመከሩ መብዛትና የሠራተኞች ቁጥር ጥቂት መሆን ነበር። ሰዎች እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተቅበዝብዘውና ተጥለው ባየ ጊዜ ኢየሱስ አዘነላቸው። ይህ ያለንበት ዘመን ሰዎች ከምን ጊዜውም ይልቅ እጅግ የተቅበዘበዙበት፣ ሰላምንና እርካታን እንዲሁም እረፍትን ያጡበት ጊዜ ነው። ሰዎች ተስፋና መመኪያ የሚሆናቸውን ከዓለም ፈልገው ሊያገኙ አልቻሉም። መንፈስ ቅዱስም በዓለም ሁሉ በአስደናቂ ሁኔታ ለወንጌል በር የከፈተበት ጊዜ ነው። የደረሰው አዝመራ በወቅቱ ካልተሰበሰበ ይበላሻል፣ ይበሰብሳል።

አዝመራን በወቅቱ የመሰብሰብን አስፈላጊነት በትክክል የተረዳው ጌታችን ኢየሱስ "እነሆ ዓይናችሁን አንሱ አዝመራውም አሁን እንደነጣ እርሻውን ተመልከቱ የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ መፈጸም ነው።" በማለት ከራሱ ፍላጎት ይልቅ የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ለመፈጸም ቅድሚያ ሰጥቷል። /ዮሐ. 4፡34-35/ ሐዋሪያው ጳውሎስም "ዳሩ ግን ወንድሞች ሆይ ይህን እናገራለሁ ዘመኑ አጭር ሆኖአል" በማለት ስለዘመኑ አጭርነት ይናገራል። /1ቆሮ. 7፡29/





መንፈስ ቅዱስ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ በሰዎች ልብ መንፈሳዊ ረሀብን የፈጠረበት ዘመን ቢኖር ይህ እኛ ያለንበት ዘመን ነው። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ወንጌል በዓለም ሁሉ እየተሰበከ ያለበት ዘመን ይህ ዘመንና ይህ ትውልድ ነው። "ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግስት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል" /ማቴ. 24፡14፣ አዲሱ ትርጉም/ የሚለው ትንቢት ሊፈጸም የተቃረበበት ዘመን ቢኖር ይህ ዘመን ነው።

በዚህ ዘመን እኛም ተነስተን ከእግዚአብሔር ጋር ልንሠራ ይገባል። እግዚአብሔር በሚሠራበት ዘመን የእርሱ ገንዘብ እንድንሆንለት ያስፈልጋል። ሠራተኞች ጥቂቶች ስለሆኑ እግዚአብሔር ሠራተኞችን ወደ መከሩ ለመላክ ይፈልጋል። በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን እንደተናገረው ዛሬም "ማንን ልላክ? ማንስ ይሄድልናል? " ይላል። አንተ "እኔን ላከኝ እኔ እሄድልሃለሁ" ትላለህ?

በአገራችን ውስጥ በአሁን ጊዜ ወደ 40 የሚጠጉ ገና ወንጌል ያልደረሳቸው ብሔር ብሔረሰቦች እንዳሉና 3,000 የሚደርሱ ሰዎች ወንጌልን ሳይሰሙ በኢትዮጵያ ብቻ በየቀኑ እንደሚሞቱ ይገመታል። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ወንጌልን ሳይሰሙ የሚሞቱት ወንጌልን አንሰማም ብለው ሳይሆን የሚያሰማቸውን ሰው ስላላገኙ ነው።

በአሜሪካን አገር የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚጠቁመው ወንጌል ወዳልደረሳቸው ለመሄድ ራሴን እሰጣለሁ ወይም እኔ እሄዳለሁ የሚል የቤተክርስቲያን መሪ ከ500 መካከል 1 ብቻ ነው። የቀሩቱ 499 መሪዎች በቤተክርስቲያናቸው ባሉበት ሥፍራ መቆየት የሚፈልጉ ናቸው እንጂ የጠፋውን ፍለጋ ለመሄድ የሚፈልጉ አይደሉም። እኔን ላከኝ እኔ እሄዳለሁ የሚሉ መሪዎች በአገራችንስ ስንት ይገኙ ይሆን?

የእግዚአብሔር ቃል "በመከር የሚተኛ ያፍራል" /ምሳ. 10፡5/ ስለሚል ከእንቅልፋችን ተነስተን የደረሰውን አዝመራ የምንሰበስብበት ጊዜው አሁን ነው። እግዚአብሔርን ዛሬም የሚያሳስበው ጉዳይ ቢኖር የሠራተኞች ቁጥር ማነስ ነው። በቤት ውስጥ በእንጀራ የሚጣሉ እንጂ በእርሻ ውስጥ በአጨዳ የሚደክሙ ሠራተኞች ብዙ የሉንም። ወንጌልን ለሰዎች ለማድረስ እግዚአብሔር አንተን የሚፈልገው በዚህ ምክንያት ነው። መከሩ ብዙ፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው።

## 5/ ጌታችን በክብር እንዲመለስ ወንጌል አስቀድሞ መሰበክ ስላለበት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንዲመጣ ሁላችንም እንናፍቃለን፣ ሁላችንም እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን ጌታችን በክብር እንዲመጣ በቅድሚያ መፈጸም ያለባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱና ዋነኛው ወንጌል ለሰዎች ሁሉ መሰበክ ነው፡፡ በዓለም ላይ ወንጌልን ፈጽሞ አልሰማሁም ወይም ለመስማት ፈጽሞ እድል አግኝቼ አላውቅም የሚል ሰው እስኪታጣ ድረስ ወንጌል ለሰዎች ሁሉ መሰበክ አለበት፡፡

ስለዚህ ነው ጌታ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" ብሎ ያዘዘን፡፡ ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ "ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል" (ማቴ. 24፡14) ይላል፡፡ ይህም ማለት ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች የመጨረሻው ምልክት የወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበክ ነው፡፡

ዓለም የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ኤትኖስ የሚል ሲሆን ትርጉሙም ወገን፣ ቋንቋ፣ ዘር፣ ነገድ፣ ጎሣ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል "ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል" ወይም "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ወንጌልን ስበኩ" ሲል ወንጌል ለየወገኑ፣ ለየቋንቋው፣ ለየዘሩ፣ ለየነገዱ ወይም ለየጎሣው ይሰበካል ማለት ነው፡፡ ያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል፣ ወይም በናፍቆት የምንጠብቀው ጌታችን በክብር ይመጣል፡፡

በቤተክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በሚቆሙበት ጊዜ ከየነገዱ፣ ከየቋንቋው፣ ከየወገኑ በበጉ ደም የታጠቡ ሰዎች በእግዚአብሔር መንግስት እንደሚገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል፡፡ "ከዚህ በኋላ እነሆ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል እጅግ ብዙ ሰዎች አየሁ፤ እነርሱ ከሕዝብና ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ የተውጣጡ ነበሩ፤ ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆመው ነበር፤ በታላቅ ድምፅ እየጮኹም፣ 'ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው የአምላካችንና የበጉ ነው' ይሉ ነበር፡፡" /ራዕ. 7፡9,14፣ አዲሱ ትርጉም፡፡/

እነዚህ ጌታ በሚገለጥበት ጊዜ ከየሕዝቡና ከየነገዱ በመንግስቱ የሚገኙ ሰዎች ጌታ ከመመለሱ አስቀድሞ ወንጌል በክርስቲያኖችና





በቤተክርስቲያን አማካይነት ወደየሕዝቡና ወደየነገዱ ደርሶ አምነውና በበጉ ደም ታጥበው የነጹ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ቤተክርስቲያን የወንጌልን ተልዕኮ ለየነገዱና ለየዘሩ ማድረስ አለባት፡፡ ቤተክርስቲያን ሲባል ክርስቲያኖች ተሰብስበን እግዚአብሔርን የምናመልክበት ህንፃ ሳይሆን እኛ ክርስቲያኖች ማለት ነው፡፡

ክርስቶስ ከመምጣት የሚዘገየው ሰዎች እንዳይጠፉ ነው፡፡ ብዙዎች ወንጌልን የመስማት እድል እንዲያገኙ ጌታ ይዘገያል፡፡ /2ጴጥ. 3፡9/ ስለዚህ ክርስቶስ ከመመለስ የሚዘገየው በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንዲባረኩ ወይም ለሁሉም "የጸጋ ሥጦታ እስኪሰጥ" ሳይሆን የምሥራቹን ወንጌል ያልሰሙ ሁሉ እንዲሰሙ ነው፡፡

እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ደግሞ ደግሞ እንዲባርከን ብዙ ጊዜ ዘምረናል፣ ብዙ ጊዜም ጸልየናል፡፡ የመጀመሪያ በረከቱን፣ ከኃጢአት ማዳኑን፣ የምሥራቹን ወንጌል ያልሰሙ እጅግ ብዙ ሰዎች በአጠገባችን ዓይናችን እያየና ልባችን እያወቀ ወደ ሲዖል ሲጓዙ እኛ ደግመን ደግመን ለመባረክ መፈለጋችን ምን ይባላል?

## 6/ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ስለሆንን

እግዚአብሔር ባሪያዎቹን ወደሚልካቸው ሥፍራ ሁሉ በመታዘዝ እንዲሄዱና ትዕዛዙንም እንዲፈጽሙ፣ የፍቅር መልዕክቱንም ለሰዎች እንዲናገሩ ያስጠነቅቃል፡፡ በነቢዩ በሕዝቅኤል አማካይነትም ለህዝቡ ለእስራኤላውያን ያስተላለፈው የማስጠንቀቂያ መልዕክት ይህ ነበር፡፡

"የሰው ልጅ ሆይ፣ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው፡፡ እኔ ኃጢአተኛውን፡- በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ፣ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፣ ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል፤ ደሙን ግን በእጅህ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን አንተ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ እርሱም ከኃጢአቱና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ፣ በኃጢአቱ ይሞታል፣ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል፡፡" /ሕዝ. 3፡17-19/ በተጨማሪም ሕዝ. 33፡ 6-8 ላይ ለእስራኤል ልጆች የተሰጠ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ እናነባለን፡፡

የጌታን አዳኝነት ላልሰሙና ከኃጢአት ነጻ የሚወጡበትን መንገድ ላላወቁ ሁሉ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የደህንነት መንገድ

የመናገር ኃላፊነት የእኛ የክርስቲያኖች ኃላፊነት ነው፡፡ ኃጢአተኞች ከሰሙ በኋላ ለራሳቸው የሕይወት መንገድ ለመከተልም ሆነ እምቢ ለማለት ምርጫቸው የራሳቸው ነው፡፡ እኛ ከተናገርን ከደሙና ከኃላፊነቱ ነጻ ነን፣ ካልተናገርን ግን እግዚአብሔር ደሙን ከእጃችን እንደሚፈልግ ወይም ለእነርሱ በኃጢአት መሞት እኛ ተጠያቂዎች እንደምንሆን ያስጠነቅቃል፡፡

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ለሚጠፉት ነፍሳት በእግዚአብሔር ፊት መጠየቅ የብሉይ ኪዳን ሕግ እንጂ አዲስ ኪዳን እንደዚህ አያስተምርም፣ እኛ ለሚጠፉት ነፍሳት አንጠየቅም በማለት በድፍረት ያስተምራሉ፡፡ ነገር ግን ይህ የአዲስ ኪዳንም ትምህርት እንደሆነና ኃጢአተኛውን ሁሉ ለማዳን በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለሞተውና ሞትን አሸንፎ ስለተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ለሰዎች ሁሉ የማድረስ ኃላፊነት፣ የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችና የራሱም ኃላፊነት መሆኑን በትክክል የተረዳው ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ራሱ አገልግሎት ሲናገር "እኔ ከሰው ሁሉ ደም ንጹህ እንደሆንሁ ዛሬ በዚህች ቀን እመሰክርላችኋለሁ" ብሏል፡፡ " ከሰው ሁሉ ደም ንጹህ ነኝ" ብሎ ለመናገር የቻለበትንም ምክንያት ሲገልጽ "አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን ንስሃ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ አስጠነቀቅሁአቸው" በማለት ኃጢአተኛውን እንዳስጠነቀቀና የተሰጠውን አደራ በታማኝነት እንደፈጸመ ተናገረ፡፡ /ሐዋ. 20፥17-27/

ጳውሎስ ኃላፊነቱንና ባለዕዳ መሆኑን በማወቁ ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ወንጌልን የመስበክ ዕዳ አለብኝ በማለት በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ወንጌልን ለሰዎች ሁሉ ሰብኳል፡፡ /ሮሜ. 1፥14-15/ ስለዚህም ሐዋሪያው ጳውሎስ ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ የተወጣ ታማኝ አገልጋይ ነበር፡፡ /ሮሜ. 15፥15-20/ እኛም የወንጌል ዕዳ አለብን፣ ወንጌልን ለሰዎች ካልተናገርን በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች መሆናችንን አውቀን፣ ከሰዎች ሁሉ ደም ንጹህ ለመሆን፤ በታማኝነት ወንጌልን ለምናገኛቸው ሁሉ እንናገር፡፡

## ተግባራዊ እርምጃዎች

እንግዲህ ወንጌልን የመመስከር ኃላፊነት እንዳለብህ ተረድተሃል፡፡ ለምን መመስከር እንዳለብህም ተገንዝበሃል፡፡ ይህን መጽሐፍ አንብበህ እንደጨረስክ ወዲያው ኃላፊነትህ መሆኑን





ዘንግተህ ተመቻችተህ እንዳትቀመጥ ለቀጣይ ሕይወትህ የሚጠቅሙ አንዳንድ ውሳኔዎችን ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አንድን ነገር እንድታደርግ ከተናገረህ ያን የተናገረህን ነገር ለመታዘዝ እርምጃ ውሰድ፡፡

ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጥ፡፡ ኢየሱስ ለሰዎች ያዘነላቸው በምን ምክንያት ነበር? አንተስ ከዚህ ምን ተማርክ? ከዛሬ ጀምሮ በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት፣ አንድ ወር፣ አንድ ዓመት ውስጥ ለስንት ሰው የክርስቶስን አዳኝነት ለመናገር ትወስናለህ? ወንጌልን ለሌሎች እንዳትመሰክር እንቅፋት የሆኑብህ ነገሮች ምንድን ናቸው? እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ምን ተግባራዊ እርምጃዎችን ትወስዳለህ?

አንተ የምታውቃቸውንና ክርስቶስን የማያውቁትን ሰዎች የምትችለውን ያህል ስም ዝርራቸውን ጻፍ፡፡ በወንጌል የሚገኘውን መዳን ሰምተው እንዲቀበሉ በየዕለቱ ጸልይላቸው፡፡ ለእነዚህ አንተ ለምታውቃቸው ሰዎች ከማንም ክርስቲያን ይልቅ ወንጌልን ለመመስከር የምትችለውና የመጀመሪያው ተጠያቂ አንተ እንደሆንክ አስብ፡፡ ለእነዚህም ሰዎች ለመመስከር የራስህን ዕቅድ አዘጋጅ፣ ቀንና ሰዓት ወስን፤ የትና እንዴት እንደምታገኛቸው በእያንዳንዱ ስም አንጻር በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መዝግብ፡፡

ወንጌልን እንዴት መመስከር እንዳለብህ ካላወቅህ በምዕራፍ ሦስት በተራ ቁጥር 6 የቀረበውን ሀሳብ ተመልከት፡፡ ለሌሎች ወንጌልን እንዴት መመስከርና ሰዎችን እንዴት የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ለማድረግ እንደምትችል ሰፋ ያለ ሥልጠና ለማግኘት ከፈለግህ ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር በመነጋገር በታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት የሚሰጠውን የወንጌል ስርጭትና የደቀ መዝሙር ሥልጠና መካፈል ትችላለህ፡፡ ትልቁ ነገር ሥልጠና መውሰዱ ሳይሆን ክርስቶስ በሕይወትህ ያመጣውን ለውጥና ምህረቱን ለሌሎች መመስከሩ ላይ ነው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ወንጌልን የማይመሰክሩበት ምክንያት ምን እንደሆነ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ክርስቲያንና መልዕክቱ

ወንጌልን ለሌሎች ሰዎች መናገርና ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲመጡ መንገዱን ማሳየት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ብዙዎቹም ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሌሎች መመስከር እንዳለባቸው ቢያውቁም እውነትን ሳይመሰክሩና ከጌታቸው የተቀበሉትን አደራ ሳይወጡ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህም የክርስቶስን አዳኝነት የሚመሰክሩ ክርስቲያኖች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ለመሆኑ ወንጌልን እንዳንመሰክርና ከጌታ የተቀበልነውን ተልዕኮአችንን በታዛዥነት እንዳንፈጽም የሚያደርጉን ነገሮች ምንድር ናቸው? ከብዙ ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ/ ቅድስና የጎደለውን መንፈሳዊ ሕይወት መኖር፣ 2ኛ/ የዲያቢሎስ አሠራርና 3ኛ/ የምናስተላልፈውን የወንጌሉን መልዕክት እንደሚገባ አለማወቅ ናቸው፡፡

ሁላችንም ባይሆን ብዙዎቻችን ወንጌልን ለሌሎች መመስከር እንዳለብን እናምናለን፡፡ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት የማምጣት አደራ እንደተሰጠንና በመክሊታችንም ማትረፍ እንዳለብን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ይህን ስናደርግ አንታይም፡፡ በዓለም ላይ በ100 ዓ.ም. ገደማ ለአንድ ክርስቲያን 360 ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ይገኙ ነበር፡፡ ይህ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቶ በአሁን ጊዜ በዓለም ላይ ለአንድ ክርስቲያን 6 ብቻ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ይገኛል፡፡

ይህም ማለት ራሱን ክርስቲያን ብሎ የሚጠራ እያንዳንዱ ሰው የወንጌል ተልዕኮ ኃላፊነት ቢሰማውና ለክርስቶስ በመታዘዝ ወንጌልን ለሌሎች ቢመሰክር ኖሮ በአጭር ጊዜ ዓለምን ሁሉ በወንጌል ለመድረስ እንደሚቻል ያመለክተናል፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ ያህል እኔ ክርስቲያን ነኝ የሚል እያንዳንዱ ሰው የኢየሱስን አዳኝነት በቀን ለአንድ ሰው ቢመሰክር ዓለም ሁሉ ከስድስት ቀን በኋላ ወንጌልን ሰምቶ ያበቃል ማለት ነው፤ ወይንም ደግሞ በወር ለአንድ ሰው ቢመሰክር በስድስት ወር ዓለም ሁሉ ወንጌልን ይሰማል ማለት ነው፡፡

በአገራችን በኢትዮጵያም እያንዳንዱ በወንጌል የሚያምን ሰው ለሌሎች አስር ሰዎች የወንጌሉን የምሥራች ቢናገር ታላቁ ተልዕ ኮን መፈጸም ይቻላል፡፡ ታላቁ ተልዕኮን መፈጸም ወይም ወንጌል ላልደረሳቸው ሁሉ ማድረስ ይህን ያህል ቀላል ከሆነ ታዲያ እንዳንፈጽም ያደረገን፣ እንቅፋት የሆነብን ምንድን ነው?

## 1. ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ስለ ደህንነታቸው እርግጠኞች አይደሉም

በአሜሪካን አገር በቤተክርስቲያን ላይ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው በዛሬ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ከሚመላለሱትና ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው ከሚጠሩ ሰዎች መካከል ግማሾቹ /50%/ ስለ መዳናቸው ወይም በክርስቶስ የዘላለምን ሕይወት ስለማግኘታቸው እርግጠኞች አይደሉም፡፡ አሁን ቢሞቱ ወደ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግስት እንደሚገቡ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆናቸውን የገለጡት ግማሹ ብቻ ናቸው፡፡

በአገራችንም ቢሆን በየአምልኮውና በየኮንፍራንሱ ወንጌልን ሰምተው የሚቀበሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል በወንጌሉ እውነት የሚኖሩና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉ ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ ለዚህም፣ ለብዙዎቹ በእግዚአብሔር ቤት አለማደግ ምክንያቱ በዎች ጌታን ለማመን በሚወስኑበት ጊዜ በቂ የሆነ የደህንነት ማረጋገጫ ስለማይሰጣቸው ነው፡፡ ታዲያ ክርስቲያኖች ራሳቸው መዳናቸውን ካላረጋገጡ እንዴት ለሌሎች ክርስቶስ ያድናል፣ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣችኋል ብለው ሊመሰክሩ ይችላሉ? አንድ በክርስቶስ ያመነ ሰው መዳኑንና የዘላለም ሕይወት እንዳለው እንዴት እርግጠኛ ሊሆን እንደሚችል በምዕራፍ አራት መመልከት ትችላለህ፡፡





## 2. ብዙዎች ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ናቸው

ይኸው ከላይ የተጠቀሰውና በአሜሪካን አገር የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው በዓለም ላይ ከሚገኙ ክርስቲያኖች መካከል በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የተቀበሉና በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሆነው እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ከመቶ አምስቱ ብቻ ናቸው፡፡ የተቀሩት ከመቶ ዘጠና አምስቱ በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ናቸው፡፡

በምድር ላይ የመንፈስ ቅዱስ ዋና ሥራው የእግዚአብሔርን መንግስት እውነት መመስከር፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር፣ በሰማይ ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግና በኃጢአታቸው ንስሐ ያልገቡትን ሰዎች ስለኃጢአታቸው መውቀስ ነው፡፡ /ዮሐ. 16፡7-15/

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የኖሩ ክርስቲያኖች በዘመናቸው የነበረውን ትውልድ በሙሉ በወንጌል ለመድረስ የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸውና ሕይወታቸውን በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ አመራር በማስገዛታቸው ነበር፡፡ በእኛ ትውልድ ዓለም ሁሉ ወንጌልን እንዲሰማ ከፈለግን በሐዋሪያት ዘመን የሠራው የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ሕይወትና በእኛ ዘመን እንዲሠራ ልንፈቅድለት ይገባል፡፡

በትልቅ ድፍረትና በብዙ መስዋዕትነት ወንጌልን እስከ ምድር ዳርቻ ያዳረሱት የወንጌል አርበኞች በበዓለ ሃምሣ ቀን ከዚያም በተደጋጋሚ የተሞሉትን መንፈስ ቅዱስ ልንሞላ ይገባናል፡፡ /ሐዋ. 2፡1-4 ፣ 4፡8,31/ ይህም መንፈስ የኃይልና የድፍረት፣ የጥበብና የእውቀት መንፈስ ነው፡፡ ሰማያዊ ሥራ የሚሠራው በሰማያዊ ኃይል ነው፡፡ የእግዚአብሔርም ሀሳብና ፈቃድ በዘመናችን ሊፈጸም የሚችለው በእግዚአብሔር አመራር ነው፡፡

የሰማያዊ ኃይልና የእግዚአብሔርም አመራር ምንጩ ደግሞ በእኛ እንዲኖርና ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ወንጌልን ለሰዎች ለማድረስ መንፈስ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ባያውቅ ኖሮ ፈሪዎችና እምነተ ቢሶች ለነበሩ ደቀመዛሙርቱ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳ ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡፡"

(የሐዋ. 1፡8) ባላላቸውም ነበር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት የመጀመሪያው ዓላማ የክርስቶስ ምስክሮች ለመሆንና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን ለሰዎች ለማድረስ ነው፡፡

## 3. ብዙዎች ክርስቲያኖች በግላቸው ወንጌልን አይመሰክሩም

በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሰው ጥናት እንደሚያመለክተው ወደ ቤተክርስቲያን ከሚመላለሱ ክርስቲያኖች መካከል የክርስቶስን አዳኝነት ዘወትር ለሌሎች የሚመሰክሩት ከመቶ ሁለት እጅ ብቻ ናቸው፡፡ ከመቶ ክርስቲያኖች መካከል ዘጠና ስምንቱ በቸልተኝነት፣ በስንፍና ወይም ኃላፊነታቸውን ባለማወቃቸው ምክንያት የምሥራቹን ቃል ለሌሎች ሳይናገሩ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡

እንግዲህ ምንም እንኳ ዓለማችንን በእኛ ትውልድ በወንጌል ለመድረስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ስድስት ሰው ብቻ የሚደርሰው ቢሆንም ብዙዎቻችን ግን ኃላፊነታችንን ዘንግተን በመቀመጣችን ምክንያት በጣም ቀላል የነበረው ሥራ እጅግ ከባድና ተራራ መስሎ ይታየናል፡፡

ስለዚህ በቸርነቱ ያዳነን ጌታ ኢየሱስ የሰጠንን ታላቁን ተልዕኮ በዘመናችን ለመፈጸም እንድንችል 1ኛ/ የዘላለምን ሕይወት ማግኘታችንን እርግጠኞች መሆን፣ 2ኛ/ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላትና ሕይወታችንን መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠር መፍቀድና፣ 3ኛ/ የክርስቶስን አዳኝነት ለሌሎች ለመመስከር ራሳችንን በፈቃዳችን ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድና ሀሳብ ማስገዛት ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህ አንተ ከላይ ከተገለጹት ከሦስቱ አይነት ሰዎች የትኛው ነህ?

### ሀ/ ስለ ዘላለማዊ ደህንነትህ እርግጠኛ ነህ?

አሁን በዚህ ሰዓት ብትሞት ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባትህ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነህ? ካልሆንክ ለሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር ከመመስከርህ በፊት ምዕራፍ አራትን በማንበብ ስለደህንነትህ እርግጠኛ መሆን ይገባሃል፡፡





### ለ/ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ትኖራለህ?

የሕይወትህ ባለቤት ማነው? ሕይወትህን የሚቆጣጠረውና የሚገዛው እግዚአብሔር ነው ወይስ አንተ ራስህ? የሕይወትህ ባለቤት፣ ገዢና ተቆጣጣሪ መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በሕይወትህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደማትችል ተገንዘብ፡፡ ምናልባት ይህ የወንጌል አደራ የተሰጠኝ ለእኔም ጭምር ነው፣ ነገር ግን ሕይወቴ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አይደለም የምትል ከሆነ አሁን ባለህበት ስፍራ ሆነህ መንፈስ ቅዱስ ሕይወትህን እንዲሞላውና የወንጌሉ ምስክር አድርጐ እንዲጠቀምብህ በጸሎት ጠይቀው፡፡ መንፈስ ቅዱስም ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ሕይወትህን መቆጣጠር ይጀምራል፡፡

### ሐ/ ዘወትር ኃላፊነት ተሰምቶህ ወንጌልን ለሌሎች ትናገራለህ?

እስከ ዛሬ በአንተ ምስክርነት ወደ እግዚአብሔር መንግስት የገባ ሰው አለ? የምስክርነት ሕይወትህ ባዶ ከሆነ ዛሬውኑ ለሰዎች ለመመስከር ወስነህ እርምጃ ውሰድ፡፡

## 4. ብዙዎች ክርስቲያኖች ቅድስናና ፍቅር የጎደለው ሕይወት ይኖራሉ

የተሰጠንን መለኮታዊ ተልዕኮ ለመፈጸም ያልቻልንበት ሌላው ምክንያት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስንኖር ቅድስና የሌለውን፣ ፍቅር የጎደለውን፤ ርኩሰት፣ ጥላቻ፣ ቂምና በቀል፣ ተንኮልና ምቀኝነት የሞላበትን ሕይወት በመኖራችን ነው፡፡ ይህም ችግር በተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች ትታወቅ በነበረችዋ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንም የነበረና ለወንጌል ሥራ ትልቅ እንቅፋት የፈጠረ በመሆኑ ሐዋሪያው ጳውሎስ ተቸግሮ ስለነበረ እንደሚከተለው ጽፎላቸዋል፡፡

"ወንድሞቼ ሆይ መንፈሳውያን ለሆኑ ሰዎች እንደምናገር አድርጌ ልናገራችሁ አልቻልም፡፡ የምነግራችሁ ሥጋውያን በመሆናችሁ ገና ለሚጠቡ ሕፃናት እንደምናገር ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ገና ስላላደጋችሁና ጠንካራ ምግብ መብላት ስለማትችሉም እንደ ህፃን ወተት ጋትኳችሁ፣ ገና አሁንም በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር እንዳለ ይሰማኛል፡፡ ይህ ሁኔታ አሁንም ገና ሕፃን

መሆናችሁንና የምትሠሩት በእግዚአብሔር ሳይሆን በገዛ ፍላጎታችሁ እየተመራችሁ መሆኑን ያሳያል፡፡ አንዱ 'እኔ የጳውሎስ ነኝ' ሌላው ደግሞ 'እኔ የአጵሎስ ነኝ' እያላችሁ እንዲህ ያለውን መለያየት መፍጠራችሁ ምን ይባላል? ይህም ገና በሥጋዊ ባህርያችሁ እንደምትመሩ ያሳያል፡፡" /1ቆሮ. 3፡1-4፣ ሕያው ቃል /

ሐዋሪያው የቆሮንቶስን ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች "ለስሙ ክርስቲያኖች ናችሁ ነገር ግን እንደ ክርስቲያን አትመላለሱም፣ ወንድሞች ናችሁ ግን ከወንድሞች የሚጠበቅ ባህርይ አይታይባችሁም፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ብዙ ማደግና መንፈሳውያን መሆን ሲገባችሁ እስካሁን ያላደጋችሁ ሕፃናት፣ ሥጋውያን፣ ዓለማውያን፣ በሰማያዊ ሳይሆን በምድራዊ ሀሳብ የምትመላለሱ፣ በአንድነት በፍቅርና በቅድስና የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ሲገባችሁ በቅናት፣ በክርክር፣ በመለያየት ተበታትናችኋል፡፡ ከዓለም ሰዎች በምን ትለያላችሁ? ክርስቲያኖች መሆናችሁ በምን ተለይቶ ይታወቃል?" በማለት በሚያሳዝን ሁኔታ ይገስጻቸዋል፡፡

እኛስ ዛሬ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ከነበሩት ሥጋውያን ክርስቲያኖች በምን እንለያለን? ቅናት፣ ክርክር፣ ምቀኝነትና መለያየት በየቤተክርስቲያኖቻችን የሞሉ በሽታዎች አይደሉምን? ቅድሚያ የምንሰጠውም ለራሳችን ኑሮ፣ ለራሳችን አገልግሎት፣ ለራሳችን ቤተክርስቲያን፣ ለራሳችን "ዲኖምኔሽን" እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ፣ ለእግዚአብሔር አገልግሎት፣ ክርስቶስ ለመሠረታት ቤተክርስቲያን፣ ለእግዚአብሔር መንግስት መሆኑ እየቀረ መምጣቱን አስተዋይ ልቦና ያለውና የእግዚአብሔር መንግስት ጉዳይ የሚገደው ሁሉ ሊመሰክር ይችላል፡፡

በትውልዳችን ወንጌልን ፈጽመን ለመስበክ ፍላጎት ያለን ሁሉ ርኩሰትን፣ መለያየትን፣ እኔነትን፣ ሥጋዊነትን፣ ቅናትንና ምቀኝነትን ከመካከላችን አስወግደን ሁላችንንም አንድ ያደረገንን፣ የለወጠንንና የዘላለም መንግስት ወራሾች እንድንሆን ያበቃንን የወንጌሉን ተልዕኮ ትኩረት ልንሰጥበት ይገባል፡፡ ስንፍናን፣ ቸልተኝነትንና ምን ቸገረኝነትን እግዚአብሔር ከሕይወታችን እንዲያስወግድልንና ወንጌልን ለመመስከር የሚያስችለንን ቅድስናና ፍቅር እንዲሰጠን አጥብቀን ልንጸልይ ይገባናል፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ የምሥራቹን ወንጌል በመካከላቸው አንድም ሰው ሳይቀር ለሁሉ ሰው መመስከሩን ያረጋገጠበት የኤፌሶን ቤተክርስቲያን /ሐዋ. 20/ ከሠላሣ ዓመት በኋላ ለእግዚአብሔር





የነበራቸውን ፍቅር ትተው እንዴት እንደወደቁ እንዲያስቡና ከኃጢአታቸውም ንስሃ እንዲገቡ ጌታ ኢየሱስ መልዕክት ልኮላቸው ነበር፡፡ "የፈጸምከውን ሥራ አውቃለሁ፡፡ በትጋት የምትሰጠውን አገልግሎትና ትዕግስትህንም ተረድቻለሁ፡፡ ... ለእኔ ስትል መከራን ሁሉ ያለመታከት በትዕግስት ተቀብለሃል፡፡ ነገር ግን፣ አንድ ጉድለት አግኝቼብሃለሁ፡፡ እርሱም የዛሬ ፍቅርህ እንደ ድሮ አይደለም፡፡ ድሮ ለእኔ የነበረህ ፍቅር አሁን ቀንሶአል፡፡ ስለዚህ የድሮ ፍቅርህ ምን ያህል እንደነበረ አስብ፡፡ ከዚህ ቀደም እንዴት ትወደኝ እንደ ነበርና፣ አሁን ግን እንዴት እንደተለወጥክ ልብ በል፡፡ ስለዚህ ንስሐ ግባ፤ መጀመሪያ ከልብ ታፈቅረኝ በነበረ ጊዜ ትፈጽመው የነበረውን ተግባር አከናውን፡፡ ንስሐ ባትገባ ግን መቅረዝህን ከሥፍራው አነሣዋለሁ፡፡ /ራዕ. 2፡ 2-5፣ ሕያው ቃል፡፡/

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን የነቀፈበት ምክንያት የአገልግሎት ብዛት ስላልነበራት ሳይሆን ለጌታ ከልብ የመነጨ ፍቅር ስለሌላት ነበር፡፡ ብዙ ትሠራለህ፣ ብዙ ትደክማለህ፣ ብዙ ታገለግላለህ እንዲያውም በአገልግሎትህ ትጉህ ነህ፤ ነገር ግን አገልግሎትህ ከፍቅር የመነጨ አይደለም፡፡ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል፣ ደክመሃል፣ ዝለሃል፡፡ ስለዚህ ድሮ የነበረህን ፍቅር አስብ፣ ያ የነበረህ ፍቅር ዛሬ አለህ ወይ? ዛሬም በቀራንዮ መስቀል ላይ የሞተልህን፣ በጌቴሰማኒ የደም ላብ ያላበውን በሥቃዩ ለአንተ እረፍትን የሰጠህን ጌታ ኢየሱስን ታፈቅረዋለህ? ለጌታ ያለህ ፍቅር ቀንሶብህ ከሆነ አሁኑኑ ንስሃ ግባ፣ ጌታ ሆይ አፈቅርሃለሁ በል፡፡

የዛሬው ቀን አልፎ አዲስ ቀን በተተካ ቁጥር ብዙ ክርስቲያኖች ለጌታ ያላቸው ፍቅር እየቀዘቀዘ እንደሚሄድ አትጠራጠር፡፡ (ሉቃ. 18፡8) አንተ ግን በግልህ ለጌታ ያለህ ፍቅር እንዳይቀዘቅዝ ትጋ፣ ጌታም እንዲረዳህ ጸልይ፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለቤተክርስቲያን ሪቫይቫልን (መንፈሳዊ መነቃቃትንና ተሃድሶን) የሚያመጡ ሰዎች በግል ሕይወታቸው ሪቫይቫል ያለባቸው ናቸው፡፡ በጌታ ፍቅር የሚቃጠሉ ሰዎች የተሃድሶ ተስፋዎችና የእግዚአብሔር ዓይን ማረፊያዎች ናቸው፡፡

ጌታን የሚያፈቅር ሰው ብዛት እየመነመነ ሲሄድ፣ ከምድር ላይ እምነት እየታጣ ሲሄድ፣ አንተ ግን ከጌታ እግር ሥር አትታጣ፡፡ ለጌታ ፍቅር ካለህ፣ ወንጌልን ቸል እንዳትል የሚያደርግ ታላቅ ኃይል በውስጥህ ይኖራል፡፡ ለጌታ ፍቅር ካለህ በስንፍና ልትኖር ከቶ አትችልም፡፡ ምክንያቱም የፍቅር እሳት የስንፍና ጠላት ነውና፡፡ የክርስትና መልዕክት የፍቅር መልዕክት ነው፣ በተግባር የሚገለጥ የቅድስና መልዕክት ነው፡፡

ወንጌል ዛሬ ወደ እኛ የደረሰው በሰነፎችና በቸልተኞች አይደለም፡፡ ነገር ግን ጊዜና ሁኔታ በማይሽረው የፍቅር እሳት ልባቸው እየነደደ፣ እግዚአብሔርን ከማፍቀራቸው የተነሳ የተሰጣቸውን የወንጌል ተልዕኮ ለመፈጸም ሕይወታቸውንና ነፍሳቸውን ሳይሳሱ ለወንጌል በሰጡ ቆራጥ የወንጌል አርበኞች ነው፡፡ ይህን በብዙ መስዋዕትነት ወደ እኛ የደረሰውን የወንጌል መልዕክት እኛ ደግሞ በትውልዳችን በቆራጥነት ለሌሎች ማስተላለፍና ኃላፊነታችንን መወጣት ያስፈልገናል፡፡

ይህን ለማድረግ የምንችለው በየዕለቱ በሕይወታችን የሚቀጣጠልና እረፍት የሚነሳን የጌታ ፍቅር ነፍሳችንን የተቆጣጠረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔርን እናፈቅረዋለን ካልን ደግሞ ማፍቀራችንን የምንገልጸው እርሱ ያዘዘንን መለኮታዊ ትዕዛዝ በመታዘዝ ብቻ ነው፡፡ "ትዕዛዜን ተቀብሎ የሚፈጽመው፣ ያ በእርግጥ ይወደኛል፡፡ የሚወደኝንም ደግሞ አባቴ ይወደዋል፡፡ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡" /ዮሐ. 14፡21፣ ሕያው ቃል፡፡/

# 5. ብዙዎች ክርስቲያኖች የሰይጣንን የማታለያ ዘዴዎች አያውቁም

የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሀሳብ ለማገልገል የምንፈልግና ለዚህም አገልግሎት ራሳችንን የሰጠን ክርስቲያኖች ሁልጊዜ በሰልፍ ሜዳ ላይ መሆናችንን መገንዘብ ያስፈልገናል፡፡ ይህንን ካወቅን በሚያጋጥመን ሁኔታ ሁሉ ተስፋ ሳንቆርጥ ለተጠራንበት ታላቅ ዓላማ በየዕለቱ ለመኖር ራሳችንን እናዘጋጃለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ " የምንዋጋው ሰብአዊ ፍጡራን ከሆኑ ሰዎች ጋር ሳይሆን፣ ይህንን የጨለማ ዓለም ከሚያስተዳድሩ መንፈሳውያን ገዢዎችና ኃይላት፣ እንዲሁም ሥልጣናትና በአየር ላይ ከገነኑ የርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው፡፡" /ኤፌ. 6፡12፣ ሕያው ቃል/ በማለት ለሰልፍ መዘጋጀት እንዳለብን ያሳስበናል፡፡ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እኛ በሰልፍ ሜዳ ላይ መሆናችንን ብቻ ሳይሆን በሰልፍ ሜዳ አሸናፊዎች መሆናችንንም ያረጋግጥልናል፡፡

"በዓለም ውስጥ እንደሌሎች ሰዎች የምንኖር ቢሆንም፣ የምንዋጋው ጦርነት መንፈሳዊ ነው፡፡ በዚህ ጦርነት ውስጥ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ሰው ሠራሽ አይደሉም፡፡ ነገር ግን፣ የጠላታችንን የዲያቢሎስን ምሽግ ለመደምሰስ የሚችሉ መለኮታዊ ኃይል ያላቸው ናቸው፡፡ በእነዚህም መሣሪያዎች፣ በእግዚአብሔር እውቀት ላይ





የሚሰነዘረውን ክርክርና ከንቱ ትምክህት ፍርስርሱን በማውጣት ሰብአዊ አስተሳሰብ ሁሉ ለክርስቶስ እንዲገዛ እናደርጋለን፡፡" /2ቆሮ 10፡3-4፣ ሕያው ቃል፡፡/

ወንጌል ሰዎችን ከሰይጣን ግዛት ነፃ በማውጣት ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚያመጣ ታላቅ መልዕክት ነው፡፡ ወንጌል በተሰበከ ቁጥር ሰዎች ነፃነት ያገኛሉ፡፡ የተጫነባቸው የጠላት ቀንበር ከላያቸው ይሰበራል፣ ከእግዚአብሔርም አስደናቂ ፍቅር የተነሳ ሰዎች ከሰይጣን መንግስት ይማረካሉ፣ የሰይጣን መንግስትና አስፈሪው ሲኦል ባዶ ይሆናል፡፡ ሰይጣን ሰዎች ወንጌልን ሰምተው ከመንግስቱ እንዲሄዱበት አይፈልግም፡፡ ስለዚህም በሚችለው ሁሉ የወንጌል መልዕክት እንዳይተላለፍ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

የወንጌልን ተልዕኮ አደራ የተቀበሉት ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሌሎች እንዳይመሰክሩ በማድረግ፣ የሚመሰክርላቸውም ሰዎች ወደ እውነት እንዳይደርሱ የእውነትን መልዕክት ከልባቸው በመልቀምና ጥርጣሬንና ፍርሃትን ወደ አእምሮአቸው በማምጣት፣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዳይገቡ ጠላት ዲያቢሎስ የሚጠቀምባቸው የማታለያ ዘዴዎች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ሁሉንም በዚህ ሥፍራ ዘርዝረን ለማየት የሚቻል ባይሆንም ዘዴዎቹን ተገንዝበን የጠላትን ሀሳብ ማፍረስ እንድንችል ከዘዴዎቹ ጥቂቶቹንና የእኛ ምላሽ ደግሞ ምን መሆን እንዳለበት ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* የራስህን እምነትና አመለካከት በማንም ላይ የግድ መጫን የለብህም ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* ይህን የሚመስል ሀሳብ ወደ ልብህ በሚመጣበት ጊዜ ይህ ድምፅ የሚመነጨው ከሰይጣን መሆኑን አውቀህ ራስህን የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቅ፡፡ "ለእኔ ክርስቶስን የመሰከረልኝ ሰው ይህን ዓይነት የማታለያ ድምፅ ሰምቶ ለእኔ ወንጌልን ሳይመሰክርልኝ ቀርቶ ቢሆን ኖሮ እኔ ዛሬ የት እገኝ ነበር? ዕጣ ፈንታዬስ ምን ይሆን ነበር?"

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* ስለ ክርስቶስ ብትመሰክርለት ይህ ሰው ይቀየምሃል፤ ስለዚህ ዝም በለው፣ አንዳች አታናግረው ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* ለምሳሌ አንድ የምታውቀው ሰው በካንሰር በሽታ ቢታመምና አንተ የበሽታው መድኃኒት ቢኖርህ ይህን መድኃኒት ብሰጠው በሽተኛው ይቀየመኛል ትላለህ? ኃጢአት ከበሽታዎች ሁሉ የከፋ በሽታ ነው፡፡ ኢየሱስም ከመድኃኒቶች ሁሉ የላቀ የዘላለም መድኃኒት ነው፡፡ ይህን ከኃጢአት ሁሉ የሚያድነውን ታላቅ

መድኃኒት ኢየሱስን ይዘህ እንዴት በኃጢአት በሽታ ለተያዙት የበለጠ አትሰጥም?

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* ዛሬ ሳይሆን ሌላ ጊዜ ቀስ ብለህ ትመሰክርለታለህ ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* እስከ ነገ ድረስ መኖሩን እርግጠኛ የሆነ ሰው ማን ነው? አንተስ ስለራስህ እርግጠኛ ነህ? የእግዚአብሔር ቃል ይህንን እውነት ሊያረጋግጥልን ስለፈለገ "እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፣ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው" /2ቆሮ 6፡2/ በማለት ማድረግ የሚገባንን ነገ ሳይሆን ዛሬ፣ ዛሬም ሲባል አሁን እንድናደርግ ያሳስበናል፡፡

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* ይህ ሰው ከመሰከርከለት በጣም ታበዛዋለህ፣ ችኮ ነህ ይልሃል ማቁት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* ምናልባት ያ ሰው ስለክርስቶስ እንድትነግረው መንፈስ ቅዱስ የመራህና በዚያች ጊዜ ጌታን ሊቀበል ልቡ የተዘጋጀ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ የክርስቶስን አዳኝነት ለሰዎች ስንመሰክር ሁሉ ላይቀበል ይችላል፣ የእኛ ኃላፊነት ግን ማሳመን ሳይሆን "ኢየሱስ ያድናል" ብሎ ለሰዎች መመስከር ነው፡፡ ሰዎችን በኃጢአታቸው መውቀስና ሕይወታቸውን መለወጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* ይህ ሰው እምቢ ይልሃል ከዚያም ታፍራለህ ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* በክርስቲያኖች እስከ ዛሬ የተነገረ ትልቅ ውሸት "እርሱ እኮ ስለ ጌታ መስማት አይፈልግም፣ እነርሱ እኮ ክርስቶስን አይሰሙም፣ አይፈልጉትም፣ አይቀበሉትም" ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ሰዎች እግዚአብሔርን የተጠሙ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ከፈጣሪው ጋር ተመልሶ ካልተስማማና እግዚአብሔርን የሕይወቱ ጌታ ካላደረገ የሚኖረው ኑሮ የመቅበዝበዝ፣ የመጨነቅና የፍርሃት ኑሮ ነው፡፡

*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* አንተ እኮ ፈሪ ነህ፣ ደግሞም ወንጌልን ለመመስከር በቂ ዕውቀት የለህም ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* ለሰዎች ወንጌልን የምንመሰክረው በራሳችን ኃይል ወይም ዕውቀት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚገለጥ ዕውቀት ነው፡፡ /2ጢሞ. 1፡7 ፣ የሐዋ 4፡13/





*የዲያቢሎስ የማታለያ ዘዴ፡-* በቤተክርስቲያን ውስጥ ስንት ሰዎች እያሉ ይህ የመመስከሩ ጉዳይ አንተን ብዙ ሊያስጨንቅህ አይገባም ማለት፡፡

*የእኛ ምላሽ፡-* ለብዙዎች ሲል በመስቀል ላይ የሞተው ክርስቶስ ለእኔም ሞቶልኛል፣ ብዙዎችን ያፈቀረው እኔንም አፍቅሮኛል፣ ብዙዎችን የጠራው እኔንም ጠርቶኛል፣ ለብዙዎች ኃላፊነት የሰጠው ለእኔም ሰጥቶኛል፡፡ እኔ በዙፋኑ ፊት በምቆምበት ጊዜ ሰዎች በእኔ ምትክ ሊቆሙና መልስ ሊሰጡልኝ አይችሉም፡፡ የሠራሁትን ሥራና ያተረፍኩትን መክሊት ይዤ በፊቱ የምቆመው እኔው ራሴ ነኝ፡፡

## 6/ ብዙ ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚመሰክሩ አያውቁም

ብዙ ክርስቲያኖች ወንጌልን የመመስከር ኃላፊነት እንዳለባቸው በሚገባ ያውቃሉ፡፡ መመስከርም ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን ምን ብለው መመስከር ወይም እንዴት መመስከር እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ ኃጢአተኞች በክርስቶስ አዳኝነት በማመን የዘላለምን ሕይወት መውረስ እንዲችሉ፣ በትክክል መተላለፍ ያለበትን የወንጌል መልዕክት ብዙ ክርስቲያኖች ስለማያውቁ፣ አስፈላጊውም ሥልጠና ስለሌላቸው ብዙ ጊዜ፣ "ሄጄ ምን ልበል? የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላንብብ? ምን ብዬ ልጀምር? ወደ ውሳኔስ እንዴት ማምጣት እችላለሁ?" ወዘተ... የሚሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ፡፡

ወንጌልን ለሰዎች ለመናገር በምንሄድበት ጊዜ ምን መናገር እንዳለብን መንፈስ ቅዱስ ሊሰጠን የሚችል ቢሆንም፣ መተላለፍ ያለበትን መልዕክት አውቀን በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለምስክርነት መውጣቱ ፍሬያማ አገልግሎት ለመስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም ምስክርነታችንን በሚከተሉት አራት ሀሳቦች ላይ ተመሥርተን ብናቀርብ የበለጠ ውጤታማ ያደርገናል ብዬ አስባለሁ፡፡

እነዚህም አራት ሀሳቦች የእግዚአብሔር ምህረት የሚያስፈልገው አንድ ኃጢአተኛ ሰው ማወቅ የሚገባው አራት መሠረታዊ የወንጌል መልዕክቶች ሲሆኑ፣ እነርሱም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የገለጠውን አስደናቂ ፍቅር፣ የሰውን ኃጢአተኛነት፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የደህንነት መንገድና ከሰው የሚጠበቀውን ምላሽ ያካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህን አራት መሠረታዊ ሀሳቦች በምስክርነታቸው ወቅት በሚገባ የተጠቀሙ ክርስቲያኖች በቀላሉ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊያመጡ ችለዋል፡፡

## ሀ/ የእግዚአብሔር ፍቅር

እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እንዲሁ ያለምንም ምክንያት ያፈቅራል፡፡ ለእያንዳንዱም ሰው እግዚአብሔር ዓላማ አለው፡፡ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡” /ዮሐ 3፡16/ እግዚአብሔር ሰዎችን ስለወደደ አንድ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በኃጢአተኛ ሰው ምትክ በመስቀል ላይ እንዲሞት አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ በዓለም ላይ እውነተኛ ፍቅር አይገኝም፡፡ ቢገኝም ደግሞ በጥቅም ላይ የተመሠረተ እንጂ ያለ ምንም ምክንያት ወይም በነፃ የሚገለጽ ፍቅር አይደለም፡፡

ይህ ዘመን በዓለማችን ላይ የሰዎች ጥበብና የረቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እጅግ እያደጉ የመጡበት ሲሆን፤ በተቃራኒው ደግሞ ፍቅር፣ የሰብዓዊነት ክብርና እውነተኛነት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እየጠፉ የመጣበት ዘመን ነው፡፡ ሰው በተፈጥሮው ፍቅርን ይፈልጋል፡፡ ይህንንም የሰው ፍላጎት ሊያሟላ የሚችለው በንጹህና በእውነተኛ ፍቅር ሰውን ሁሉ የሚወደው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ማፍቀር ሳይሆን ለሰው የሚያስበውም አሳብ ፍጹምና መልካም ነው፡፡ “ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም፡፡” /ኤር 29፡11/

## ለ/ የሰው ኃጢአተኛነት

እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በፍጹም ፍቅር የሚወድ ቢሆንም ብዙዎች ይህን ፍቅርና እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን መልካም ዓላማና አሳብ የራሳቸው አድርገው፤ ትርጉም፣ ሰላምና እርካታ ያለበትን ሕይወት ለመኖር አልቻሉም፡፡ ይህን መለኮታዊ ፍቅር ሊቀምሱ ያልቻሉት ሰዎች በኃጢአተኛ ባህርያቸው መኖርን ስለመረጡ ነው፡፡ ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት በሚታይበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ንጹህ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ “ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ .... ልዩነት የለምና፣ ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል” በማለት ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ /ሮሜ 3፡ 11,23/





## ሐ/ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው መፍትሄ

የክርስትና ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ እጅግ የተለየ ነው፡፡ ሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የሞከሩባቸውና የሚሞክሩባቸው መንገዶች ሲሆኑ የክርስትና ሃይማኖት ግን ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የሆነውን ሰው ፍለጋ ከሰማይ ወደ ምድር የመጣበትና ሰዎችን ሊያድን የራሱን እርምጃ የወሰደበት መንገድ ነው፡፡ ሰዎች በራሳቸው ጥረት የእግዚአብሔርን ክብር ሊያገኙ እንዳልቻሉ እግዚአብሔር በማየቱ በኃጢአተኛው ሰው ምትክ እንዲሞትና ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያስታርቅ አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስም ሞትና ትንሣኤ ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው የጥል ግድግዳ ፈረሰ፣ የኃጢአት ደመወዝ የሆነውም ሞት ተሸነፈ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ሰዎች ጽድቅን እንዲያገኙ ሆነ፡፡ “ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፡፡” /ሮሜ 3፡23-24/

“የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው፡፡” /ሮሜ 6፡23/ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነሳ፣ ክርስቶስ የሰውን የኃጢአት ዕዳ ሙሉ በሙሉ ስለከፈለ ጽድቅ በጸጋ፣ የዘላለምም ሕይወት በክርስቶስ ብቻ የሚገኝ ሆነ፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው እርሱ ኃጢአተኛ ስለሆነ አልነበረም፣ ነገር ግን ኃጢአተኛ የሆነውን ሰው ለማዳንና ለማጽደቅ ነው፡፡ “ክርስቶስ ታዲያ መከራ የተቀበለው ኃጢአት ሠርቶ፣ በደል ፈጽሞ አይደለም፡፡ እርሱ ግን እኛን ለማዳንና ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን፣ አንድ ጊዜ ለሁላችን ኃጢአት ሞተ፡፡ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ተመልሶ ሕያው ሆነ፡፡” /1ጴጥ. 3፡18፣ ሕያው ቃል፡፡/

ከዚህም የተነሣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚገቡበት መንገዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ሆነ፡፡ ምክንያቱም ከክርስቶስ በቀር ሌላ ማንም ለሰዎች ኃጢአት አልሞተም፤ እንዲሁም ከክርስቶስ በቀር ሌላ ማንም ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ የለም፡፡

ስለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ "በሩ እኔ ነኝ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል፡፡" /ዮሐ. 10፡9/ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር (በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር) ማንም ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡" /ዮሐ. 14፡6/ በማለት ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት መንገዱ በእርሱ በኩል ብቻ መሆኑን የገለጸው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአተኞችን ዕዳ ለመክፈል ነፍሱን ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ብቸኛ አስታራቂ፣ ብቸኛ መንገድ ሆኗል፡፡ "አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል እርቅን ማስገኘት የሚችልም አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቶስ ሕይወቱን ለሰዎች ሁሉ ኃጢአት ቤዛ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን እንደሚፈልግ በተገቢው ወቅት የታወጀ ማረጋገጫ ነው፡፡" /1ጢሞ. 2፡5-6፣ ሕያው ቃል፡፡/

## መ. እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን የደህንነት መንገድ ሰዎች በግላቸው መቀበል አለባቸው

ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆነና እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአተኞችን ለማዳን ያዘጋጀውን የደህንነት መንገድ ተመልክተናል፡፡ ሰው ይህንን የተዘጋጀለትን የደህንነት መንገድ ለራሱ መምረጥ አለበት፡፡ አንድ በሽተኛ ሰው ከሐኪም የታዘዘለትን መድኃኒት በታዘዘው ሁኔታ እራሱ ካልወሰደ ከበሽታው ሊድን እንደማይችል ሁሉ አንድ ኃጢአተኛም ከኃጢአቱ በሽታ ለመዳንና የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ እንዲችል ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘለትን መድኃኒት ጌታ ኢየሱስን በግል ሕይወቱ መድኃኒቱና ጌታው አድርጎ ለመቀበል መወሰንና መምረጥ አለበት፡፡ "ለተቀበሉት፣ ማለትም በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ ግን፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡" /ዮሐ. 1፡12፣ ሕያው ቃል፡፡/

ይህን መድኃኒት ወደውና ፈቅደው ለተቀበሉት ሁሉ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወትና የልጅነትን ሥልጣን ሰጣቸው፡፡ ስለዚህም ደህንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንጂ በራሳችን ጽድቅ አይደለም፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስን በማመናችሁ በጸጋው ድናችኋል፤ ይህም እናንተ በራሳችሁ ያገኛችሁት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ መዳን ለምናደርገው መልካም ተግባር የሚሰጥ ዋጋ አይደለም፡፡ ማንም ሰው 'ደህንነትን ያገኘሁት በበጎ ሥራዬ ነው' ሊል አይገባም፡፡" /ኤፌ. 2፡8-9፣ ሕያው ቃል፡፡/





ስለዚህም ሰው ይህን የዘላለምን ደህንነት ከእግዚአብሔር ለማግኘት በራሱ መወሰን አለበት፡፡ በኃጢአቱ ምክንያት በመስቀል ላይ የሞተለትን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መምረጥ አለበት፡፡ ሕይወት የግል እንደመሆኑም መጠን ለማንም ሰው ቢሆን አባቱ ወይም እናቱ ወይም ጓደኛው ሊወስንለት አይችልም፡፡ ይህም ማለት እኔ ከበሽታዬ እንድፈወስ በሐኪም የታዘዘልኝን መድኃኒት አንተ ዋጥልኝ እንደ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው በምድር ላይ ለኖረበት ኑሮ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ስለሆነ ዛሬ ምርጫውን ማድረግና በምርጫው መኖር የራሱ የሰውዬው ብቻ ውሳኔ ነው፡፡

ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ይህን ውሳኔ ማድረግ እንዲችል ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚህ በማለት ይጋብዛል፡፡ "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፣ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ፣ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፣ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል፡፡" /ራዕ. 3፡20/

ፈቃደኛ ሆኖ የልቡን በር ከፍቶ ኢየሱስን ወደ ሕይወቱ ለመጋበዝ ለሚፈልግ ሁሉ ኢየሱስ ወደ ሕይወቱ ለመምጣት ይፈልጋል፡፡ አንተም ከዚህ በፊት በራስህ ውሳኔ ኢየሱስን የሕይወትህ ጌታና አዳኝ እንዲሆን ወደ ሕይወትህ ካልጋበዝከው አሁን ይህን ውሳኔ ማድረግ ትችላለህ፡፡ ምናልባት በክርስቲያን ቤተሰብ አድገህ ወይም ደግሞ ብርቱ አገልጋይ ልትሆንም ትችላለህ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወትህ እንዲመጣና የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጥህ በራስህ ውሳኔ አድርገህ አታውቅም ይሆናል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወትህ እንዲመጣ አሁን ልትጋብዘው ትችላለህ፡፡ "ጌታ ሆይ የልቤን በር ከፍቼ አንተን ለመቀበል የግል ውሳኔ አደርጋለሁ፡፡ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፣ የሕይወቴ አዳኝና ጌታ እንድትሆን እፈቅዳለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ሕይወቴን ለአንተ እሰጣለሁ" በማለት አጭር የእምነት ጸሎት በመጸለይ ኢየሱስን ወደ ሕይወትህ ጋብዘው፡፡ አንተም ለሌሎች ሰዎች ወንጌልን በምትመሰክርበት ጊዜ ሁሉ ሰዎችን ወደዚህ የግል ውሳኔ ማድረስ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዘብ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ወንጌልና የወንጌል በረከቶች

ብዙ ክርስቲያኖች የምሥራቹን ወንጌል ለሌሎች መናገር ካልቻሉባቸው ምክንያቶች አንዱ ስለራሳቸው የሕይወት ደህንነትና ክርስቲያን በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ስለተቀበሉት ነገር እርግጠኛ አለመሆን እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን ክርስቲያን ሁሉ በትክክል በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ክርስቲያን ከሆነ፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል ደግሞ ስለ ደህንነቱ እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡ ስለ ደህንነቱ እርግጠኛ ያልሆነ ክርስቲያን ለሌሎች የምሥራች ብሎ ወንጌልን የመመስከር ትርጉሙ አይገባውም፡፡ ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደህንነት የሚሰጠውን ማረጋገጫ በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ ሥፍራ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ በዓለም ላይ ራሳቸውን ክርስቲያን ነን ብለው የሚጠሩ ሁሉ ለሌሎች ወንጌልን ቢመሰክሩላቸው ኖሮ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚደርሰው ድርሻ ስድስት ሰው ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ ያህል እያንዳንዱ ክርስቲያን በወር ለአንድ ሰው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ቢመሰክር ከስድስት ወር በኋላ ለዓለም ሁሉ ተመሰከረለት ማለት ነው፡፡ ነገር ግን እውነቱ ሲታይ እንደዚህ ሳይሆን፣ ቤተክርስቲያን ወንጌልን ክርስቶስ ለሞተላቸው ሰዎች ማድረስ እንዳቃታት እነሆ ሁለት ሺ ዓመታት አስቆጥረናል፡፡

አሁንም ኃላፊነታችንን አውቀን በታማኝነት የምሥራቹን ወንጌል ካልተናገርን፣ በየቀኑ በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔር እየተለዩ ለሰይጣን ወደተዘጋጀው የሥቃይ ሥፍራ ይገባሉ፡፡ ለዚህ ሁሉ ምክንያቶቹ ክርስቲያኑ ኃላፊነቱን መዘንጋቱ፣ በወንጌል ያገኛቸውን በረከቶች እንደ ቀላል ነገር መቁጠሩና የዘላለምን ሕይወት ማግኘት ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆነ በትክክል ያለማወቁ ናቸው፡፡

ስለዚህም አንድ ሰው ወንጌልን ሲቀበል በሕይወቱ የሚያገኛቸው በረከቶች ምን እንደሆኑ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ፡፡ ለመሆኑ መዳንን አግኝተናል ስንል ምን ማለታችን

ነው? አንድ ሰው በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት የሚያገኛቸው በረከቶችስ ምንድር ናቸው? አንድ ክርስቲያን የዘላለምን ሕይወት የሚያገኘውስ መቼ ነው? መጽሐፍ ቅዱስስ ስለ ደህንነት ማረጋገጫ ምን ይላል? ክርስቶስን ተቀብለናል ስንል ምን ማለታችን ነው? አንድ ሰው ክርስቶስን ከተቀበለበት ቅጽበት ጀምሮ በሕይወቱ የሚፈጸሙ ነገሮች ምንድር ናቸው?

## 1. እጅግ ልዩ የሆነውን ክርስትና መኖር ጀምረናል

በዓለም ላይ ያሉ ሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ሰው በራሱ ጥረት፣ በመልካም ሥራው፣ ደግ በመሆን፣ በራሱ ጥበብ ወይም ራሱ በፈጠራቸው መንገዶች ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የሞከረበት መንገድ ነው፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ ሰው በገዛ ጥረቱ ወደ እግዚአብሔር ክብር ለመድረስ ከቶ አልቻለም፡፡ ክርስትና ግን ሰው በራሱ ጥረት ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ ስላልቻለ እግዚአብሔር ከክብር ሥፍራው ሰውን ለማዳን የወረደበት መንገድ ነው፡፡ ይህም ማለት ባጭሩ ሌሎች ሃይማኖቶች ሰው እግዚአብሔርን ለማግኘት ከምድር ወደ ሰማይ ለመጓዝ የሞከረበት ሲሆን ክርስትና ግን እግዚአብሔር ሰውን ለማግኘት ከሰማይ ወደ ምድር የወረደበት ነው፡፡

"የሰው ልጅ (ክርስቶስ) የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" /ሉቃ. 19፡10/፡፡ ስለዚህ ሰው የዘላለምን ሕይወት የሚያገኘው በራሱ ጥረት ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ በመሞከር ሳይሆን፣ ጠፍቶ ሳለ ሊፈልገው ለመጣው ለእግዚአብሔር ራሱን በመስጠት ብቻ ነው፡፡ ሰው ተቅበዝብዞ ሳለ እግዚአብሔር ሊፈልገው፣ ሊሰበስበውና ከራሱ ጋር ሊያስታርቀው አንድ ልጁን ሰጠ፡፡ "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፣ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፣ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" /ኢሳ 53፡6/፡፡

እኛ በራሳችን ጥረትና ብዙ አስፈላጊ ያልሆነ ዋጋ በመክፈል ደህንነትን ልናገኝ ከቶ አንችልም፡፡ ነገር ግን አስፈላጊውን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ እኛን በጸጋው ብቻ ሊያድነን የመጣውን እግዚአብሔርን በማመስገን ሕይወታችንን ለእርሱ ካስገዛን የዘላለምን ሕይወት እናገኛለን፡፡ ክርስቶስን ወደ ሕይወታችን የተቀበልን እንደሆነ ይህን





ልዩ የሆነውን የክርስትናን ሕይወት መኖር ጀምረናል ማለት ነው፡፡ የክርስትና ሕይወት የደስታ፣ የሰላም፣ የእረፍት፣ የእርካታ ሕይወት ነው፡፡ ክርስቶስን በሕይወታቸው የተቀበሉ ሁሉ ይህን ልዩ የሆነውን የእረፍትና የእርካታ ሕይወት ይኖራሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሕይወት በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ ወይም በሌላ ዘዴ የሚገኝ ሳይሆን ክርስቶስን ለማመን በሚደረግ ምርጫ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡

## 2. የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቶናል

አንድ ሰው ለኃጢአቱ የሞተለትን ክርስቶስን የሕይወቱ አዳኝ አድርጎ ለመቀበል እንደወሰነ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ሥልጣን ወይም መብት ያገኛል፡፡ የዘላለምን ሕይወት አግኝተው በእግዚአብሔር መንግስት ለዘላለም ከሚኖሩ ጋር ቤተሰብ ሆኖ በእግዚአብሔር መንግስት ተወለደ ማለት ነው፡፡ "ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር፡፡ በዓለም ነበረ፣ ዓለሙም አላወቀውም፡፡ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡፡ ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" /ዮሐ. 1፡9-13/፡፡

በእነርሱ ምትክ በመስቀል ላይ የሞተውን ክርስቶስን በእምነት ለሚቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ እኔ ይህን ስጽፍ በዚህ ሰዓት የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኔ፣ በእርሱ ቤተሰብ ስለመወለዴና የዘላለምን ሕይወት ስለማግኘቴ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ የሚናገረውን በሙሉ አምናለሁ፡፡ እግዚአብሔር 'ልጄን ክርስቶስን በእምነት ከተቀበልክ የእኔ ልጅ የመሆን መብት አለህ' ሲለኝ ካላመንኩት እግዚአብሔርን ሐሰተኛ ማድረጌ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እውነተኛ ነው፡፡ ለዘላለም መንግስትም በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ እንድንወለድ ፈቃዱ እንደሆነ ገልጦልናል፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔርን ቃል ማመን አለብን፡፡

## 3. የዘላለምን ሕይወት አሁን አግኝተናል

ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ የዘላለምን ሕይወት ስለማግኘታቸው እርግጠኞች አይደሉም፡፡ ወደፊት ወደ እግዚአብሔር ፊት ስደርስ አውቃለሁ፣ መዳኔንና ኣለመዳኔን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው ይላሉ፡፡ መጽሐፍ

ቅዱስ ግን አንድ ክርስቲያን ክርስቶስን የግል ሕይወቱ አዳኝና ጌታ አድርጎ በልቡ አምኖና በአፉ መስክሮ ከተቀበለበት ቅጽበት ጀምሮ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኘ ያረጋግጣል፡፡ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፡- ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም” /ዮሐ. 5፡24/

ክርስቲያን የሚለው ስም የሚገኘው በክርስቲያን ቤተሰብ ተወልዶ በማደግ፣ ቤተክርስቲያን ዘወትር በመመላለስ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ልጅ በመሆን፣ ብዙ መልካም ሥራዎችን በመሥራት፣ ከሌሎቹ ሃይማኖቶች ሁሉ የተሻለ ሃይማኖት ተከታይ በመሆን ወይም በጾምና በጸሎት አይደለም፡፡ እነዚህ ሁሉ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ቢሆኑም ክርስቲያን ማለት ግን ክርስቶስን የተቀበለ፣ ያመነ፣ ክርስቶስ በሕይወቱና በልቡ ውስጥ ያደረ የክርስቶስ ተከታይና ክርስቶስን የሚመስል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው ክርስትናው ትክክለኛ ከሆነና ክርስቶስን የተከተለው በራሱ ወስኖ፣ በእውነተኛ ልቡ ከሆነ፣ የትንሣኤው ጌታ የሆነው ክርስቶስ ወደ ሕይወቱ ስለገባ፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ክርስቶስን ለማመን ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ከሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ተሻግሯል፡፡ “እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና” /ሮሜ 8፡1-2/

እኔ የዘላለም ሕይወት አሁን አለኝ፣ አሁን ብሞት ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደምገባ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ ብዬ ስናገር የሰሙ ሰዎች ተናደው ለምን በራስህ ትመጻደቃለህ ብለው ተናግረውኝ አውቃለሁ፡፡ እኔ ግን ጽድቄ ክርስቶስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚያረጋግጥልኝ በቃሉ እታመናለሁ፣ በቃሉ እመካለሁ፡፡ እኔ ኃጢአተኛ መሆኔን አውቄ እግዚአብሔር ከኃጢአት ሊያድነኝ ያዘጋጀልኝን መድኃኒት ለራሴ ስለተቀበልኩ ከኃጢአትና ከሞት ድኛለሁ፡፡

እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገር “ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና፡፡” (ሮሜ. 10፡9-10) በማለት ጽድቅና መዳን እንዴት እንደሚገኙ መንገዱን ያሳያል፡፡ እኔም ስለ ደህንነቴ እርግጠኛ





እንድሆን ያደረገኝ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ኢየሱስ ጌታ ነው፣ እግዚአብሔርም ከሙታን አስነስቶታል ብዬ በልቤ ስላመንኩ ጽድቅን አግኝቻለሁ፤ የኢየሱስንም ጌትነት በአፌ ስለመሰከርኩ ድኛለሁ፡፡

የአባቴ እምነትና በክርስቲያን ቤተሰብ መወለዴ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል ያለ እምነት ደጋግሜ ማንበቤ እንደማያድነኝ ገባኝ፡፡ ስለዚህም ራሴ ለማመን፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመወለድና የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ብቻ ሳይሆን ያነበብኩትን ቃል ለማመንና ለመታዘዝ ወሰንኩኝ፡፡ ይህን ውሳኔ ካደረግኩ በኋላ መላ ሕይወቴ ተለወጠ፡፡ ክርስቲያን ሆንኩ፣ የዘላለምንም ሕይወት አገኘሁ፡፡ የዘላለም ሕይወት እንዳገኘሁም እግዚአብሔር ራሱ ከተናገረው ቃል ብዙ ማረጋገጫ አገኘሁ፡፡

“እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው፡፡ ልጁ ያለው ሕይወት አለው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ” /ዮሐ.5፡11-133/፡፡ ይህ ቃል እንደሚያረጋግጠው እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶናል፣ ይህም ሕይወት የሚገኘው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት የተቀበሉ ወይም ልጁ በሕይወታቸው ያላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት አግኝተዋል፡፡ ይህም የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው ከሞትን በኋላ ሳይሆን ጌታን ከተቀበልንበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ አንተ ክርስቲያን ሆነህ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ እርግጠኛ ካልሆንክ አሁን እርግጠኛ መሆን ትችላለህ፡፡ ደግሞም እርግጠኛ መሆን አለብህ፡፡

የክርስትና ጉዞ የጨለማ ጉዞ ሳይሆን ቃሉን ተረድተህና አምነህ በብርሃን የምታደርገው ጉዞ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ እርግጠኛ ለመሆን በመጀመሪያ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በራስህ ውሳኔ በሚገባ ገብቶህና ተረድተህ የሕይወትህ ንጉስና አዳኝ አድርገህ መቀበልህን ክርስቶስም በአሁን ሰዓት በልብህ ዙፋን ላይ መቀመጡንና ሕይወትህን የሚቆጣጠረው እርሱ መሆኑን እርግጠኛ ሁን፡፡ ይህንን እርግጠኛ ካልሆንክ ጌታን በራስህ ውሳኔ አሁን መቀበል ትችላለህ፡፡

ደህንነትህን ለማረጋገጥ ቀጥሎ የምታደርገው ነገር ቢኖር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወትህ ካለ እግዚአብሔር በተናገረው ቃል መሠረት የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠህ እርግጠኛ ሁን፡፡ በምድር ላይ እያለህ የዘላለምን ሕይወት መኖር እንደ ጀመርክና አሁን እንኳ ብትሞት ወይም ጌታ የሆነው ክርስቶስ ዳግመኛ ቢመጣ ወደ ዘላለም መንግስት እንደምትገባ እርግጠኛ ሁን፡፡ የዘላለምንም ሕይወት የሰጠህን እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡

የዘላለም ሕይወት እንዳለህ እርግጠኛ ከሆንክ በኋላ የዘላለምን ሕይወት ሳያገኙ ወደ ዘላለም ጥፋትና ሥቃይ ለሚሄዱ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ለእነርሱም የዘላለምን ሕይወት ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን የመናገር የወንጌል አደራ አለብህ፡፡ በተጨማሪም ክርስቲያን ነን እያሉ ስለ ደህንነታቸው እርግጠኛ ላልሆኑ ሁሉ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው እንዲያውቁ የመርዳት ኃላፊነት አለብህ፡፡

የዘላለምን ሕይወት እንዳገኘን እርግጠኛ ያልሆንን ሰዎች ስለ ዘላለም ሕይወት በትክክል መናገር፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የሰጠንን የወንጌል አደራ በትክክል መወጣት ስለማንችል፤ በመጀመሪያ እኛ ራሳችን የዘላለም ሕይወት እንዳገኘን ልናረጋግጥና የደህንነትን ትርጉምና ጣዕም ልናውቅ ይገባል፡፡

## 4. በክርስቶስ አዳዲስ ፍጥረታት ሆነናል

በወንጌል ደህንነትን አግኝተናል ስንል ከክርስቶስ ጋር ከመገናኘታችን በፊት እንኖር ከነበረው ከርኩስና ከጨለማ ሕይወት ተለይተናል ማለታችን ነው፡፡ ወንጌል በሕይወታችን የሚታይ ለውጥ ማምጣት አለበት፡፡ ስለዚህም ደግሞ የሕይወታችንን ለውጥ በሚገባ መመስከር መቻል አለብን፡፡ በወንጌል ስብከቱ ትልቅ ምሳሌያችን የሚሆነልን ሐዋሪያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ የስብከቱ መልዕክት እንዴት በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆኑን ለሰዎች መመስከር ነበር፡፡ ክርስቶስን ከማመኑ በፊትና ካመነ በኋላ ባለው ሕይወቱ መካከል ያለውን ልዩነት ማሳየት ነበር ዋና መልዕክቱ፡፡

በክርስቶስ መዳንን ከተቀበሉ በኋላ እንዳልተቀበሉ ዓይነት ሆነው የክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች በተግባር በማያሳይ ሕይወት ውስጥ ይመላለሱ ለነበሩ የቆሮንቶስ ምዕመናን መዳንን መቀበል ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆነ "ማንም ሰው በክርስቶስ ሲያምን አዲስ





ፍጥረት ይሆናል፡፡ አሮጌው ሕይወት አልፎ ሁሉም ነገር ታድሷልና፡፡" /2ቆሮ. 5፡17፣ ሕያው ቃል/ በማለት ጽፎላቸዋል፡፡

መዳንን መቀበል ማለት መታደስ ወይም ከሰው ልጅ ውድቀት በፊት ወደነበረው ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ህብረት መመለስ፣ አሮጌውን ሕይወትና አዳማዊ ባህርይን መጣል ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ አዲስ ሕይወትን የሰጠን እኛን በዘላለም ፍቅሩ ስለወደደን እንጂ እኛ መልካም ሰዎች ሆነን አይደለም፡፡ እግዚአብሔርም አዲስ ሕይወት የሰጠን፣ አዲስ ሕይወትን ላላገኙ ሁሉ ምስክሮች እንድንሆን ነው፡፡

እግዚአብሔር ይህን አዲስ ሕይወት እንዴትና ለምን ለእኛ እንደሰጠን ሐዋሪያው ጳውሎስ ግልጽ አድርጎ እንደሚከተለው ጽፎልናል፡፡ "ይህም ሁሉ የሆነው (ሕይወታችን የታደሰው) ጠላቶቹ የነበርነውን እኛን፣ በክርስቶስ ወዳጆቹ ባደረገን በእግዚአብሔር ነው፡፡ ሌሎችም ሰዎች እንደ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁና ወዳጆቹ እንዲሆኑ የማስታረቅን አገልግሎት ለእኛ ሰጥቷል፡፡ ይህንን የማስታረቅን አገልግሎት አደራ ስለተቀበልንም፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ ሰዎችን ሁሉ ወዳጆቹ እንደሚያደርጋቸውና በደላቸውን እንደማይቆጥርባቸው እንሰብካለን፡፡" (2ቆሮ. 5፡18-19፣ ሕያው ቃል፡፡)

በዚህም መሠረት ከእኛ የሚጠበቁ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንዳሉ እንመለከታለን፡፡ የመጀመሪያው ነገር ክርስቶስን በእምነት ወደ ሕይወታችን ከጋበዝንበት ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ በሕይወታችን ስለሚኖር ከእግዚአብሔር ዘንድ አዲስ ሕይወትን ተቀብለናል፡፡ የቀደመው ሕይወታችን በተለወጠ፣ በታደሰና ክርስቶስን ሊመስል በሚገባው ሕይወት ተቀይሯል፡፡ ይህንን እውነት በትክክል መረዳትና በጊዜውም አለጊዜውም በዚህ እውነት ላይ ጸንቶ መቆም ያስፈልጋል፡፡ ሁለተኛው ከእኛ የሚጠበቀው ነገር ደግሞ ሕይወታችን በክርስቶስ መለወጡን ያመንን ከሆንን በሕይወታችን ያየነውን ለውጥ፣ እግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር፣ ጠላቶቹ ሳለን ከእርሱ ጋር እንዴት እንዳስታረቀን ይህን አዲስ ሕይወት ገና ላላገኙ ሁሉ መስካሪዎች እንድንሆን ነው፡፡

እኛም ከክርስቶስ ሐዋሪያት ጋር "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፡፡ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፣ ከአብ ዘንድ የነበረውን ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፡፡"

(1ዮሐ. 1፡1-2) እንድንል ይጠበቃል፡፡ ይህንንም እንድንመሰክር፣ ያየነውንና የቀመስነውን እንድንናገር ተጠርተናል፡፡ አይተን እንዳላየን፣ ቀምሰን እንዳልቀመስን፣ ተደርጎልን እንዳልተደረገልን፣ ተገልጦልን እንዳልተገለጠልን ሆነን ልንኖር አልተጠራንም፤ ልንኖርም አንችልም፡፡ አዳዲስ ፍጥረታት ሆነናል፣ የሌሎችንም ሕይወት የሚያድሰውን የምሥራቹን ወንጌል ለመናገር ተጠርተናል፡፡

## 5. የእግዚአብሔር ንብረት ሆነናል

ሕይወታችን በክርስቶስ ከተለወጠበት ጊዜ ጀምሮ እኛ የራሳችን ሳንሆን የእግዚአብሔር ንብረት ሆነናል፡፡ እግዚአብሔር ውድ የሆነ ዋጋ ከፍሎ የራሱ ገንዘብ አድርጎናል፡፡ "ከአባቶቻችሁ ከተማራችሁት ከንቱ የሕይወት ጉዳና እግዚአብሔር መልሶ ያዳናችሁ ዋጋ ከፍሎ ነው፡፡ የተከፈለላችሁም ዋጋ፣ እንደምታውቁት የሚጠፉ ብር ወይም ወርቅ ሳይሆን፣ የኃጢአት እድፍና ጉድፍ ያላረፈበት የእግዚአብሔር በግ የሆነው የክርስቶስ ክቡር ደም ነው፡፡ ይህንንም የማዳን ተግባሩን እንዲያከናውን (ክርስቶስ) የተመረጠው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሲሆን በዚህ በመጨረሻው ዘመን ግን ስለ እናንተ ተገልጧል፡፡" (1ጴጥ. 1፡18-19፣ ሕያው ቃል፡፡)

እግዚአብሔር እኛን ለራሱ የገዛን በክርስቶስ ክቡር ደም ነው፡፡ እኛ በክርስቶስ መዳንን ከተቀበልን በኋላ የራሳችን እንዳልሆንን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ የገዛን በዓላማ ነው፡፡ የክብር እቃ እንድንሆን፣ እግዚአብሔር በሚሠራበት ዘመን ገንዘቡ አድርጐ ሊጠቀመን ፈልጎ ነው፡፡ "እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የእኔ ገንዘብ ይሆናሉ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡" (ሚል. 3፡17) እኛ በክርስቶስ መዳንን አግኝተናል፣ መዳን ያገኘነው እንድንቀመጥ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲጠቀምብንና እንዲሠራብን፣ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ለማቅረብና የእርሱ ምስክሮች ለመሆን ነው፡፡

## 6. የኃጢአት ይቅርታን አግኝተናል

ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው በደለኛ የሆነውን ሰው የበደሉን ዋጋ በሞቱና በደሙ ከፍሎ ከእግዚአብሔር ለማስታረቅ ነው፡፡ የሰውን ውድቀት፣ ዓመጽና ኃጢአት በሙሉ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሸከሙ ምክንያት ሰው ከወደቀበት የሚነሳበት፣ ከኃጢአቱ የሚነጻበት መንገድ ክርስቶስ ብቻ ሆነ፡፡ ስለዚህ ሰው





ክርስቶስን በሚያምንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የኃጢአትን ይቅርታ ይቀበላል፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውም የጥል ግድግዳ ይፈርሳል፡፡ እኛም ክርስቶስን ተቀብለናል ስንል፣ እግዚአብሔር የቀደመውን ኃጢአታችንን በሙሉ ይቅር ብሏል ማለታችን ነው፡፡ (ቆላ. 1፡13-14፣ 2፡13-15 ተመልከት፡፡)

ስለዚህ መዳንንና የኃጢአት ይቅርታን ያገኙ ሁሉ፣ ወንጌል የሚያስገኘውን በረከት በሕይወታቸው የቀመሱ ሁሉ፣ ስላገኙት መዳንና ዘላለማዊ በረከት ይመሰክራሉ፣ ላገኙት ሰው ሁሉ ይናገራሉ፣ የትም ሥፍራ ቢሆን በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ይናገራሉ፡፡ አንተም በወንጌል ምክንያት ከእግዚአብሔር የተቀበልካቸው መንፈሳዊና ሥጋዊ በረከቶች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ እጅግ ልዩ የሆነ ዕረፍትና እርካታ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን፣ የዘላለም ሕይወት፣ በወንጌል ምክንያት ያገኘሃቸው ታላላቅ በረከቶች ናቸው፡፡

እነዚህንና ሌሎችንም በሕይወትህ ያየሃቸውን በረከቶች ለሌሎች ሳትመሰክር ዝም ማለት እግዚአብሔርን መበደል ነው፣ የምስጋናንም ሕይወት ማጣት ነው፡፡ ስለ መዳንህና እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገር ሁሉ ለሌሎች መመስከር ይጠበቅብሃል፡፡ ስለ መዳናችን በምንመሰክርበት ጊዜ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ያጋጥሙናል፣ ለእነዚህ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች እንዴት መመስከር እንደምንችል በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

## ምዕራፍ አምስት

# ለተለያዩ ዓይነት ሰዎች ወንጌልን መመስከር

ወንጌልን ለመመስከር በምንወጣበት ጊዜ የተለያየ ጥያቄ፣ፍላጎትና አመለካከት ያላቸው ሰዎች ያጋጥሙናል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ሰዎች መልስ ለመስጠት የተዘጋጀን መሆን ያስፈልገናል፡፡ ዝግጅታችን ደግሞ ለመከራከርና በክርክርም ለማሸነፍ ሳይሆን ለሰዎች እውነቱን አሳይተን ወደ እውነት ለማምጣት መሆን አለበት፡፡ የሰዎች ጥያቄና አመለካከታቸው እጅግ ብዙ ስለሆነ ሁሉንም ዓይነት በዚህ ሰፍራ ለመዘርዘር ባይቻልም እጅግ ጎልተው የሚወጡትን ብቻ በመጥቀስ ለጥያቄዎቻቸው ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ለማስገንዘብ የተወሰኑትን ከዚህ በታች አቅርቤአለሁ፡፡

## 1/ ለመሆኑ ኃጢአት ምንድር ነው? የሚሉ

ኃጢአት ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መጣስ ነው፡፡ "የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች ተለይተው የሚታወቁት እነሆ በዚህ ነው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም፡፡" /1ዮሐ. 3፡10፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡ ኃጢአት ማለት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ እንዲሞት በላከው በልጁ አለማመን ነው /ዮሐ. 16፡8-9/፡፡ ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው /1ዮሐ. 5፡17/ መልካምን ማድረግ እያወቀ የማያደርግ ሰው ያን መልካም ነገር አለማድረጉ ኃጢአት ነው /ያዕ. 4፡17/፡፡

## 2/ እግዚአብሔር መልካም አምላክ ከሆነ በዓለም ላይ ለምን ተንኮልና ክፋት እንዲኖር ፈቀደ? የሚሉ

እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለሆነ ለሰዎች የምርጫ ነፃነትን ሰጥቷል፡፡ "በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን

እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን አስመሰክራለሁ። እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጡ።" /ዘዳ. 30፡19/ እግዚአብሔር ለሰዎች ከሕይወትና ከሞት እንዲመርጡ ነፃነትን ከሰጣቸው በኋላ መልካም አምላክ በመሆኑ ለሰዎች የሚበጀውን በማሳየት "ሕይወትን ምረጡ" ብሎ ይመክረናል። ክፋት፣ ተንኮል፣ ወንጀልና ኃጢአት የመነጨው ከሰው እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም። (ዘፍ. 3፡17-19 ተመልከት።) እግዚአብሔርማ መልካምና ቸር አምላክ በመሆኑ እኛ ገና ኃጢአተኞች ሆነን ሳለን ፍቅሩን ገልጾልናል። ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢአት እንዲሞት በመስጠቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ያስረዳናል። /ሮሜ. 5፡8 ፣ 8፡32/

## 3/ የእኔ ኃጢአት በጣም ትንሽ ስለሆነ ብዙ አያስጨንቀኝም የሚሉ

የኃጢአት ትንሽና ትልቅ የለውም። ማንኛውም ኃጢአት ሰውን ያስጨንቃል፣ የህሊናን ወቀሳ ያስከትላል። "ኃጢአተኞች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር" /ኢሳ. 48፡22/። ማንኛውም ኃጢአት ሰውን ያዋርዳል፣ ሰውን ባሪያ ያደርጋል /ዮሐ. 8፡34/። ማንኛውም ኃጢአት ሰውን ወደ ሞት ይመራል /ሮሜ. 6፡23/። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ኃጢአት ይላል እንጂ ትንሽ ኃጢአት ወይም ትልቅ ኃጢአት ብሎ አያውቅም። ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ህብረት ይለያል፣ የእግዚአብሔርም ክብር እንዳይኖረው ያደርጋል /1ቆሮ. 6፡9-10/።

## 4/ እኔ ኃጢአተኛ አይደለሁም እንደ አንተም ያለሁ ንጹህ ሰው ነኝ የሚሉ

ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሚከተለውን ምላሽ መስጠት ያሉበትን ሁኔታ በትክክል እንዲረዱትና ወደ እውነት እንዲመጡ ሊረዳቸው ይችላል። ትክክል ነህ እንደ እኔም ንጹህ ሰው ነህ፣ ምናልባትም ከእኔም ትሻል ይሆናል፤ ነገር ግን አንድ እውነት ማወቅ አለብህ፤ አንድ ሰው አንድን ሰው ከገደለ ነፍሰ ገዳይ ይባላል፣ አንድን ነገር ሲዋሽ ከተገኘም ውሸታም ይባላል። እንዲሁም አንድን ኃጢአት የሠራም ኃጢአተኛ ይባላል /ያዕ. 2፡10 ፣ ሮሜ. 3፡10,23 ፣ 6፡23/። እኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ





ደህንነትን ያገኘሁት ከአንተ የተሻልኩ ሰው ሆኜ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምህረትና ይቅርታ ስለተቀበልኩና ክርስቶስን ስላመንኩ ነው። አንተስ እኔ ያደረግሁትን አታደርግም? ለኃጢአትህ ይቅርታ ክርስቶስን አትቀበልም?

## 5/ በፍጹም ከኃጢአቴ ልላቀቅ አልችልም የሚሉ

በክርስቶስ አምኖ ደህንነትን ማግኘት በሞትና በሕይወት መካከል የሚደረግ ምርጫ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር "ነገር ግን ንስሃ ባትገቡ ሁላችሁ ትጠፋላችሁ" ይላል /ሉቃ. 13፡3/። "ሥጋውን ለማስደሰት የሚዘራ ከሥጋው ሞትን ያጭዳል፣ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳልና" /ገላ. 6፡8/

ከኃጢአቴ ወይም ካለብኝ ሱስ መላቀቅ አልችልም ወይም አልፈልግም በማለት በምድር ላይ እያሉ ሕይወትን ለመምረጥ የተሰጣቸውን እድል ችላ ብለው የሚያሳልፉ ሁሉ መጨረሻቸውና መድረሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። "ነገር ግን ፈሪዎች፣ እምነተ ቢሶች፣ ርኩሶች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ አመንዝሮች፣ አስማተኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ውሸታሞች ሁሉ ዕጣ ክፍላቸው በዲን በሚቃጠለው በእሳት ባህር ውስጥ ይሆናል። ይህም ሁለተኛው ሞት ነው።" /ራዕ. 21፡8፣ አዲሱ ትርጉም።/

ማንም ሰው በራሱ ኃይል ከኃጢአትና ከመጥፎ ልማድ ሊላቀቅ አይችልም። ነገር ግን ሰውን ከማንኛውም ኃይል ነፃ ሊያወጣ የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ሰው በራሱ ኃይል ነፃ ለመውጣት እንደማይችል ጌታ ኢየሱስ "ስለዚህ ወልድ ነፃ ካወጣችሁ በእርግጥም ነፃ ትሆናላችሁ" /ዮሐ. 8፡36፣ ሕያው ቃል/ በማለት ሰውን ነፃ ማውጣት የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ አረጋግጧል። ሐዋሪያው ጳውሎስም እንዲሁ "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።" /ፊል. 4፡13/ በማለት የኃይልና የጉልበት ሁሉ ምንጭ ክርስቶስ መሆኑን ይመሰክራል።

## 6/ የእኔ ኃጢአት እጅግ ብዙ ነው የሚሉ

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ማንኛውንም ዓይነት ኃጢአተኛ ለማዳን ነው። ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ

ሲገልጽ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጣ" አለ እንጂ "ኃጢአታቸው አነስተኛ የሆኑትን ለማዳን መጣሁ" አላለም። /ሉቃ. 19፡10/ እግዚአብሔር፡- "ኑ እንወቃቀስ፣ በኃጢአታችሁ እንደ አለላ የቀላችሁ ብትሆኑ እኔ አጥቤ እንደ በረዶ አጸዳችኋለሁ፣ እንደ ደም የቀላችሁ ብትሆኑም እንደ ባዘቶ ትነጣላችሁ" /ኢሳ. 1፡18፣ አዲሱ ትርጉም/ በማለት የእግዚአብሔርን ምህረት ለሚፈልግና በእምነት ለሚቀበል ሁሉ ከማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ለማንጻት እንደሚችል ይናገራል።

ከክርስቶስ የማዳን ኃይል በላይ የሚሆን ኃጢአት በፍጹም የለም። ቅዱሳንን በማሳደድ የታወቀውን ጳውሎስን እንኳ ክርስቶስ ለውጦታል። እግዚአብሔር ደህንነትን የሚሰጠው ለሁሉም ዓይነት ሰው ነው። የሐዋሪያው ጳውሎስ ምስክርነትም ይህንን እውነት ለማረጋገጥ ነው። "ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፣ አድምጡ! በኢየሱስ አማካይነት ለኃጢአታችሁ ይቅርታ ማግኘት እንድትችሉ፣ ይኸው በሩ ተከፍቶላችኋል። በእርሱ (በክርስቶስ) የሚያምን፣ የሙሴ ሕግ ሊያስገኘው የማይችለውን ከኃጢአት ባርነት ነፃ መውጣትን ያገኛል።" /የሐዋ. 13፡39፣ ሕያው ቃል።/

እግዚአብሔር ይቅር የማይለው ዓይነት ኃጢአት የለም። እግዚአብሔር ነፍሰ ገዳዩን ይቅር ብሏል /መዝ. 32፡5/፣ ሌባውን ይቅር ብሏል /ሉቃ. 23፡43/፣ ተሳዳቢውን ይቅር ብሏል /1ጢሞ. 1፡13/፣ አመንዝራዋን ይቅር ብሏል /ዮሐ. 8፡11/፤ እግዚአብሔር በፍጹም ቅንነት ኃጢአቱን የሚናዘዘውን ሰው ሁሉ ይቅር የሚል አምላክ ነው /ኢሳ. 55፡7/። ስለዚህ እግዚአብሔር ያንተንም ኃጢአት በሙሉ ይቅር ይላል።

## 7/ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክል አይደለም የሚሉ

ይህ ማለት የእግዚአብሔር ሥራ ትክክል አይደለም ማለት ነው። እግዚአብሔር ግን ከቶ በማንም ሊከሰስ አይችልም፣ እርሱ ፍጹም ጻድቅ አምላክ ነውና። እግዚአብሔር ማንንም ለአንድ ዕዳ ሁለት ክፍያ ጠይቆ አያውቅም። የሰዎችን የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል ኃጢአት ያላወቀውን አንድ ልጁን በኃጢአተኞች ምትክ በመስቀል ላይ እንዲሰቀል ፈረደበት። ምናልባት በኃጢአተኞች ፈንታ ቅዱሱን እንዲሰቀል በመፍቀዱ ፍርዱ ትክክል አይደለም ልትል ትችላለህ። ይህን ያደረገው ከፍቅሩ የተነሣ ነው፤ የሰውን ልጆች ስለሚያፈቅር ወደ ዘላለም ሞት ሲሄዱ እያየ ዝም ማለት አላስችል ብሎት /ዮሐ.





15፡13/። እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑም ከኃጢአተኞች ምንም ዋጋ ሳያስከፍል በነፃ ሊያድናቸው ወደደ።

## 8/ ጓደኞቼ ይስቁብኛል ወይም ከጓደኞቼ እለያለሁ የሚሉ

ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል። "እናንተ ሞኞች! እስከ መቼ ሞኝነትን ትመርጣላችሁ! በዕውቀቱስ ላይ በማፌዝ ደስ የሚላችሁ እስከ መቼ ነው? እስከ መቼ ዕውቀትን ትጠላላችሁ? ተግሣጼን ስሙ፣ መልካም ምክርን እሰጣችኋለሁ፣ ወደ እኔ እንድትመጡ እጄን ዘርግቼ ጠራኋችሁ፣ እናንተ ግን ጥሪዬን ቸል አላችሁ። ምክሬን ናቃችሁ፣ ተግሣጼንም አልተቀበላችሁም፤ ስለዚህም መከራ በእናንተ ላይ በሚደርስባችሁ ጊዜ እስቅባችኋለሁ። ድንጋጤ በሚይዛችሁ ጊዜ አፌዝባችኋለሁ።" /ምሳሌ 1፡22-26፣ አዲሱ ትርጉም/ እግዚአብሔር ሲስቅብንና ሲያፌዝብን እንዴት ያስፈራል! እግዚአብሔር ከሚስቅብህ ጓደኞች ቢስቁብህ ይሻላል። ከእግዚአብሔር ከምትለይ ከጓደኞችህ ብትለይ ይሻላል።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይታረቅ እንቅፋት የሚሆኑ ባልንጀሮች ክፉ ባልንጀሮች ናቸው። ክፉ ባልንጀሮችን መራቅ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስጠነቅቅ "ዐመፀኞች በሚሄዱበት መንገድ አትሂድ፣ የክፉ ሰዎችን ምሳሌነት አትከተል ይህን ከቶ አታድርግ፣ ከክፉም ራቅ የክፉዎችን መንገድ ትተህ የምትራመድበትን ቅን መንገድ ተከተል።" ይላል። /ምሳሌ 4፡14-19፣ አዲሱ ትርጉም/።

## 9/ ስደትን እፈራለሁ የሚሉ

ስለ ኢየሱስ ስም መሰደድ ትልቅ ክብር ነው። "ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳደዋቸዋልና።" /ማቴ. 5፡11-12/ ስለ ኢየሱስ ስም የሚያፍሩ ሁሉ ኢየሱስ ደግሞ በእግዚአብሔር አብ ፊት እንደሚያፍርባቸው ተናግሯል። /ማር. 8፡38/ በዚህ ምድር ላይ በኢየሱስ ስም በማመናችን ምክንያት ስደት ቢደርስብን በሰማይ የሚጠብቀን ክብር እጅግ ታላቅ ነው። /ሮሜ. 8፡18/

ስደት በእኛ ላይ ቢደርስ አዲስ ነገር እንዳይደለና በኢየሱስም ላይ የደረሰበት መሆኑን በመገንዘብ ልንበረታና ስደትን በደስታ ልንቀበል ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ በእርግጥ እንደሚሰደዱ የእግዚአብሔር ቃል በግልጥ ይናገራል። በስደትና በመከራ ውስጥ በትዕግስት መጽናት ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የምንነግስበት መንገድ ነው። /2ጢሞ. 2፥12/ ስለ ክርስቶስ መሰደድ ለእግዚአብሔር መንግስት ከተመረጡት ወገን መሆናችንን ስለሚመሰክር ደስ ሊለን ይገባል። /ሉቃ. 6፥22-23/

## 10/ ኢየሱስን አሁን ማመን አልፈልግም የሚሉ

ማንም ሰው ስለ ነገ የሚያውቀው ምንም ነገር የለም። እኔ እስከዛሬ ሳምንት በዚህ ምድር ላይ ለመኖሬ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ የሚል ማንም ሰው አይኖርም። እግዚአብሔርም በጥበቡ ይህን ከሰው ሰውሮታል። ስለዚህም እግዚአብሔር "እነሆ የተመረጠው ሰዓት አሁን ነው፤ የደህንነትም ቀን አሁን ነው። " /2ቆሮ. 6፥2/ በማለት እያንዳንዱ ሰው ደህንነትን መቀበል ያለበት ዛሬ ሆኖ ሳለ ጊዜውም አሁን እንደሆነ በግልፅ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪም "ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ" /ዕብ. 4፥7/ በማለት ኢየሱስን ለማመን መወሰን ያለብን ዛሬ እንደሆነ ያስጠነቅቀናል።

## 11/ እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለሆነ ሰውን ሁሉ እንደማይቀጣ አምናለሁ የሚሉ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ አያስተምረንም፤ ነገር ግን የጻድቃንና የክፉ ሰዎች መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን በግልጥ ተጽፏል። "ስለዚህ ክፉ ሰዎች በፍርድ ቀን ጸንተው አይቆሙም፣ ኃጢአተኞችም በጻድቃን መካከል አይገኙም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የጻድቃንን አካሄድ ያውቃል፣ የክፉ ሰዎች አካሄድ ግን የሚያመራው ወደ ጥፋት ነው።"/መዝ. 1፥5-6፣ አዲሱ ትርጉም/።

የእያንዳንዱ ሰው መዳን ወይም ያለመዳን የሚወሰነው ክርስቶስን ለመቀበልና ላለመቀበል በሚያደርገው ውሳኔ ነው። "እኔን የማይፈልግና ቃሌንም የማይቀበለውን ሰው የሚፈርድበት አለ፤ እኔ የተናገርሁት ቃል በመጨረሻ ቀን ይፈርድበታል።" /ዮሐ. 12፡48/





በእርግጥ እግዚአብሔር መልካምና የምህረት አምላክ ስለሆነ ሰዎችን ሁሉ እንዲሁ ያፈቅራል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን የነፃ ስጦታ የማይቀበሉትን ሁሉ ይቀጣቸዋል።

## 12/ መጽሐፍ ቅዱስ ግጭቶችና እርስ በርስ የሚቃረኑ ሀሳቦች ያሉበት መጽሐፍ ነው የሚሉ

እስቲ አንተ ግጭቶችና ተቃራኒ ሀሳቦች የምትላቸውን አሳየኝ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚጋጩ ሀሳቦች አሉበት ከሚሉ መካከል አብዛኞቹ፣ ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ በሰሙት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው ተመራምረው ተቃራኒ ሀሳቦች እንዳሉበት ስለደረሱ አይደለም። እርስ በርሱ ይቃረናል ብለው ከሚናገሩ ሰዎች አብዛኞቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ የሚሉትን ተቃራኒውን ሀሳብ እንኳ ለይተው ማሳየት የማይችሉ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች የማይገባቸው ምክንያቱ ሰዎቹ አስቀድመው ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር መንፈስ ባለመስጠታቸው ነው። መለኮታዊውን የእግዚአብሔርን ቃል መግለጥ የሚችለው መለኮታዊው መንፈስ ቅዱስ ነው።

የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል፣ ሀሳብና ፈቃድ ለማወቅ ያልቻሉበትን ምክንያት እግዚአብሔር ሲናገር "አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዴም እንደ መንገዳችሁ አይደለም። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል መንገዴ ከመንገዳችሁ እጅግ ከፍ ያለ ነው" ይላል /ኢሳ. 55፥8-9/።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ አስቀድሞ የቃሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ማወቅ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃል ሰው በራሱ ጥበብና ማስተዋል ሊገልጠው የሚችል ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የሚገልጠው ራዕይ ነው። "የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሥጋዊ ሰው ግን ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰጠውን ስጦታ መቀበል አይችልም፣ ምክንያቱም የስጦታው ታላቅነት የሚመረመረው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ስለሆነ ሊያስተውለው አይችልም፣ እንዲያውም ለእርሱ ሞኝነት መስሎ ይታየዋል።" /1ቆሮ. 2፥14፣ አዲሱ ትርጉም/ በተጨማሪም /ዳን. 12፥10 ተመልከት/።

መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እውነት ከመሆኑም በላይ ሁልጊዜም እውነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነትነት ጊዜ

ሊሽረው አልቻለም፣ ወደፊትም አይችልም፡፡ ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሳሳተ አመለካከት የሚኖራቸው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንነት ስለማያውቁ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ 66 የተለያዩ መጻሕፍትን የያዘ፣ በሙያቸው በልምዳቸውና በትውልድ አገራቸው በተለያዩ በ40 ጸሐፊዎች የተጻፈ፣ በ3 ክፍለ ዓለማት የተጻፈ፣ በ3 ቋንቋዎች የተጻፈ፣ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ለመጻፍ የፈጀበት ጊዜ 1600 ዓመታት ሆኖ ሳለ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክቱ አንድ ነው፡፡ ይኸውም ስለ ሰው ልጅ ውድቀትና ስለ እግዚአብሔር ምህረት፣ እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ደህንነት ያዘጋጀውን መንገድ የሚገልጥ መልዕክት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም እውነት ነው፣ የሚያምኑትንም ይለውጣል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነበር አሁን ግን ጊዜው አልፎበታል የሚሉ አንዳንድ ሰዎች በዓለማችን ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ሰዎች "እኛ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘመን እያለን ከ2000 ዓመት በፊት የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እናምናለን?" ይላሉ፡፡ ነገር ግን እውነት ከቶ ስለማይለወጥ የእግዚአብሔርም ቃል እውነት ስለሆነ እስከዛሬ አልተለወጠም፣ ወደፊትም አይለወጥም፡፡ የሰዎች አመለካከትና አስተሳሰብ፣ ግኝቶችና ፍልስፍናዎች ብዙ ተለዋውጠዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን አልተለወጠም፣ ለዘላለም የሚኖረው እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በቃሉ ውስጥ ነውና፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ሲመሰክር "ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል፣ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ፀንታ ትኖራለች" ይላል /ኢሳ. 40፡8/፡፡ በተለያዩ ዘመናት ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ከምድር ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ቀዳደውታል፣ በእሳት አቃጥለውታል፣ ከየሰው ቤት ሰብስበው በየመጋዘኑ ቆልፈውበታል፣ ወደ ባህር ወርውረውታል፡፡ ይህን ያደረጉ ሰዎች የሕይወት ዘመናቸው ሲፈጸም አልፈዋል፡፡

እነርሱ ውሸት ነው ብለው የተቃወሙትና ሊያጠፉት የተነሱበት መጽሐፍ ቅዱስ ግን እውነት ሆኖ የሰዎችን ሕይወት ሙሉ በሙሉ እየለወጠ ዛሬም ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ ወደፊትም ጌታ ኢየሱስ በክብር እስኪመጣ ድረስ ቃሉ (መጽሐፍ ቅዱስ) ፀንቶ ይኖራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የማይጋጭና የማይቃረን አንድ ዓይነተኛ ዓላማ ያለው እውነተኛና ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡





ዓላማውም የሰው ልጆች አንብበውትና ተረድተውት ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቁበትንና የዘላለምን ሕይወት የሚወርሱበትን መንገድ መግለጥ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ብዙ ሰዎች በየዘመናቱ ተነስተው ነበር፡፡ ማናቸውም ቢሆኑ ዛሬ የሉም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ዛሬም አለ፡፡ በቢሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች የሚፈለግና እጅግ የተወደደ፤ ሕይወትን፣ ቤተሰብን፣ ሀገርን ለመልካም የሚለውጥ መጽሐፍ ነው፡፡

ከ1850 እስከ 1910 ዓ.ም. ድረስ በ60 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም የሚሉ 747 የተለያዩ ሰዎች መግለጫዎች አውጥተው ነበር፡፡ እጅግ የሚገርመው ነገር ቢኖር ከእነዚህ ሰዎች መካከል የአንድም ሰው ሀሳብ ከሌላው ሀሳብ ጋር አይስማማም ነበር፡፡

ይህንንም በተመለከተ በ18ኛው ምዕተ ዓመት የኖረው ታዋቂው እንግሊዛዊ ሰባኪ ጆን ዌስሌይ እንዲህ ሲል አጠቃሎታል፡፡ "መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው በመልካም ሰዎች ወይም በመላዕክት፣ በክፉ ሰዎች ወይም በሰይጣን፣ አሊያም በእግዚአብሔር በራሱ መሆን አለበት፡፡ ከቶ በመልካም ሰዎች ወይም በመላዕክት ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የራሳቸው ግኝት ሆኖ ሳለ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል' በማለት ውሸት እየደረደሩ መጽሐፍ ሊያዘጋጁልን አይችሉምና፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከቶም በሰይጣን ወይም በክፉ ሰዎች የተገኘ ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም ኃጢአትን የሚጠላና ቅድስናንና ጽድቅን የሚያስተምር መጽሐፍ ጽፈው በራሳቸው ላይ ፈርደው ገሃነም እሳትን አይጠብቁም ነበር፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ብቻ የተገኘ መጽሐፍ ነው፡፡"

## 13/ እግዚአብሔር መኖሩን እንዴት አውቃለሁ የሚሉ

እያንዳንዱ ዕቃ የሚመረትበት ፋብሪካ አለው፣ እያንዳንዱ ፍጥረትም ፈጣሪ አለው፤ ሰውም ደግሞ የተፈጠረው ፈጣሪ ስላለው ነው፡፡ ሰው "ከወዴት መጣሁ?፣ ወዴትስ እሄዳለሁ?" ብሎ ራሱን መጠየቅ ካልቻለ የሚያስብ ፍጥረት አይደለም ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ማሰብ እንዲችል እግዚአብሔር መልካሙንና ክፉውን መለየት የሚችል ህሊና ሰጥቶታል፡፡

ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን መኖር በህሊናው ያውቀዋል፡፡ ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል የሚከተለውን በማለት ያረጋግጣል፡፡ "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብሔር ባህርይ፣ ይኸውም ዘላለማዊው ኃይሉና አምላክነቱ፣ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጥ ሆኖ ታይቶአል፤ ስለዚህ እንደእነዚህ ያሉት የአዋቂ አጥፊዎች የሚያመካኙት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ እግዚአብሔርን አውቀውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምስጋና አልሰጡትም፤ በአሳባቸውም ከንቱ ሆኑ፤ የማያስተውል ልቦናቸውም ጨለመ፤ ጥበበኞች ነን ሲሉ ሞኞች ሆኑ ዘላለማዊ የሆነውን እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ አላፊና ጠፊ በሆኑት በሰው፣ በወፍ፣ በእንስሳ፣ በመሬት ላይ በሚሳቡ ፍጥረቶች መልክ የተሠሩትን ምስሎች ማምለክ ጀመሩ፡፡" /ሮሜ. 1፡20-23፣ አዲሱ ትርጉም/

እንዲሁም ሰዎች እግዚአብሔርን በተፈጥሮ ሊያውቁት በተገባቸው ነበር፣ ምክንያቱም ተፈጥሮ ያለ ፈጣሪ ሊኖር ከቶ አይችልምና፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱን በተፈጥሮ፣ በቃሉ አማካይነትና አንድ ልጁን በመላክ ስለገለጠ ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖር አናውቅም ለማለት ምንም ምክንያት ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ ከፍጥረት ሁሉ መካከል አምልኮን የሚፈልግ ሰው ብቻ ነው፡፡ ይህም በሰው ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የፈጠረው ባዶ ቦታ መኖሩን ያመለክታል፡፡ የሰው ነፍስ የፈጠራትን ለማወቅ ሁልጊዜ ትናፍቃለች፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን መኖር በውስጡ ባለው ባዶነትና የነፍስ ናፍቆት ሊያውቅ ይችላል፡፡

## 14/ የራሴ ሃይማኖት አለኝ የሚሉ

ለመሆኑ ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ነው? ሃይማኖት ማለት የቤተክርስቲያን ህንፃ ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም ሃይማኖት ማለት መልካም ኑሮን መኖር ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ መሰብሰብና የተለያዩ በዓላትንም ማክበር አይደለም፡፡ ነገር ግን ሃይማኖት ማለት በላቲን ቋንቋ ሬ፣ ሊጃሬ /ሬሊጃሬ/ የሚል ቃል ሲሆን፣ በእንግሊዝኛው ሬሊጅን ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም ተመልሶ መጣበቅ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ሃይማኖት ማለት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶና ርቆ የነበረው ሰው ተመልሶ ከአምላኩ ጋር መጣበቅ ማለት ነው፡፡ ሃይማኖት ትልቁን የሰውን የነፍስ ጥያቄ ይኸውም





ነፍስ ከፈጣሪዋ ጋር ተመልሳ ለመጣበቅ የምታደርገውን ጩኸት የሚመልስ ነው፡፡

እያንዳንዱ ሰው የግድ የራሱ የሆነ አንድ ሃይማኖት እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ አንድ ሰው ስለዚህ ሲናገር "ሰው ሃይማኖት ያለው ፍጥረት ነው" ብሏል፡፡ ሰው ሲፈጠር እግዚአብሔር በአፍንጫው የሕይወትን እስትንፋስ እፍ በማለት ከሌሎቹ ፍጥረታት ሁሉ በተለየ መንገድ ስለፈጠረው፣ ይህ በሰው የሚኖረው የሕይወት እስትንፋስ ሕይወትን ስለሚፈልግ ሰው ሁሉ የራሱን ሃይማኖት ይፈልጋል፡፡

ሰው እርካታን በትምህርት፣ በሀብት፣ ባለውም ነገር ብዛት ሊያገኝ አልቻለም፤ ነገር ግን ሰው ውስጣዊ እርካታንና የልብ ደስታን እንዲሁም የአእምሮ እረፍትን የሚያገኘው ተመልሶ ከአምላኩ ጋር ሲጣበቅ ብቻ ነው፡፡ ቅዱስ አውግስጦስ የተባለ ሰው ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር "እግዚአብሔር ሆይ አንተ ለራስህ ሰራኸን፣ ልባችንም አንተን እስኪያገኝ ድረስ እረፍት የሌለው ተቅበዝባዥ ነው" በማለት ተናግሯል፡፡

የሰው ነፍስ እግዚአብሔርን ስለመጠማቷ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፡፡ "ሕያው አምላክ ሆይ! ውሃ የመጠማትን ያህል አንተን እናፍቃለሁ፣ በፊትህ ለመስገድ ወደ አንተ የምቀርበው መቼ ነው?" /መዝ. 42፡2፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡ "እዚያም ለመሆን እጅግ እናፍቃለሁ፣ በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ መሆን እፈልጋለሁ፡፡" /መዝ. 84፡2፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡ ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ያለው የልቡ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ዊሊያም ጀምስ የተባለ አንድ አሜሪካዊ የስነ ልቡና ሊቅ የሰው ነፍስ እግዚአብሔርን ስለመፈለግ ሲመሰክር "እኛና እግዚአብሔር እርስ በርሳችን እንፈላለጋለን፣ እኛም እንፈልገዋለን እርሱም ይፈልገናል" በማለት ተናግሯል፡፡

ስለዚህ ሃይማኖት አለኝ በማለት የሃይማኖትን ምንነት ሳናውቅና በሕይወታችንም ተግባራዊ ሳናደርግ መኖሩ ሞኝነት ነው፡፡ ሃይማኖት አለን ካልን ራሳችንን መጠየቅ የሚገባን ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም በዓላማ እንድንኖር ከፈጠረን አምላክ ጋር ነፍሳችን ተጣብቃለች ወይ? ነፍሳችን እግዚአብሔርንስ ታፈቅረዋለች ወይ? ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ የሚቻለው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን የደህንነት መንገድ በመከተልና ምህረቱን በእምነት በመቀበል ነው፡፡ እግዚአብሔር ያዘጋጀውም የምህረትና የደህንነት መንገድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

## 15/ ኢየሱስ ታላቅ ሰው ወይም ነቢይ እንጂ አምላክ አይደለም የሚሉ

ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ራሱ መስክሯል፡፡ "እርሱ የመለኮት ባህርይ አለው፣ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባህርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም፡፡" /ፊልጵ. 2፡6/ ኢየሱስ ከተከሰሰበትና የመስቀል ሞት ከተፈረደበት ምክንያቶች አንዱ ራሱን እግዚአብሔር ነኝ ብሏል የሚል ነበር /ማቴ. 26፡63-65/፡፡ እርሱ የሞትን ኃይል አሸንፎ ተነስቷል፡፡ /ሐዋ. 2፡24/ በፍጹም ኃጢአትን አላደረገም /ዮሐ. 8፡46/፡፡ እርሱ የዓለምን ታሪክና የሰዎችንም ሕይወት ለውጧል፡፡

በእርሱ አማካይነት ሕይወታቸው የተለወጠላቸው ስለ እርሱ አዳኝነትና አምላክነት መስክረዋል /ዮሐ. 4፡42/፡፡ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን አምላክነት ሲያረጋግጥ እንደዚህ ይላል፡- "እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው፡፡" /1ዮሐ. 5፡20/፡፡

ስለ እግዚአብሔርና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ኃጢአትና ሃይማኖት፣ ወዘተ የተለያየ አመለካከትና መረዳት ያላቸውን ሰዎች ወደ እውነት መድረስ እንዲችሉ እንዴት ልንረዳቸው እንደምንችል በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ለማየት ሞክረናል፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የወንጌልን አደራ በታማኝነት መፈጸም እንድንችል እግዚአብሔር የሚያቀርብልንን ጥሪ ስናነብ ለዚህ ሰማያዊ ጥሪ አሜን የሚል ምላሽ ለመስጠት እንድንችል መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን ጸሎቴ ነው፡፡



# ምዕራፍ ስድስት

## የመከሩ ጥሪ

እግዚአብሔር አምላክ ለዘላለም የሚኖረውን የሕይወት እስትንፋስ ሰጥቶ የሰውን ልጅ ከፈጠረ በኋላ ሰው እንዲያገለግለው መለኮታዊ ጥሪ አቅርቦለታል፡፡ ከአዳም ጀምሮ በየትውልዱ ሰዎች እንዲያገለግሉት እግዚአብሔር ጥሪ አቅርቧል፡፡ ኖህ እንዲያገለግለው እግዚአብሔር መርጦታል፡፡ አብርሃም እንዲያገለግለው ከዘመዶቹ መካከል ጠርቶታል፡፡ የእስራኤል ልጆች እንዲያገለግሉት "ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" (ዘጸአ. 8፡2) በማለት ለፈርዖን እንዲናገርና እስራኤልን ከግብፅ ባርነት እንዲያወጣ ሙሴን ጠርቶታል፡፡

ስለ እግዚአብሔር ጥሪ ብዙ ምሳሌዎችን ወይም ታሪኮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነገር ግን እጅግ አስፈላጊው ነገር እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን አንተንና እኔን እንድናገለግለው እየጠራን መሆኑን ማወቅና ለጥሪውም ተገቢውን ምላሽ መስጠት መቻል ነው፡፡

በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን "ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል" (ኢሳ. 6፡8) በማለት ለኢሳይያስ ጥሪ ያቀረበው ቅዱሱ እግዚአብሔር ዛሬም ለአንተ ይህንኑ ጥሪ እያቀረበ ነው፡፡ ይህም ጥሪ ለተወሰኑ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በክቡር የክርስቶስ ደም ለተዋጁት ሁሉ የቀረበ ጥሪ ነው፡፡ የእግዚአብሔርም ቃል ስለዚህ ጥሪ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል" (1ጴጥ. 2፡9-10)፡፡ ከዚህ ክፍል እንደምንመለከተው በክርስቶስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቃችን ምክንያት ወይም የክርስቶስን አዳኝነት በማመናችን ምክንያት እጅግ ብዙ አስደናቂ ነገሮች ተደርገውልናል፡፡

እነዚህም፡- 1ኛ) ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ተጠርተናል፣ 2ኛ) የእግዚአብሔርን ቸርነት እንድንነግር ተመርጠናል፣ 3ኛ) የንጉሥ ካህናት ሆነናል፣ 4ኛ) ተቀድሰናል፣ 5ኛ) ለእግዚአብሔር ርስት ወራሽነት ተጠርተናል፣ 6ኛ) የእግዚአብሔር ወገን ሆነናል፣ 7ኛ) ምሕረትን አግኝተናል፡፡ ስለተደረገልን ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ስንጀምርና ከእግዚአብሔር ያገኘነውን በረከት ስንቆጥር ብቻ ነው ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ መስጠት የምንችለው፡፡ እግዚአብሔርን እንድናገለግለው የሚያነሳሳንም በክርስቶስ የተደረገልንን በረከት ስናስብና ውለታውን ለመመለስ ስንዘጋጅ ነው፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልን አስደናቂ ነገሮች ሲሆኑ፣ የተደረገለት ሰው ደግሞ እንዲያደርግ ስለሚጠበቅበት የሚከተሉትን ደግሞ እንድንታዘዝ ጥሪ ቀርቦልናል፡፡ 1ኛ) ከእርሱ ያገኘነውን ብርሃን እንድናበራ፣ 2ኛ) ቸርነቱን ለሌሎች እንድንናገር፣ 3ኛ) የክህነትን (በሊቀካህኑ በክርስቶስ የተጀመረውን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅ) አገልግሎት እንድንሰጥ፣ 4ኛ) ምሕረት ያላገኙትን ወደ ምሕረቱ እንድናመጣ 5ኛ) በኃጢአትና በዓመፅ ያሉትን ወደ መታዘዝና ወደ ቅድስና እንድናመጣ፣ 6ኛ) የእግዚአብሔር ወገን ያልሆኑትን ወገኑ መሆን የሚችሉበትን እውነተኛ መንገድ እንድናሳይ፣ 7ኛ) በሰይጣን ታስረው ያሉትን ለዘላለም ወደሚኖር ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ርስት እንድናመጣ ተጠርተናል፡፡

ይህንን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ጥሪና ፈቃድ መታዘዝ እንጂ "ጌታ ሆይ በጎነትህን እንድነግር ፈቃድህ ምንድር ነው?" በማለት ጊዜ ማጥፋት ስንፍና ነው፡፡ ለመለኮታዊው ጥሪ ምላሽ የምንሰጥበት ጊዜ ደግሞ አሁን ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ የኖረው ለዚህ ጥሪ ነበር፡፡ ሕይወቱ በሙሉ የተሞላው ይህን ጥሪ በመታዘዝ ነበር፡፡ ወንጌላዊው ማቴዎስ ይህን እውነት ሲገልጽ እንዲህ በማለት ጽፏል፡፡ "ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፣ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፣ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር፡፡ ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፣ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን መከሩስ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው" (ማቴ. 9፡35-38)፡፡





ጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ሠራተኛ ሆኖ ነበር የምድር ላይ ሕይወቱን የፈጸመው፡፡ በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ ሳይወሰን ሰዎች ወደሚገኙበት ሥፍራ ሁሉ በመሄድ የመንግሥትን ወንጌል ይሰብክ ነበር፡፡ በሥጋ ደዌ የተቸገሩ እንዲሁም የኃጢአት ሸክም የከበደባቸው ወዳሉበት ድረስ በመሄድ ይረዳቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ጥሪ የመሄድ እንጂ በቤተክርስቲያን ወይም በቤተመቅደስ ውስጥ ሰዎች ወደ እኛ እስኪመጡ ድረስ የመጠበቅ ጥሪ አይደለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሄደ፡፡ ከየት ወደየት? ከሰማይ ሰማያት ከክብሩ ዙፋን ወርዶ ኃጢአተኛ ሰው ወደሚገኝበት ወደዚህ ምድር፣ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" (ሉቃ. 19፡10) በማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ተላከ፡፡

የእግዚአብሔር ጥሪ ለፍለጋ የመሄድ ጥሪ ነው፣ የጠፋውን ለመፈለግ መሄድ፡፡ ያለውን ዘጠና ዘጠኙን ትቶ የጠፋውን አንዱን ለመፈለግ መሄድ፡፡ ከአባቱ ጋር ያለውን ትቶ በምድረ በዳ የሚቅበዘበዘውን ለመፈለግ የመሄድ ጥሪ፡፡ የጠፋው ያለው በቤተመቅደስ ውስጥ ሳይሆን በብዛት ያለው ከቤተመቅደስ ግቢ ውጭ በየመንደሩ፣ በየጎዳናው፣ በየቤቱ ነው፡፡ ስለዚህ ነበር ጌታ ኢየሱስ በከተማዎችና በመንደሮች ይዞር የነበረው፡፡ ዓላማው የጠፋውን ለመፈለግ ስለነበረ፣ ደዌና ሕማማቸውን እየፈወሰ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከ፣ የአባቱን ፈቃድ እየፈጸመ ኖረ፡፡

ጠላታችን ሰይጣን ግን ይህን የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር የመጣበትንና የሞተበትን ዓላማ እንዳናስተውልና ይህንንም እውነት እንድንረሳ አድርጎናል፡፡ በየጎዳናው ለሚገኙ ሰዎች "በክርስቶስ እመን ትድናለህ" ብለን ስንመሰክር "ለምን በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ብቻ አትሰብኩም" በማለት የሚተቹና የሚቃወሙ ሰዎች ያጋጥሙናል፡፡ አሊያም ደግሞ የጠፋውን ለመፈለግ የመሄድ ራዕይ ስለጠፋ የተገኘውን ለመከፋፈል በመሻማት፣ እርስ በርስ እየተነካከስን እንገኛለን፡፡

ዘመናችንን በሙሉ እውነትን ሸፍነን ከመኖር አንድ ቀን ለእውነት ኖረን መሞት ምነው በተገኘ! በየቤተክርስቲያኑ የሚታይ መገፋፋትና ጥላቻ ምንጩ ምን ይሆን? የጠፋውን ለመፈለግ በየአቅጣጫቻችን መበታተን ትተን የተገኘው 'ለእኔ ይገባኛል' በማለት እኛው የፈጠርነው ጠባቡ አዳራሽ ስለጠበበን አይደለምን?

በእርግጥ መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ የመከሩ ጌታ የሆንክ እግዚአብሔር አንተው ራስህ የመከሩን

ሠራተኞች አስነሳልን፡፡ የጠፋውን ፍለጋ የሚሄዱ፣ ቤት ውስጥ ተቀምጠው የሚበሉ ሳይሆን መከር ወዳለበት የሚሄዱ፤ 'ክርስቲያን ነኝ' ብለው የሚቀመጡ ሳይሆን፣ የክርስቶስን ምሳሌነት የሚከተሉ የመከሩን ሠራተኞች ላክልን፡፡ አምላክ ሆይ በቤትህ ውስጥ አገልጋዮች ብዙ ናቸው፣ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው፣ ክርስትናን የሚኖሩ ግን ጥቂቶች ናቸው፤ የእንጀራ ሠራተኞች ብዙ ናቸው፤ የመከሩ ሠራተኞች፣ በእርሻው ውስጥ ለመሆንና ዋጋ ለመክፈል የቆረጡ፣ ስለ እውነት ለመሞት ራሳቸውን የሚሰጡ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ እባክህን ለፈቃድህ የሚገዙ ሠራተኞችን ላክልን፡፡ የአንተን እውነት እየሸፈንን ለራሳችን የምንኖር ከሆነ ግን ይቅር በለንና በጊዜ ወደ ቤትህ ውሰደን፡፡ ዋጋ የሌለውን ኑሮ እንድንኖር አትፍቀድልን፡፡ አሜን፡፡

ወንድሜ ሆይ በዚህ ሰዓት ልብህ ለእውነትና እግዚአብሔርን በእውነት አገልግሎ ለማለፍ የእኔ ልብ የሚቃጠለውን ያህል የሚቃጠል ከሆነ አንተ የመከሩ ሠራተኛ ነህ፡፡ ወደ መከሩ በእግዚአብሔር ተልከሃል፣ ተግተህ ሥራህን ፈጽም፡፡ እግዚአብሔር ሲጠራቸው ግን ቶሎ የማይነቁና ራሳቸውን የማይሰጡ ሰዎች አሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ቶሎ እንዲነቁና ወደ መከሩ ሄደው አዝመራውን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰበስቡ መርዳት ያስፈልጋል፡፡

ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለሦስት ዓመት ተኩል አብረው የተጓዙ ደቀ መዛሙርት እንኳን ሳይቀሩ ስለ መከሩ በትክክል አልገባቸውም ነበር፡፡ በዮሐ. 4:31-36 ላይ ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ስለጊዜው የነበራቸውን የአመለካከት፣ የመረዳትና የራዕይ ልዩነት መመልከት ስለ መከሩ የተሻለ ግንዛቤ ይሰጠናል ብዬ ስላመንኩ ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ አቅርቤአለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስና ደቀመዛሙርት፡-

## 1) ጊዜውን ያለማወቅ ልዩነት ነበራቸው

ለደቀመዛሙርቱ የመከር ጊዜ ገና አልደረሰም ነበር፣ እነርሱ ለመከር ገና አራት ወር ቀርቷል ይሉ ነበር፡፡ ደቀመዛሙርቱ ያዩ የነበረው የእንጀራውን (የገብሱንና የስንዴውን አዝመራ) ጉዳይ እንጂ የእግዚአብሔርን መንግሥት አዝመራ፣ በሰማሪያ ከተማ (ያለ ክርስቶስ) የጠፉትን ሰዎች ጉዳይ አልነበረም፡፡ ለክርስቶስ ግን የአዝመራው ጊዜ አሁን ነበር፡፡ የሰማይ መንግሥት አዝመራ





የሚሰበሰበው ነገ ወይም የሚመጣው ዓመት ሳይሆን አሁን ነው፡፡ የተመቸ ጊዜ ሲመጣ ሳይ
ሆን በጊዜውም አለጊዜውም፣ ቢመችም ባይመችም አሁን ነው፡፡

ይህንን እውነት በትክክል የተረዳው የወንጌል ሰው ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት "ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና .... መከራን ተቀበል፣ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ አገልግሎትህን ፈጽም" (2ጢሞ. 4:2,5) በማለት ዘመኑን መዋጀት እንዳለበት ይመክረዋል፡፡ ወገኔ ሆይ፣ ለጠራህ አምላክ ታማኝ የምትሆንበትና አገልግሎትህን የምትፈጽምበት ጊዜ አሁን እንጂ ነገ አይደለም፡፡ ዛሬ የምትችለውን ሁሉ አድርግ፣ በጎን ነገር ነገ ለመሥራት አታሳድር፡፡

## 2) ቅድሚያን የማወቅና ለቅድሚያ የመኖር ልዩነት ነበራቸው

ደቀመዛሙርቱ በዚያን ጊዜ ለየትኛው ጉዳይ በሕይወታቸው ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባቸው አላወቁም ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር አይን ሞኝነት የሆነውን ነገር በቅድሚያ ለመሥራት መረጡ፣ ከከተማ የገዙትን እንጀራ በቅድሚያ ለመብላት፡፡ የክርስቶስ ቅድሚያ ግን በዚያን ሰዓት፣ በእግዚአብሔር አብ፣ ለሰማሪያ ከተማ ህዝብ የተላከ የመከሩ ሠራተኛ መሆን ነበር፡፡ ስለዚህም ነው ደቀ መዛሙርት "ጌታ ሆይ ብላ" ብለው ሲለምኑት "የእኔ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" (ዮሐ. 4:34) ያላቸው፡፡

በሕይወታችን ለምን ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ካላወቅን ፈጽሞ ደስተኞች ሳንሆን ዘመናችን ይፈጸማል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን የመኖር ዓላማን በትክክል ያወቀ መሪያችን ነበር፡፡ "የእኔ መብል፣ እኔን የሚያረካኝና የሚያስደስተኝ የላከኝን የአባቴን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ነው" አለ፡፡ ደግሞም ዛሬ ብቻ ሳይሆን እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ ለተጠራሁበት ዓላማ በታማኝነት መኖር ነው አለ፡፡ የአንተስ የሕይወትህ ትልቁ ዓላማ ምንድር ነው? ይህንንስ ዓላማ ለመፈጸም እንዴት እየኖርክ ነው?

## 3) በራዕይ የመኖር ልዩነት ነበራቸው

በራዕይ ለመኖር የሚቻለው በመጀመሪያ ራዕይ ሲኖር ነው፡፡ ራዕይ ደግሞ ለሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በሕይወታቸው ራዕይ ያላቸው ሰዎች የሕይወታቸውን ዘመን ይጠቀሙበታል እንጂ በከንቱ አያሳልፉትም፡፡ ዘመናችንን በከንቱ ስለማሳለፍና በቁም ነገር ስለመኖር በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተላልፎ የነበረው "እማማ አከስጅን" የተባለው ድንቅ ድራማ ብዙ ትምህርት ሊሰጠን እንደሚችል አምናለሁ፡፡ ዕድሜያቸውን በከንቱ ከሚያሳልፉ ሰዎች በብዙ ብር ዕድሜን ለመግዛት ዞረው ስላጡ ስለ አንዲት አሮጊት ሴት የሚተርክ ድራማ ነበር፡፡ ሰው በሕይወቱ ራዕይ ከሌለው ተወልዶና ኖሮ፣ ነገር ግን የሚያረካ ኑሮ ሳይኖር ይሞታል፡፡ እየኖሩ መሞትና እየሞቱ መኖር በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ እየሞቱ መኖር ጊዜንና ዘመንን አንድ ቁም ነገር ሳይሰሩ በምድር ላይ በከንቱ እየተመላለሱ መኖር ሲሆን፣ እየኖሩ መሞት ግን ሕይወታችን ትልቅ ዓላማ እያከናወነ ዘመናችን ጣፋጭ እንደሆነ መሞት ማለት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ኖሮ የመሞትን ትርጉም በእጅጉ ስላወቀ ነበር እያንዳንዱን የሕይወቱን ቀን "ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ (ዓላማዬን) ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች" (ዮሐ. 9፡4) በማለት የኖረው፡፡ በዓላማ ለመኖር ቁልፉ የራዕይ ሰው መሆን ነው፡፡ ራዕይ ደግሞ የሚገኘው እኛን ከሠራ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ እኛን ሲሠራን ምን ሠርተን ማለፍ እንደምንችል ያውቃልና፡፡

ደቀመዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስ ያይ የነበረውን ሊያዩ አልቻሉም ነበር፡፡ የእነርሱ ዓይኖች በጊዜያዊው ላይ ነበሩ፤ እንዲበሉ በቀረበው ምሣ ላይ፡፡ ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ "እነሆ ዓይናችሁን አንሡ" ያላቸው፡፡ "ዓይናችሁን አንሡ የእግዚአብሔርም አዝመራ አሁን እንደነጣ እርሻውን ተመልከቱ" ነበር ያላቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስና ደቀመዛመርት የራዕይ ልዩነት ነበራቸው፡፡ ደቀመዛሙርቱ የእግዚአብሔር ሀሳብ ምን እንደሆነ ሊረዱ አልቻሉም ነበር፡፡

እግዚአብሔር ዛሬም እኛን እርሱ የሚያየውን እንድናይ ይጠራናል፣ ዓይኖቻችንን አንስተን የአዝመራውን ብዛት እንድናይ፡፡ ለኃጢአቱ የሞተለትን ክርስቶስን ሳያውቅ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይቶ ወደ ሥቃይ ሥፍራ የሚወርደውን ሕዝብ ብዛት ተመልከተን "ጌታ ሆይ ወደ አዝመራው ላከኝ" እንድንለው





ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር የሚመለከተውን እንድንመለከት እርሱ ዓይኖቻችንን ይከፈትልን፡፡

## 4) ውስን ጊዜ እንደነበራቸው የማወቅ ልዩነት

ደቀመዛሙርት መከሩን ለመሰብሰብ ወይም እግዚአብሔርን ለማገልገል የነበራቸው ጊዜ ውስን መሆኑን አላወቁም ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን በምድር ላይ የነበረው ጊዜ ውስን መሆኑን በሚገባ ያውቅ ነበር፡፡ በውስን ጊዜያችን በጊዜ ያልተወሰነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሀሳብ አገልግለን ለማለፍ ራሳችንን መስጠት ምንኛ መታደል ነው፡፡ በጊዜያችን መሥራት እንደሚገባ የእግዚአብሔር ቃል ሲያረጋግጥ "በበጋ የሚያከማች ልጅ አስተዋይ ነው፤ በመከር የሚተኛ ግን እርሱ ራሱን ያስነውራል" ይላል (ምሳ. 10፡5)፡፡ በጋ ማለት የአዝመራ ጊዜ ማለት ነው፡፡

አዝመራ በደረሰበት ጊዜ አዝመራውን በወቅቱ የሚሰበስብ ሰው አስተዋይ ሲሆን፣ በአዝመራ ጊዜ የሚተኛ ደግሞ ሰነፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሰነፍ ልጆች የሉትም፤ ስለዚህም ነው እግዚአብሔር "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ (እንድትኖሩ) በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ፡፡ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ" (ኤፌ. 5፡ 15-17) ብሎ የሚናገረን፡፡ በተጨማሪም "አንተ የምትተኛ ንቃ" (ኤፌ. 5፡14) ይለናል፡፡

የመከሩ ሠራተኞች እንድንሆንለት እናንተ የምትተኙ ንቁ፣ ሰነፎች አትሁኑ፣ ዘመኑን ዋጁ ይለናል፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ግን ከስንፍናቸው የተነሣ ወይም ለወንጌል ዋጋ መክፈል ስለማይፈልጉ "የእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ አልደረሰም" በማለት ይናገራሉ፡፡ ለአንድ ክርስቲያን የመከር ጊዜ መቼ ነው ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ ያ ሰው ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ ወደ ጌታው የሚሄድበት ጊዜ እስኪደርስ ያለው ጊዜ ለእርሱ የመከር፣ የአዝመራ ጊዜ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ድምፅ በዚህ ሰዓት ወደ እኛ እየመጣ ያለው እንደ ጥበበኞች እንድንኖር ነው፡፡ ዘመኑን እንድንዋጅ ነው፡፡ ለመሆኑ ጥበበኞች እንዴት ይኖራሉ? መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጠናል፡፡ "..... በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል፡፡ በምድርም ትቢያ ውስጥ

ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፣ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና፡፡ ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ፡፡" (ዳን. 12፡1-3)

ጥበበኞች ማለት እግዚአብሔርን በመፍራት የኖሩ፣ እግዚአብሔርን ያፈቀሩና ትዕዛዙን የፈጸሙ ማለት ነው፡፡ ጥበበኞች ማለት ጥበብን የሚያስተላልፉ፣ በበጋ የሚያከማቹ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚመላለሱ፣ እግዚአብሔር ሲጠራቸው የሚታዘዙ፣ የሕይወታቸውን ዓላማ የተረዱ ማለት ነው፡፡

## ሀ) ጥበበኛ ማለት የሕይወቱን ዓላማ የተረዳ ነው

የመኖር ትርጉም የገባቸውና የሕይወት ዓላማ ያላቸው ሰዎች ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶች ናቸው፡፡ የሕይወታቸውን ዓላማ የተረዱ ማለት በዚህ ዓለም ላይ ለምን እንደሚኖሩ የገባቸው ማለት ነው፡፡ የሰው ልጆች በዓለም ላይ የመኖር ዓላማ ሁለት ዋና ዋና ሲሆን እነርሱም እግዚአብሔርን ማወቅና እግዚአብሔርን ማሳወቅ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርም የፈጠረን ለዚሁ ዓላማ ነው፡፡ (የሐዋ. 17፡25-26)

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ በምድር ላይ እንዲኖሩ የተወሰነ ጊዜንና ቦታን ወስኖላቸዋል፡፡ የሰው ልጆች ለኖሩበት ጊዜና ለኖሩበት ቦታ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ አንተ በዚህ ጊዜ በምድር ላይ ያለኸው በአጋጣሚ መጥተህ ወይም ከአባትና እናትህ በድንገት ተወልደህ አይደለም፡፡ የትም ብትወለድ፣ እንዴትም ብትወለድ በዚህ ጊዜ በምድር ላይ መወለድህን እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ አንተ ከእግዚአብሔር ፊት የተሰወርክ ሰው አይደለህም፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረህና አሁን በሕይወት እንድትኖር የፈቀደልህ በዓላማ ነው፡፡ ሰው ወደሚበዛበት ሥፍራ ሂድ፣ በዓይንህ ለማየት የምትችለውን ያህል ሰው ተመልከት፤ አንተን የሚመስል ሰው አንድም አታገኝም፡፡ በዓለም ከሞላው ሕዝብ ሁሉ መካከል በባህርይም ሆነ በመልክ አንተን የሚመስል ሰው የለም፡፡ እግዚአብሔር አንተን ሲሠራ አንተን ብቻ እንጂ የማንም ግልባጭ (ኮፒ) አድርጎ አልሠራህም፡፡ ማንንም ሰው እንዳትመስል አድርጎ ሠራህ፡፡

አንተን ከሌላው ሰው ሁሉ ለየት አድርጎ እንደ ሠራህ እንዲሁም በአንተ ለመፈጸም የሚፈልገው ዓላማውም ለየት ያለ ነው፡፡ አንተ





ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ሰው ነህ፡፡ እንዲሁ በቤተሰብህ መካከል በገበታ ዙሪያ አንድ ወንበር ለመያዝ ወይም በመኝታ ቤት አንድ አልጋ ለመያዝ ወይም በአገር ህዝብ ቁጥር ላይ አንድ ሰው እንዲጨመር ብቻ አይደለም የተወለድከው፡፡ ነገር ግን አንተ ብቻ መሥራት የምትችለውን አንድ ሥራ ለመሥራት ነው የተፈጠርከው፡፡

እግዚአብሔር አንተን ሲፈጥር አልተሳሳተም፡፡ "አምላኬ ሆይ ለምን ፈጠርከኝ" አትበል፡፡ ነገር ግን "አምላኬ ሆይ እኔን የፈጠርከኝ ለየት አድርገህ፣ ማንንም እንዳልመስል ተጠንቅቀህ ነው፣በእኔም ሕይወት ያለህ ዓላማ ልዩ ነው፤ ምን እንድሠራልህ እንደምትፈልግ አሳየኝ" ብለህ ጠይቀው፡፡

ሁሉም ሰው እንዲሠራ የተጠራበት ጥሪ፣ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ መርዳት፣ ከሥራዎች ሁሉ ቀዳሚ መሆኑንና ይህንንም ከአሁን ሰዓት ጀምረህ መሥራት እንደምትችል አትዘንጋ፡፡ ማንም ሰው ወደ ጌታ ኢየሱስ ሊያመጣ የማይችለውን አንድ ሰው ወደ ጌታ ብታመጣ ማንም ሰው ሊሠራ የማይችለውን ሥራ ሠራህ ማለት ነው፡፡ አያስደንቅም?

## ለ) ጥበበኛ ማለት ብዙዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልስ ነው

ሰዎችን ወደ ሲኦል ከመግባታቸው በፊት ወደ ጽድቅ የሚመልስ ጥበበኛ ነው፡፡ "በሕዝቡም መካከል ያሉ ጥበበኞች ብዙ ሰዎችን ያስተምራሉ፡፡" (ዳን. 11፡33)፡፡ ጥበበኞች ማለት የምሥራች የሚያወሩ፣ መልካም ነገር በማይሰማበትና ጨለማ ባንዣበበት ሁኔታ ውስጥ ላሉ "የምሥራች፣ ኢየሱስ ብርሃን ነው" ብለው የሚያወሩ ናቸው፡፡ ለተገፉ፣ ለተጣሉ፣ ፍቅር ለራባቸው፣ "የምሥራች፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ብለው የሚያወሩ እነርሱ ጥበበኞች ናቸው፡፡ እኔ ከዳንኩ ምን ቸገረኝ ብለው እጃቸውን አጣምረው የማይቀመጡ፣ ነገር ግን የወንጌል ጉዳይ እረፍት ይነሳኛል የሚሉ እነዚህ ጥበበኞች ናቸው፡፡

በዓላማ የሚኖሩ፣ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ቀን ሳለ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚሰጡ፤ ዘላለማዊ ዋጋ ላላቸው ነገሮች ቅድሚያ ሰጥተው የሚኖሩ፣ ብዙዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ፣ "እኔ ሞኝ አይደለሁም ስለዚህም እንደ ሞኝ አልመላለስም" የሚሉ እነዚህ ጥበበኞች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር

“ማንን ልላክ ማንስ ይሄድልኛል?” ሲል “ጌታ ሆይ እኔን ላከኝ” በማለት ራሳቸውን የሚሰጡ እነዚህ ጥበበኞች ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ ሰማይ ፀዳል፣ እንደ ከዋክብትም ለዘላለም ይደምቃሉ፡፡ ወገኔ ሆይ በጥበብ ትኖራለህን? ለመከሩስ ጥሪ የምትሰጠው ምላሽ ምንድር ነው?

በዚህ ምድር ላይ በሕይወት እንድትኖር እግዚአብሔር የሰጠህ ዘመን ይህ ብቻ እንደሆነ አስብ፡፡ የእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ገና አልደረሰም ስትል ወይንም እንደዚህ የሚሉትን ሰዎች ሀሳብ እየሰማህ ስታመነታ የዘመንህ ቀኖች እያለፉ እንደሚሄዱ አትዘንጋ፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ሆይ ለእኔና ለአንተ የሥራ ጊዜ አሁን ነው በል፡፡ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋራ ሊሠራ ዝግጁ ነው፡፡

ዶ/ር ሳም ሾሜከር የተባሉ አንድ ጸሐፊ (Extraordinary Living for Ordinary Men) በተባለ መጽሐፋቸው “በበሩ አጠገብ ልቆይ” በሚል ርዕስ የጻፉትን አንድ አስደናቂ ውሳኔ አንተም በሕይወትህ በምታደርገው ውሳኔ ሊረዳህ ስለሚችል ከዚህ ቀጥሎ አቅርቤአለሁ፡፡

## በበሩ አጠገብ ልቆይ

“በበሩ አጠገብ እቆያለሁ፡፡ ብዙም ርቄ ሳልገባ ብዙም ርቄ ሳልወጣ፡፡ ይህ በር በዓለም ላይ እጅግ አስፈላጊ በር ነው፡፡ ሰዎች እግዚአብሔርን በግላቸው ሲያገኙ የሚገቡበት፡፡ ብዙዎች ከውጭ ሆነው በሩን ለማግኘት ሲንከራተቱ የእኔ ወደ ውስጥ ርቄ መግባት ጥቅም የለውም፡፡ ብዙዎችም የሚያገኙት በሩን ሳይሆን ግድግዳውን ነው፡፡ በሩን እናገኛለን በማለት እጆቻቸውን ዘርግተው በዳበሳ እንደ ዓየነ ስውር የግድግዳውን ጥግ ይዞራሉ፣ በሩን ግን አላገኙትም፡፡ ስለዚህ እኔ በበሩ አጠገብ ልቆይ፡፡ በዓለም ላይ ለሰው ልጆች እጅግ አስደናቂው ነገር ያን በር ማግኘት ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር የሚገቡበትን በር፡፡

ማንም ሰው ሊያደርገው የሚገባ እጅግ አስፈላጊ ነገር እነዚያን እንደ ዕውር የሚንከራተቱትን ሰዎች እጆች ይዞ ወደ በሩ መምራት ነው፡፡ ውርጭ ሲበዛ በየጎዳናውና በየበረንዳው እንደሚሞቱ ለማኞች ከዚህ በር ውጭ ሆነው የሚሞቱ ብዙዎች ናቸው፡፡ ሌሎች በውስጥ ያሉ ደግሞ ይኖራሉ፣ በሩን ስላገኙ እንዲገቡና እነርሱም እንዲኖሩ ከመርዳት የተሻለ ምን ነገር አለ? ስለዚህ እኔ በበሩ አጠገብ እቆያለሁ፡፡





ታላላቅ ቅዱሳን ወደ ውስጥ ዘልቀው ይገባሉ፣ በዚያ እጅግ ደስ በሚል ሥፍራ፣ ደስታና ሐሴት ነፍስን በሚያረካበት በዚያ እግዚአብሔር ባለበት ይሆናሉ፡፡ አዎን ወደ ውስጠኛው መግባት አለባቸው፣ የእግዚአብሔርን ጥልቀትና ስፋት፣ ምህረትና ፍቅር ማወቅ አለባቸው፣ ያኔ እኛንም ወደ ውስጥ ይጠሩናል፡፡ ውስጡም ምንኛ አስደናቂ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ ይህንን ሳስብ የእኔም ልብ ወደ ውስጠኛው ይከጅላል፣ ወደ ውስጥም ርቄ መሄድ እጀምራለሁ፡፡ ግን ወዲያውኑ የእኔ ቦታ በሩ አጠገብ መሆኑን እገነዘባለሁ፣ ስለዚህም በበሩ አጠገብ እቆያለሁ፡፡፡

በሩ አጠገብ ለመቆየቴ ሌላም ምክንያት አለኝ፡፡ አንዳንዶች ወደ ውስጥ ይገቡና፣ የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድ ይሰሙና፣ ታላቅነቱን ይገነዘቡና፣ ከቅድስናው ብዛት የተነሣ እኔ ውስጥ መሆን አልቻልኩም ይሉና መውጣት ይጀምራሉ፡፡ ልውጣ ልውጣ እያሉ መጮህ ይጀምራሉ፡፡ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ሊረዷቸውና ሊያድኑአቸው ሲገባቸው ይልቁኑ ያስበረግጓቸዋል፡፡ ወጥተው ከመሄዳቸው በፊት እግዚአብሔር እስከ መጨረሻ እንደሚወዳቸው የሚነግራቸው ሰው በሩ አጠገብ ያስፈልጋል፡፡

ከፍርሃትና ካለማወቅ የተነሳ በገቡበት በር ሊወጡ ያሉትን የሚመልስና በውስጥ መሆን ምንኛ ድንቅ ነገር እንደሆነ የሚነግራቸው ሰው ያስፈልጋል፡፡ ወደ ውስጥ ርቀው ያሉቱ ሊወጡ የተዘጋጁትን ሊያዩአቸው አይችሉም፣ ሀሳባቸው ሁሉ ውስጥ በሚየዩት ተዓምር ተይዟልና፣ ስለዚህ እኔ የሚወጡትን ለመመለስ በበሩ አጠገብ ልቆይ፡፡

ወደ ውስጥ ዘልቀው የሚገቡትን ሰዎች አደንቃቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን ከመግባታቸው በፊት እንዴት ተንከራታች እንደነበሩ ባይዘነጉ እወዳለሁ፡፡ ያኔ በሩ የት እንዳለ ያላወቁትንና ከውስጥ ደግሞ ወደ ውጭ ሊወጡ ያሉትን ሰዎች ሊረዱአቸው ይችላሉና፡፡ አንተ ወደ ውስጥ ርቀህ መሄድ፣ እዚያም ብዙ መቆየትና ከበሩ ውጭ ያሉትን ሰዎች መርሳት ትችላለህ፡፡

እኔ ግን ያ የለመድኩት ሥፍራ ይሻለኛል፡፡ በእግዚአብሔር አጠገብ ከእርሱ ልሰማ፣ እርሱም እዚያ መኖሩን ለማወቅ፣ ከሰዎች ሳልርቅ እነርሱንም ለመርዳት፡፡ የት ያሉትን ሰዎች? ከበሩ ውጭ በሺህና በሚሊየን የሚቆጠሩ፣ ከሁሉ ይልቅ ለእኔ የሚበልጠውን የእነዚህን ሰዎች እጆች እየያዝኩኝ ወደ በሩ መምራት፣ ከሚወዳቸው አምላክ ጋር ማገናኘት፡፡ ስለዚህ በበሩ

አጠገብ ልሁን፣ በሩን የሚፈልጉትን ልጠብቅ፡፡ የበር ጠባቂ ብሆን ይሻለኛል፡፡”

የዶ/ር ሳም ሾሜከር ውሳኔ እንዴት የሚያስቀና ውሳኔ ነው? እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ኃላፊነት አውቆ ያን ኃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም በየቀኑ የመኖር ውሳኔ፡፡ ይህ ጊዜ እግዚአብሔር በምድራችንና በዓለም ዙሪያ ሁሉ አስደናቂ የሆነ ሥራን እየሠራ ያለበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ዛሬ በዓለም ላይ በየቀኑ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች የምሥራቹን ወንጌል እየሰሙ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እየተጨመሩ ያሉበት ጊዜ ነው፡፡

በአገራችንም በኢትዮጵያ በየሳምንቱ በአማካይ አምስት ሺ ሰዎች በክርስቶስ አዳኝነት በማመን ወደ እግዚአብሔር መንግስት እየተጨመሩ ናቸው፡፡ ይህም ማለት በየአራት ዓመቱ አንድ ሚሊየን ሰዎች በአገራችን ብቻ ወደ ክርስቶስ በመምጣት ላይ ናቸው ማለት ነው፡፡ በእርግጥም መከሩ ብዙ ነው፣ የመከሩ ሠራተኞች ቁጥር ማነስ ግን ዛሬም እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር የመከሩን ሠራተኛ ይፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር አሁንም በዚህ ሰዓት “ማንን ልላክ ማንስ ይሄድልናል?” እያለ ነው፡፡ ለአንተም አሁን ባለህበት ሁኔታና ሥፍራ እግዚአብሔር እየተናገረህ ነው፡፡ የአንተስ ምላሽና ውሳኔ ምንድር ነው? ይህን ውሳኔ ማድረግ የምትችለው አሁን ነው፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ መክሊት ሰለተሰጣቸው ባሪያዎች ለማንበብ ከመቀጠልህ በፊት እግዚአብሔር ባስቀመጠህ ሥፍራ ሁሉ የመከሩ ሠራተኛ ለመሆን አሁን ወስን፡፡ አንተ ስትወስን እግዚአብሔርም በሕይወትህ ሊፈጽም የሚፈልገውን የራሱን ዓላማ ማከናወን ይጀምራል፡፡



## ምዕራፍ ሰባት

# *መክሊት የተሰጣቸው ባሪያዎች*

መክሊት ስለተሰጣቸው ባሪያዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማቴዎስ ወንጌል 25፡14-30 እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል 19፡12-27 የተጠቀሰውን ተመሳሳይ ታሪክ የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

በሁለቱም ወንጌላት ውስጥ ይህ ታሪክ የተነገረው ከወንጌል መልዕክት፣ ከሰዎች ደህንነትና ከመጨረሻው ዘመን ጋር በተያያዘ ሁኔታ መሆኑ የወንጌልን አደራ የተቀበልን እያንዳንዳችን ልናደርገው የሚገባንን ብርቱ ጉዳይ የሚያሳስበን በመሆኑ በጥሞና ልንመለከተው ይገባል፡፡

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ያለው የታሪኩ ዐውድ ወይም አገባብ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ከመገለጡ በፊትና በሚገለጥበት ጊዜ ሊሆኑ ስላላቸው ነገሮች፣ በማቴ. 24፡3 ላይ ደቀመዛሙርቱ ጌታን ለጠየቁት ጥያቄ ጌታ ከሰጣቸው መልሶች መካከል አንዱ የተሰጠንን የመክሊት አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ የሚያመለክተን ነው፡፡

በተለይም “ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል” /ማቴ. 24፡14/ የሚለው የክፍሉ ወይም የአውዱ ቁልፍ ቃል ሆኖ ሳለ ይህ የወንጌሉ አደራ የተሰጣቸው የእግዚአብሔር ባሪያዎች የተሰጣቸውን መክሊት ቀብረውት ወይስ ተጠቅመውና ትርፍ አግኝተው ጌታቸውን ይጠብቁ ይሆን? የሚለው ጥያቄ እያንዳንዱ ክርስቲያን ለራሱ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡

በሉቃስ ወንጌልም ውስጥ የሚታየው የመክሊት ታሪክ አገባቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቀራጮች አለቃ በነበረው በኃጢአተኛው በዘኬዎስ ቤት ተቀምጦ ሳለ፣ ጌታ ከዙፋኑ ወርዶ ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ “የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና” /ሉቃ. 19፡10/ በማለት ከገለጸ በኋላ፤ በቀጥታ

መክሊት ስለተሰጣቸው ባሪያዎች ጉዳይ ማንሳቱ ዛሬ በአደራ ተሰጥቶን በእጃችን ስለሚገኘው ስለ ወንጌል ያለንን ምላሽ፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እየሠራን ያለነውን ሥራ በሚገባ እንድናስተውልና እርምጃ ለመውሰድ እንድንነሳ የሚያደርገን ሁኔታ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የመክሊቱ ታሪክ በቀጥታ የክርስቶስ የሕይወቱ ዓላማ ከነበረው ከወንጌል ጋራ የተያያዘ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

## መክሊት ምንድር ነው?

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁሉ መክሊት ማለት አደራ፣ ንብረት፣ ችሎታ ወይም ስጦታ ማለት ነው፡፡ አንድ ጌታ እራሱ ያደረገውንና እንዲሁም ሊያደርገው የሚገባውን ጉዳይ ታማኞች ይሆናሉ፣ ይሠሩልኛል፣ ይፈጽሙልኛል ብሎ ላሰባቸው ሰዎች የሚያስተላልፈው አደራ ማለት ነው፡፡ ይህም እኛ ክርስቲያኖች ጌታ ከመመለሱ በፊት ልንታዘዘውና ልንፈጽመው የሚገባንን የወንጌልን አደራ የሚያመለክት ነው፡፡

በዚህ በተጠቀሰው በማቴ. 25፡14-30 በሚገኘው የመክሊት ታሪክ እንደምንመለከተው አንድ ጌታ ለባሮቹ እንደየአቅማቸው መክሊት ሰጥቶአቸው በመክሊቱ እንዲሠሩበትና ትርፍ ይዘው እንዲጠብቁት ካዘዛቸው በኋላ ዳግመኛ ወደ እነርሱ ተመልሶ ሊመጣ ወደ ሌላ አገር ይሄዳል፡፡ እነዚህም ባሪያዎች መክሊቱን ከተረከቡ በኋላ በመክሊቱ ምን እንደሚሠሩ የየራሳቸውን ውሳኔ ይወስናሉ፡፡ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል አደራ የተቀበልን እኛስ ከእነዚህ ባሪያዎች ሕይወት ምን ልንማር እንችላለን?

### 1. መክሊት የተሰጣቸው ሰዎች ባሪያዎች ናቸው /ማቴ. 25፡14/

ባሪያ ማለት የራሱ የሆነ ፈቃድ፣ ምርጫ፣ ንብረትና ሥልጣን የሌለው፤ ነገር ግን የጌታውን ፈቃድና ሀሳብ ለመፈጸም ሁለንተናውን ያስገዛ፣ ደስ ያለኝን ነገር ላድርግ ማለት የማይችል፣ በጌታው ሥልጣንና ቁጥጥር ስር ለመሆን የፈቀደ፣ ራሱን የጌታው ንብረት አድርጎ የሰጠ ማለት ነው፡፡ ባሪያ ማለት ለጌታው የሚታዘዝ፣ ጌታውን ለማስደሰትና ለማክበር የወሰነ ማለት ነው፡፡

እንግዲህ እኛ ራሳችንን ለጌታችን እንዴት እንዳስገዛንና ለእርሱም ክብር እንዴት እየኖርን እንዳለን ሕይወታችንን መመዘኑ አስፈላጊ





ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔ የጌታ ባሪያ ነኝ ወይ? የምፈጽመው የራሴን ፈቃድና ምርጫ ነው ወይስ የጌታዬን? በጌታዬ ሥልጣን ሥር ነኝ ያለሁት? ወይስ በራሴ ሥልጣን ደስ ያሰኘኝን በማድረግ? እኔ የኢየሱስ ብቻ ነኝ ወይስ ከኢየሱስ ሌላ ፈቃዴን፣ ስሜቴን፣ ሀሳቤን፣ ጊዜዬንና፣ ጉልበቴን የሚሻማ አለ? የጌታ ባሪያዎች ከሆንን ለጌታ እንታዘዛለን፡፡ እርሱም ለሚለን ነገር ሁሉ ራሳችንን በፈቃዳችን ለእርሱ እንሰጣለን፡፡ የእርሱን ጌትነት ካመንን የተሰጠንንም አደራ በታማኝነት እንጠብቃለን፡፡ 'አንተ የጌታ ባሪያ ነህ ወይስ የራስህ ጌታ ነህ?

### 2. የተሰጣቸው ትዕዛዝ ግልጽ ነው /ማቴ. 25፡14 ፤ ሉቃ. 19፡13/

ሦስቱም ባሪያዎች የተቀበሉት ጥሪና ትዕዛዝ በጣም ግልጽና ቀላል ነው፤ ይኸውም መክሊቱን ከጌታቸው እጅ በአደራ ተቀብለው ጌታቸው እስኪመለስ ድረስ እንዲሠሩበትና ትርፍ ይዘው እንዲጠብቁት ነው፡፡ ለሁሉም የተሰጣቸው አንድ ዓይነት ጥሪ ነው፡፡ መክሊቱን ላተረፉት ሁለቱ ባሪያዎች አንድ ዓይነት፣ ለቀበረው ለሦስተኛው ባሪያ ደግሞ ሌላ ዓይነት ትዕዛዝ አልተሰጠም፡፡

ወደ ሰዎች የመሄድና የምሥራቹን ወንጌል የመናገር ጥሪ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠው በጌታ ኢየሱስ አምኖ የዘላለምን ሕይወት ለተቀበለው ሁሉ እንጂ ለጥቂት ወይም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ኃላፊነታችንን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ጥቂት ሰዎች ብቻ የወንጌሉን ኃላፊነት እንዲወጡ በመተው ብዙዎቻችን ችላ ብለናል፡፡ ይህም ማለት መክሊቱን እንደቀበረው ባሪያ መሆን ማለት ነው፡፡ መክሊታችንን ከመቅበር ሕይወት ጌታ ያድነን!

### 3. ጌታቸው ያለውን ሁሉ አስረከባቸዋል /ማቴ. 25፡14/

ጌታቸው ለባሪያዎቹ ያለውን ሁሉ፣ ንብረቱን፣ ሥልጣኑን፣ ፈቃዱን ሰጥቶአቸው ነበር ወደ ሌላ አገር የሄደው፡፡ በዚያች አገር ጌታቸውን ወክለው በእርሱ ገንዘብ መሥራት የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት እግዚአብሔርን በምድር ወክለን የእርሱን

ሥራ እንድንሠራ ያለውን ሁሉ ሰጥቶናል፡፡ ፈቃዱን፣ ሥልጣኑን፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፣ ሹመቱን ሁሉንም ሰጥቶናል፡፡

ከዚህም በላይ ሰውንና እግዚአብሔርን እንድናገናኝ የማስታረቅን ቃል፣ የወንጌልን መልዕክት በእኛ አኖረ፡፡ "ሌሎችም ሰዎች እንደ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁና ወዳጆቹ እንዲሆኑ፣ የማስታረቅን አገልግሎት ለእኛ ሰጥቷል፡፡ ይህንን የማስታረቅ አገልግሎት አደራ ስለተቀበልንም፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ ሰዎችን ሁሉ ወዳጆቹ እንደሚያደርጋቸውና በደላቸውን እንደማይቆጥርባቸው እንሰብካለን፡፡ እኛ የክርስቶስ አምባሳደሮች ነን፡፡" (2ቆሮ. 5፡18-20፣ ሕያው ቃል) ጌታችን ኢየሱስ "አምባሳደሮቼ" ናችሁ ብሎ ሹመትን ሰጥቶናል፡፡

እንግዲህ አምባሳደር ሊሆን የሚችል ሰው ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ካሰብን የተሰጠን ሥራ ምን ያህል ልንጠነቀቅለት የሚገባን እንደሆነ ማሰብ እንችላለን፡፡ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ሁሉና ከዚያም በላይ የሆነውን እኛ ክርስቶስን ወክለን በምድር ላይ የመሥራት ኃላፊነት ተሰጥቶናል፡፡

ጌታ በምድር ላይ ያደረጋቸው ነገሮች፣ እርሱን ያሳዘኑት፣ እረፍት የነሱትና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ቅድሚያ የሰጣቸው ጉዳዮች ይኸውም የነፍሳት ደህንነት ፣ የአዝመራው መድረስና የእግዚአብሔርን ሥራ መፈጸም ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ የእርሱ ተከታዮች ከሆንን እኛንም ሊያሳዝን፣ ሊያስጨንቅና እረፍት ሊነሳን ይገባል፡፡ /ማቴ. 9፡35-36 ተመልከት፡፡/ ምክንያቱም እርሱ ሥራውን ሁሉ ለእኛ አስረክቦ ወደ አብ ቀኝ አርጓል፡፡ እርሱ የጀመረውንም ሥራ እኛ በዘመናችን እንድንሠራና እንድንፈጽም ይጠብቀናል፡፡

## 4. ጌታቸው በእርግጥ በክብር ይመለሳል /ማቴ. 25፡19፣ ሉቃ. 19፡15/

የእነዚህ ባሪያዎች ጌታ በሄደበት ሁኔታ ወይም ከዚህ በፊት በመካከላቸው በነበረበት ሁኔታ ሳይሆን የተመለሰው መንግሥትን ይዞ ማለትም ክብሮ፣ ነግሦና የበለጠ ሥልጣንን ይዞ ነበር (ሉቃ. 19፡12፡፡) የእኛ ጌታ ከዚህ በፊት ወደ ምድር በመጣበት ጊዜ ራሱን አዋርዶ፣ የባሪያን መልክ ይዞ፣ ውበትና ደም ግባት አጥቶ፤ በበረት ለመወለድ፣ በመስቀል ለመሞት፣ ከኃጢአተኞች መከራንና ግፍን ለመቀበል ነበር የመጣው፡፡ (ኢሳ. 53፤ ፊልጵ. 2፡5-8፡፡)





ጌታችን ዳግመኛ ሲመጣ ግን በሰማይና በምድር ያለውን ሥልጣን ሁሉ ጠቅልሎ፣ በሚያስደንቅ ክብርና ግርማ፣ በክብር ደመና፣ በመላዕክት አጀብ፤ ያስጨነቁትን ለማስጨነቅ፥ እርሱን ያፈቀሩትን ለማክበር በልዩ ክብርና ሥልጣን ይመጣል፡፡ /ማቴ. 24፡30፤ የሐዋ. 1፡11፤ ፊልጵ. 2፡ 9-11፤ ራዕ.1፡7/ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ግን እኛ በተሰጠን መክሊት ልናተርፍ፣ የተሰጠንን አደራ ጠብቀንና ፈጽመን ልንዘጋጅ ይገባል፡፡

በእንቅልፍ ብዛት መቅረዛችን ባዶ ሆኖ ሳይሆን በጊዜ ገዝተን ዘይት ሞልቶበት መጠበቅ ይኖርብናል /ማቴ. 25፡1-13/፡፡ ጌታችን በሚገለጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በየተራ በፊቱ ይቆማል፡፡ ጌታ ሆይ 'ይኸው አተረፍኩልህ' ወይስ 'የሰጠኸኝን ቀበርኩት' እያልን በፊቱ እንቆም ይሆን? /ማቴ. 25፡19/፡፡

## 5. ባሪያዎቹ ሁሉም የመሥራት ችሎታ አላቸው

በታሪኩ ውስጥ የምናገኛቸው ባሪያዎች መክሊቱ እንደየአቅማቸው ሲሰጣቸው በአቅማቸው የመሥራት ችሎታ እንዳላቸው ጌታ ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህም ነበር እንደየአቅማቸው የሰጣቸው፡፡ መሥራት የማይችሉትን ነገር አልጠየቃቸውም፡፡ የቀበረውም ባሪያ የመሥራት ፍላጎትና ፈቃደኝነት ስለሌለው ቀበረ እንጂ በመክሊቱም ቢሠራበት ኖሮ የእርሱም መክሊት እንደ ሁለቱ ባሪያዎች ትርፍ ያስገኝ ነበር፡፡ ስለዚህ ነበር ጌታው ክፉን ባሪያ "ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፣ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር" ብሎ የወቀሰው፡፡ /ማቴ. 25፡27/፡፡ ቢያንስ ለሌላ ለአንድ ሰው ቢያስተላልፍ ኖሮ ያ ሰነፍ ባሪያ ባልተወቀሰ ነበር፡፡

እኛ የክርስቶስን አዳኝነት ያደረገልንንም ነገር ቢያንስ ለአንድ ሰው መናገር እንችላለን ብዬ አምናለሁ፡፡ እንደበቱ መናገር የሚችል ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ይወድሃል፣ ኢየሱስ ያድናል ብሎ ለሌላ ሰው መናገር ይችላል፡፡ ወደ ዓለም ሁሉ ለመሄድ፣ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ለመስበክና የክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን እንደምንችል ባያውቅ ኖሮ እግዚአብሔር ሂዱ፣ ምስክሮቼም ሁኑ ብሎ ባላዘዘን ነበር፡፡ ነገር ግን መሄድ እንችላለን፣ የክርስቶስም ምስክሮች መሆን እንችላለን፡፡

## 6. ሁለቱ ባሪያዎች የምስጋና፣ የፍቅርና የመታዘዝ ሕይወት ነበራቸው

ያተረፉት ሁለቱ ባሪያዎች ከቀበረው ይልቅ ጌታቸውን ይወዳሉ፣ ያመሰግኑታል፣ ውለታ አለባቸው። ጌታ ሆይ ይህን ያህል ሰጥተኸኝ ነበር፣ እኔ ደግሞ ይህን ያህል መልጄ ከምስጋና ጋር እሰጥሃለሁ ይሉታል። ላደረገላቸው ነገር ክብርን ይሰጡታል። ይህንን ያንተን የከበረ አደራ ልንቀበል የሚገባን አልነበርንም፣ ግን አንተ ከሰጠኸን የምንችለውን ሁሉ አድርገናል ይሉታል። በፈቃዳቸው ትዕዛዙን ለመፈጸም እርሱንም ለማክበር ራሳቸውን ሰጡ። አፈቀሩት።

የተቀበሉትን አደራ ለመፈጸምና መክሊታቸውን ለማትረፍ ቀንና ሌሊት ተጉ። ጌታችን ከመመለሱ በፊት የተሰጠንን ጊዜ በጥበብ እንጠቀም አሉ። እነርሱም እንደ ጓደኛቸው የተሰጣቸውን ቀብረው ለራሳቸው ጉዳይ መሮጥና እጃቸውን አጣምረው የጌታቸውን መመለስ መጠበቅ ይችሉ ነበር። ነገር ግን ፈቃዳቸውን ለፈቃዱ፣ ጉዳያቸውን ለጉዳዩ፣ ፍላጎታቸውን ለፍላጎቱ፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ዘላለማዊ ዋጋ ላለው ለአንድ ነገር አስገዙ። በመክሊቱ ለመሥራትና ትርፍ ይዘው ጌታቸውን ለመጠበቅ!

## 7. ሁለቱ ባሪያዎች ለተሰጣቸው አደራ ታማኞች ነበሩ

አምስት መክሊት የተቀበለው ባሪያ ያተረፈው አምስት መክሊት ነበር። ሁለትም መክሊት የተቀበለው ባሪያ ያተረፈው ሁለት። ያተረፉትንም ለጌታቸው አስረከቡት። ጌታም የሁለቱንም ትርፍ በደስታ ተቀበለ። ሁለት ያተረፈውን አንተ እንደ ጓደኛህ ለምን ሌላ አምስት አላተረፍክም አላለውም። ጌታ ከእኛ የሚፈልገው ወንጌልን የምንመሰክርላቸውን ሰዎች ብዛት ሳይሆን የልብ ፈቃደኝነታችንንና ለእርሱም ያለንን ታማኝነት ነው። እነዚህን ባሪያዎች በታማኝነት ሚዛን ላይ ነበር ጌታ ያስቀመጣቸው። ሁለቱ ባሪያዎች ታማኞች ሲሆኑ ሦስተኛው ግን የማይታመንና ሰነፍ ነበር።

በግል ሕይወታችን፣ በቤታችን፣ በኅረቤትና እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ ሁሉ ለጌታ ያለን ታማኝነት እንዴት ይሆን? የተሰጠንን ዘመን ፈጽመን በጌታ ፊት በምንቆምበት ጊዜ "አንተ





በጎና ታማኝ ባሪያ፣ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" /ማቴ. 25፡21/ እንዲለን ዛሬውኑ ለጌታና ለተቀበልነው አደራ ታማኞች ልንሆን ይገባናል።

## 8. ሦስቱም ባሪያዎች በዓላማ ተጠርተዋል

ጌታ ሦስቱንም ባሪያዎች ሲጠራቸው እንዲፈጽሙለት የሚፈልገው ዓላማ ነበረው። ይህም ዓላማ ባሪያዎቹ እንዲታዘዙትና የሰጣቸውን መክሊት እንዲያተርፉ እንዲሁም እርሱ በሚመለስበት ጊዜ የሥራቸውን ዋጋ አግኝተው ደስታቸው ፍጹም እንዲሆን ነው። የተጠሩት ለእርሱ እንዲኖሩ፣ ፍሬ እንዲያፈሩ፣ ፍሬያቸውም እንዲበዛ፣ በዘመናቸውም የእርሱን ፈቃድ እንዲያገለግሉ ነው። እነዚህ ባሪያዎች ከጌታቸው የተቀበሉት ሁለት ዓይነት ጥሪ ሲሆን የመጀመሪያው ወደ እርሱ እንዲመጡና እርሱን እንዲያውቁት፣ ሁለተኛው ደግሞ የእርሱን ዓላማ የራሳቸው ዓላማ አድርገው እንዲኖሩ ነው።

ጌታ እኛን በመጀመሪያ ሲጠራን "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ" (ማቴ. 11፡28) በማለት ነው። ኃጢአተኞችና ሸክም የከበደብን በነበርን ጊዜ ወደ እርሱ ጠርቶ ከሸክማችን ካሳረፈን በኋላ ደግሞ የሚቀጥል ጥሪ አለ፡- "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ" (ማቴ. 11፡29) የሚል ጥሪ። የመጀመሪያው ጥሪ ከኃጢአት ቀንበር ነፃ ወጥተንና ደህንነትን አግኝተን የምናርፍበት ጥሪ ሲሆን የሁለተኛው ጥሪ ደግሞ የአገልግሎት ጥሪ፣ የጌታን ቀንበር የመሸከም ጥሪ ነው። ሦስቱም ባሪያዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ተጠርተዋል፣ ሦስቱም ደግሞ ቀንበሩን እንዲሸከሙ ተጠርተዋል።

ቀንበሩን በታማኝነት የተሸከሙት ግን ሁለቱ ብቻ ሲሆኑ ሦስተኛው ባሪያ ቀንበሩን አስቀምጦታል። ወንድሜ ሆይ ወደ ጌታህ መጥተህ እረፍትን ካገኘህ በኋላ የእርሱን ቀንበር እንድትሸከም ጥሪ ቀርቦልሃል። የእርሱን ቀንበር መሸከም ደግሞ ለነፍስ እረፍትን ይሰጣል። "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ።" /ማቴ.11፡29/። ቀንበሩን ተሸከመህ የነፍስህን ዕረፍት አግኝ። ቀንበሩን አታስቀምጥ፣ መክሊቱንም አትቅበር።

## 9. ሦስቱም ባሪያዎች የተሰጣቸው ጊዜ እኩል ነበር

የተሰጣቸው ጊዜ በመክሊታቸው ሠርተው ላተረፉት ረጅም፣ ለቀበረው ደግሞ አጭር ጊዜ ሳይሆን ሁሉም የነበራቸው ጊዜ እኩል ነበር፡፡ ልዩነቱ የጊዜያቸው አጠቃቀም ነበር፡፡ ያተረፉቱ ሁለቱ ጊዜያቸውን ለማትረፍ ሲጠቀሙ ሦስተኛው ግን ጊዜውን የተጠቀመው ጉድጓድ ለመቆፈርና መክሊቱን ለመቅበር ነበር፡፡ ልዩነታቸው የመታዘዝና ያለመታዘዝ፣ ፈቃደኛ የመሆንና ያለመሆን፣ ጥሪውን የመቀበልና ያለመቀበል፣ ጌታቸውን የማፍቀርና ያለማፍቀር፣ የጌታቸውን መልካምነት የማወቅና ያለማወቅ ልዩነት ነበር እንጂ የጊዜ ልዩነት አልነበራቸውም፡፡

ልዩነታቸው ትክክለኛ ምርጫን የመምረጥና ያለመምረጥ፣ በተሰጣቸው ጊዜ ፍሬን የማፍራትና ያለማፍራት፣ ታማኝ የመሆንና ያለመሆን፣ ዋጋ ለመክፈል የመወሰንና ያለመወሰን ልዩነት ነበር እንጂ፤ የጊዜ ልዩነት፣ የትዕዛዝ ልዩነት ወይም የጥሪ ልዩነት አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ጊዜ ሰጥቶናል፡፡ ውድ በሆነውና በሚያልፈው ጊዜያችን ተጠቅመን የማያልፍና ለዘላለም የሚኖር ፍሬ እንድናፈራ፣ መክሊታችንን እንድናተርፍ እግዚአብሔር ጠርቶናል፡፡

በሚቀጥለው ምዕራፍ የትውልዱ የወንጌል ባለአደራ የሆነ ክርስቲያን ያለበትን ኃላፊነትና እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን ተግባር ከማንበብህ በፊት ንባብህን ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም እንድታደርግ እጠይቅሃለሁ፡፡ እግዚአብሔር በዘመናችን በመንፈሱ ቀብቶ ካስነሳቸውና ተወዳጅ ከሆኑ መዘምራን መካከል አንዱ የሆነው ወንድማችን ተስፋዬ ጋቢሶ በተሰጠን መክሊት ስለማትረፍና የእግዚአብሔርን ሥራ ስለመፈጸም የዘመረውን መዝሙር በዚህ ጊዜ በማስተዋል እንድትዘምር እጋብዝሃለሁ፡፡

ከእግዚአብሔር ቃል በተጨማሪ ይህ መዝሙር የጊዜን ውድነትና በዚህ ውድ ጊዜ እግዚአብሔር ከእኔ ምን እንደሚጠብቅ እንድገነዘብ እኔን ስለረዳኝ አንተንም ሊረዳህ እንደሚችል አስባለሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በመዝሙሩ እንዲናገርህ ፍቀድለት፡፡ ጌታ አድርግ የሚልህንም ለማድረግ ፈቃደኛ ሁን፡፡ መክሊትህ ምን ያህል እያተረፈ እንዳለ ቆም ብለህ አስብ፡፡ በተሰጠህም መክሊት ለጌታህ ለማትረፍ ከዛሬ ጀምሮ በታማኝነት ሥራ፡፡ መዝሙሩም እነሆ፡-





ሲተጉ ለሚያገኛቸው ሲመጣ ጌታቸው
በመክሊታቸው የሠሩ ምስጋና አላቸው
አገልግሎቱን ያልናቀ በጥቂቱ ታምኖ
ሽልማቱን ይቀበላል ሥራው ተመዝኖ

ነፍሴም ወደ አምላኳ ሥጋም ወደ አፈሩ ሳይመለስ
ቶሎ ቶሎ ብዬ ሥራዬን ልጨርስ
ነፍሴም ወደ አምላኳ ሥጋም ወደ አፈሩ ሳይመለስ
ሌት ተቀን ልትጋና ሥራዬን ልጨርስ

አደራው ከቶ የማይገዳቸው ቸልተኞች
የጌታቸውን መመለስ የረሱ ዝንጉዎች
ዕድላቸው ለቅሶ ነውና ዋይታ እንዳይጠብቀኝ
መንፈስህ ዘወትር ያንቃኝ ለክብርህ ያቁመኝ

ጥቂት ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት
እንደሆነ መቼ አጣሁት ከቶ የኔ ሕይወት
ከእንግዲህ ታከተኝ ሳልል ልሩጥ ለጌታዬ
የሰነፍ ሰው ሞት እንዳልሞት ልትጋ ባላማዬ

መልካሙን ገድል ተጋድዬ አበቃሁኝ
ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ሩጫውን ጨረስኩኝ
ለማለት ልክ እንደ ጳውሎስ ተፈጸመ እንደ ኢየሱስ
ምስጋናዬንም እንዳቀርብ ለሠራዊት ንጉስ

መዝሙሩን ዝም ብለህ አንብበህ ብታልፍ ለሕይወትህ ትርጉም አይሰጥም፤ ነገር ግን በመክሊትህ እያተረፍህ እንደሆነ ጌታን ለማመስገን ወይም ደግሞ መክሊትህን ቀብረህ እንደሆነ በጌታ ፊት ንስሃ የምትገባበት የጸሎት ጊዜ አሁን እንደሚያስፈልግህ አስባለሁ፡፡ በዘላለም ፍቅሩ ለወደደን ጌታ እያተረፍክለት ያሉ መክሊቶችህ ምንድር ናቸው? በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የቀበርካቸው የጌታ መክሊቶችስ ምንድር ናቸው? በእነዚህ መክሊቶች ከዛሬ ጀምሮ ምን ልትሠራ ትወስናለህ?